


# መለኮታዊ መገለጥ

# ገነት

ሜሪ ኬ. ባክስተር
ከዶር. ቲ.ኤል ሎውሪ ጋር

# የመንግሥተ ሰማይ መለኮታዊ ራእይ

## በ ማርያም ካትሪን ባክስተር






-----------------------------------------

## መቅድም

የማርያም ካትሪን ባክስተር የተገለጹት ጽሑፎች በያሑዋሕ(በእግዚአብሔር) በመለኮታዊ የተቀቡ ናቸው፥ እናም በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ሰዎችን ባርከዋል። ያሑዋሕ ለእርሷ የሰጣትን መልእክት በስፋት ማሰራጨት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ። እርሷ እነዚህን ልምምዶች በየአመቱ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ቤተ ክርስቲያኖች ታካፍላለች። እርሷም አሁን እነዚህን ልምምዶች በመጽሐፍ መልክ አኑራቸዋለች።

የእርሷ የቀድሞ መጽሐፍ፥ ስለ ሲኦል መለኮታዊ ራእይ፥ የድኅነትን የዘላለም መልእክት ለጠፉት ነፍሳት ለማድረስ በያሑዋሕ በተለየ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። መጽሐፉ በብዙ የተለያዩ አገሮችና በብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች ታትሞ፥ በዓለም ዙሪያ ያሉት ሰዎች መጽሐፉን በጉጉት በስፋት ተቀብለውታል። ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሕትመቶች እስከ ዛሬ ድረስ ተሸጠዋል። ይህ መጽሐፍ፥ የመንግሥተ ሰማይ መለኮታዊ ራእይ፥ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ተቀባይነት እንደሚኖረው አምናለሁ።

ለብዙ ዓመታት የማርያም ካትሪን ባክስተር መጋቢ እንደመሆኔ፥ እርሷን በግል አውቃታለሁ፥ እኔም አገልግሎቷን በሙሉ እደግፋለሁ። ያሑዋሕ የእርሷን አገልግሎት በመቀባትና ይህን መልእክት እንዲህ በጣም ሰፊ ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረግ የእርሱን ፈቃድ በሥራዋ ላይ አኑሮአል።

ይህ መጽሐፍ የብዙ ጸሎቶች፣ እንባዎች፣ እና የብርቱ ሥራ ውጤት ነው። የመጽሐፉ ሰፊ ሥርጭት የብዙ ነፍሳት አዶናይን (ጌታን) ለማወቅ መንስኤ እንዲሆንና ዘላለምን በመንግሥተ ሰማይ ለማሳለፍ ዝግጅቶችን እንዲያደርጉ መንስኤ እንዲሆን እጸልያለሁ!

**-ቲ. ኤል. ሎውሪ፥ Ph.D.**

--------------------------------------------------------

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ከያሑዋሕ ጋር ኖረውኝ የነበሩትን ብዙ እውነተኛ ልምምዶች መግለጫ ነው። ይህ መጽሐፍ ከእውነታው የራቀ ልብ ወለድ ሥራ ወይም ይህ ህይወት ከሚያቀርበው በላይ የተሻለ ነገርን ተስፋ የሚያደርግ ሰው የቅዠት ሕልም አይደለም።

መንግሥተ ሰማይ እውነታ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የገለጽኳቸው ልምምዶችም እኔ ላይ እንደሆኑት እንደዛው ነው የተነገሩት። በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ከሚታየው እያንዳንዱን ነገር አላየሁም - ያን ለማድረግ ዘላለም ይወስዳል። በመንግሥተ ሰማይ ያየሁትን ሁሉ አላዛመድሁም/አላወራሁም፤ ጳውሎስ እንኳ ያንን አላደረገም። (2ኛ ቆሮንቶስ 12፥1-4 ተመልከቱ።) ነገር ግን ያሑዋሕ እንዳካፍለው የነገረኝን ሁሉ እያወራሁ ነው።

ለፓስተሬ ለሬቨረንድ ዶክተር ቲ. ኤል. ሎውሪ፣ እና ለውቧ ሚስታቸው ሚልድሬድ፥ ስለ ድጋፋቸው፣ ማበረታታቸው እና በዚህ ጥረት ውስጥ ዋጋ ያለው አስተዋፅኦዋቸው ልዩ አክብሮትና ምስጋና ልሰጥ እፈልጋለሁ። ለብሄራዊ የያሑዋሕ ቤተ ክርስቲያን (the National Church of God) ሠራተኞች እና በዚህ መጽሐፍ ላይ ስለጽሑፍ አዘገጃጅ አመራሩ ለሬቨረንድ ማርቆስ ቪ. ሃንድ ልባዊ ምስጋናዬን በድጋሜ መግለፅ እፈልጋለሁ። በተጨማሪም፥ የመንግሥተ ሰማይ መለኮታዊ ራእይ እና ስለ ሲኦል መለኮታዊ ራእይ ሁለቱንም ለሕዝቦች ለንባብ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማዘጋጀት በጣም በብዙ መልኮች በትጋት ያገለገሉትን፥ በኒው ኬንሲንግተን፥ ፔንሲልቬንያ በኋይቴከር ሃውስ ያሉትን ሁሉንም በምስጋና እውቅና እና ዋጋ መስጠት እፈልጋለሁ።

ይህን መልእክት እንዳካፍል የጠራኝን ያሑዋሕን አመሰግናለሁ። አምላኬ ያሑዋሕ-በጠራው አገልግሎቴ ያጠናከራችሁኝንና ያበረታታችሁኝን አመሰግናለሁ። ያሑዋሕ ሁላችሁንም ይባርክ!

-ማርያም ካትሪን ባክስተር

--------------------------------------------------------

# ከኢየሱስ ለካትሪን

**እነዚህ ነገሮች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና፥**

**ያሳየሁሽንና የነገርሁሽን ትጽፊና ትነግሪ ዘንድ ለዚህ ዓላማ ተወልደሻል።**

**ጥሪሽ አንድ መንግሥተ ሰማይ እና አንድ ሲኦል እንዳለ፣**

**እና እኔም ኢየሱስ፥ እነርሱን ከሥቃይ ላድናቸው**

**እና በመንግሥተ ሰማይ ቦታ ላዘጋጅላቸው**

**በአብ ተልኬ እንደነበር ዓለም እንዲያውቅ ማድረግ ነው።**

-------------------------------------------------------

# ደጆቹ ውስጥ

ያሕዌሕ፥ በማይወሰነው ምሕረቱና ጸጋው፥ መንግሥተ ሰማይ ወደሚባለው ውብ ቦታ እንድሄድ ፈቀደልኝ። ወደ እርሱ ቤት እና ወደ መሬት መመለስ ስለሆነው ጉዞዬ የተቀናጁ ገለጻዎች ለኔ ግልፅ አይደሉም። ነገር ግን ስለ እውነታው የተሳሳትሁ ልሆን አልችልም።

እንዴት ነበረ የመንግሥተ ሰማይ የማይነፃፀሩ ድንቆች እንደ እኔ ላለ ተራ ሰው ሊገለፅ የቻለው? መጀመሪያው ላይ ልጀምር።

አንድ ምሽት አዶናይ (ጌታ) ወደኔ መጣና ለልዩ አገልግሎት/የተሰጠ-ሥራ እንደተመረጥሁ ነገረኝ። እርሱ እንዲህ አለ፦ “*ልጄ ሆይ፥ ሰዎችን ከጨለማው አውጥቼ ወደ ብርሃኑ ውስጥ ለማምጣት ራሴን እገልጥልሻለሁ። እኔ ለዓላማ መርጬሻለሁ፡ እኔ የማሳይሽንና የምነግርሽን ነገሮች ልትጽፊና አንድ መዝገብ ልታዘጋጂ ነው።*”

ራሴን ለያሕዌሕ ሙሉ በሙሉ ሰጠሁ፥ አስገራሚም ነገሮች መሆን ጀመሩ። በሰዓቱ ከነበርኩበት ተወሰድሁና ወደ ውስጥ ሲኦል ተጓጓዝሁ። ሁሉንም አምስቱንም የስሜት ሕዋሳቶቼን አውቅ ነበረ: ማየት፣ መዳሰስ፣ መስማት፣ ማሽተት፣ እና መቅመስ እችል ነበር። ሆኖም፥ ይህ ከተፈጥሮ በላይ ሁነት ነበረ። በእኔ ላይ ያደረገው ተጽዕኖ ለዓላማ እንደነበረ ተገነዘብሁ።

በጌታ ወደ ሲኦል ከተወሰድሁ በኋላ ለቀናት በልቤ በጣም አዝኜ ነበረ። ካየኋቸው አሰቃቂዎች/ታላቅ-ፍርሃቶች የተነሣ ልቤ አዝኖና ተቸግሮ ነበረ። የያሕዌሕን ፍርድ በኃጢአት ላይ እና ወደ ሲኦል በሄዱት ሰዎች ላይ አይቻለሁ። በቅንነት ከልቤ ወደ ያሕዌሕ ጸልዩአለሁ እና የእርሱን መጽናኛ ፈልጌአለሁ።

እነዚህ ሁኔታዎች ከጀመሩ በሰላሳ አንደኛው ቀን፥ የኀያሉ የያሕዌሕ ኃይል በእኔ ላይ በድጋሜ ወረደ። ከጠዋቱ 2 ሰዓት ላይ (በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር: ከሌሊቱ 8 ሰዓት ላይ)፥ አንድ በጣም ግዙፍ ኃይለኛ መልአክ ከአልጋዬ አጠገብ ቆመ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከመልአኩ ኋላ ቆሞ ነበር። አዶናይ (ጌታ) እዛ እንደቆመ ፊቱን ስመለከት፥ እርሱ ወደኔ ፈገግ አለ፥ ነገር ግን እርሱ አንዳች ነገር አላለም።

በጣም ግዙፉ የያሕዌሕ መልእክተኛ እንዲህ አለ፦ “ያሕዌሕ ለእኔ አንድ ልዩ ተልዕኮ ሰጥቶኛል። እኔ እዚህ የተላክሁት ወደ መንግሥተ ሰማይ እንድወስድሽና የመንግሥተ ሰማይን አንዳንድ ክፍሎች/ቦታዎች እንዳሳይሽ ነው።”

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እርሱ በድጋሜ ተናገረ፥ “ነይ እና የያሕዌሕን ክብር እዩ!”

በአፋጣኝ፥ ከተፈጥሮበላይ በሆነ ሁኔታ ከቤቴ ተጓጉዤና ራሴን ከሰማያዊው መልአክ ጋር ከመንግሥተ ሰማይ ካሉት ደጆች ከአንዱ ውጪ ቆሜ አገኘቼው ነበር።

በዙሪያዬ ያየሁት የበዛ ውበት እጅግ አስደናቂ ነበረ! ሰማያዊው ፍጡር የለበሰው የሚያንጸባርቅ የብርሃን ልብስ ይመስላል። መልአኩ በቀስተደመና ቀለሞች የሚያንጸባርቁ ባለ ሦስታዊ ጎን - ቅርጽ ክንፎች ነበሩት። በድንገት ያልተደነቅሁ ቢሆንም፥ በሁሉም ዙሪያ እርግጥ በሆነው በማይገለጸው የያሕዌሕ ውበት ተገርሜ ነበረ።

ቀጥሎ የማውቀው ነገር፥ ብዙ ጊዜ እሰማው የነበረ ቃለ አጋኖ ድምፅ መልአኩ ደጋገመ:

“እነሆ፥ የያሕዌሕ ክብር!”

ከፊቴ በውበት የቆመው በጣም ውቡ ደጅ ከጠንካራ እንቁ ነበረ የተሠራው። በመደነቅ ከዚህ እጅግ ውብ እይታ የምችለውን ሁሉ ወደ ውስጤ ወሰድሁ። በዚህ ጊዜ ላይ፥ አዶናይን (ጌታን) የትም ቦታ ማየት አልቻልሁም፥ ነገር ግን በመንግሥተ ሰማይ ክብር በፍጹም/ሙሉ በሙሉ ተደስቼ ነበረ።

## *መንግሥተ ሰማይ እየገባን*

እዛ ስንደርስ፥ ሁለት በጣም ረጅም መላእክት ከደጁ ውጭ ቆመው ነበረ። ሁለቱም የሚያንጸባርቁ ልብሶች ለብሰውና በእጃቸውም ሰይፎች ይዘው ነበር። ጸጉራቸው እንደተፈተለ ወርቅ፥ ፊታቸውም በብርሃን ያበራ ነበረ።

እኔን እያጀበኝ ያለው መልአክ ደጁን እየጠበቁ ያሉትን ሁለቱን መላእክት ለማናገር ወደ እነርሱ ሄደ፥ እኔም ብቻዬን ቆሜ ቀረሁ። በመገረም እንዲህ ብዬ አሰብሁ፥ "አሀ፥ የመንግሥተ ሰማይ በሮች እንዴት የከበሩ/ያሸበረቁ ናቸው! ይህን ራሴው ማየቴ እንዴት ድንቅ ነው!" በድንገት፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ውስጥ ለመግባት በእርግጥ እየሄድሁ እንደሆነ ተገነዘብሁ።

የአዶናይን (የጌታን) መላእክት ስመለከት፥ እያደረጉ ከነበረው ውይይት አንዳንድ መስማት እችል ነበር። ከእነርሱ አንዳቸው ወደ ደጁ ውስጥ ገባና ወዲያውኑ ማለት ይቻላል ከአንድ ትንሽዬ መጽሐፍ ጋር ተመለሰ። መጽሐፉ ወርቃማ ሽፋን ነበረው፥ በውስጡ የተጻፈው ጽሑፍም ደግሞ በወርቅ ነበረ። ስለ ሕይወቴ ታሪክ የሆነ መጽሐፍ ይመስላል። ስሜ በሽፋኑ ላይ ታትሞ ነበረ: ***ማርያም ካትሪን ባክስተር***

የፈቃደኝነት ፈገግታ የመላእክቱ ፊት ላይ መጣ። እነርሱ መጽሐፉን ከፈቱት። እርስ በርሳቸው ተያዩ፥ ከዛ እኔ ልሰማው በምችለው ድምፅ:- "እርሷ ወደ ደጁ ውስጥ ልትመጣ ትችላለች።" አሉ።

የሚያስጎበኘኝ መልአኬ በእጹብ ድንቁ ደጅ ውስጥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ውስጥ አጀበኝ።

ወዲያው በድንገት፥ አየሩን በሙሉ ሙዚቃ ሞላው። ሙዚቃው በዙሪያዬ ሁሉ ነበረ። ከላዬ ነበረ። ተፈጥሮዬን/ህልውናዬን ዘልቆ የሚገባ ይመስላል። ከውብ ሙዚቃና ዝማሬ ኃይለኛ ሞገድ በኋላ ሞገድ በምድሩ በሙሉ በኃይለኛ እንቅስቃሴ ነበረ እና ማንኛውንም ነገር እና ሁሉንም የሚሸፍን ይመስላል።

ከተማው ውስጥ ስገባ፥ አግራሞት/መደነቅ ትንፋሼን ተቆጣጠረው። የዛ የማያነጻጽሩት ከተማ ገፀ ምድር ከገለጻ በላይ ነበረ። እስከዛሬ ካየኋቸው ሁሉ እጅግ ውብ፣ የሚያምሩ አስደናቂ አበባዎች በዙሪያዬ ነበሩ። እጅግ አስደናቂ አረንጓዴ ዕፅዋትና አትክልቶች በሁሉም ቦታ ነበሩ። እምቡጥ አበቦች እንኳ ለሙዚቃውና ለዝማሬው ሕይወት ያላቸው ይመስላሉ።

ሙዚቃ በዙሪያዬ መዞር ጀመረ። የሙዚቃው አካል የሆንሁ መሰለ።

የዚህን ከተማ ድንቆች ለመግለፅ መሞከር አንድ ነገር ነው፤ የከተማውን ደስታ እንደምታካፍሉ ማወቅ ሙሉ በሙሉ በጣም ሌላ ነገር ነው።

በደስታ የተሞሉ አንዳንድ የመንግሥተ ሰማይ ዜጋዎችን አየሁ፣ ሁሉም መጎናጸፊያ/ልብስ/ቀሚስ ለብሰው ነበረ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወደ እኔ መጣ:-

*አክሊልን እንደ ለበሰ ሙሽራ፥ በጌጥ ሽልማትዋም እንዳጌጠች ሙሽራ፥ የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፥ የጽድቅንም መጎናጸፊያ ደርቦልኛልና በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፥ ነፍሴም በአምላኬ ሐሤት ታደርጋለች።* (ኢሳይያስ 61፥10)

ከፊታቸው ላይ የሚያበራው ደስታውና ሐሤቱ ከንፅፅር በላይ/ባሻገር ነበረ።

መንግሥተ ሰማይ እውን ቦታ ነው። መንግሥተ ሰማይ የአንድ ሰው ልብ ወለድ ምናባዊ ነገረ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **ኢየሱስ** (**ያሕሹዋ**) እንዲህ እንዳለ ተጽፎአል:-

*ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤*

(የጌታችንና የመድኃኒታችን የንጉሣችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሐዋርያው ዮሐንስ እንደጻፈው 14፥1-2)

መንግሥተ ሰማይ ለተዘጋጁ ሰዎች የተዘጋጀ ቦታ ነው። እኛ እንደ **ያሑዋሕ** ልጆች/ልጅነታችን በዳግም ውልደት ተዓምር ስለተለወጥንና አዲስ ስለሆንን፥ እና አሁን እኛ በ**ክርስቶስ** አዲስ ፍጥረታት ስለሆንን፥ ዘላለም የምንኖርበት/የምናሳልፍበት ቦታ እኛን ባዳነን በአዳኙ መዘጋጀቱን ማወቃችን ታላቅ ደስታ ነው።

መንግሥተ ሰማይ ፍጹም ቦታ ነው። አዳኛችን **ፍጹም፣ ሁሉንቻይ እጅግ በጣም** **ኃያል አምላክ**፣ እና **ዘላለማዊ** ስለሆነ፥ መንግሥተ ሰማይ ፍጹም መሆን አለባት። ምክንያቱም **እርሱ** ለዘላለም ሁሉ ከ**እርሱ** ጋር እንድንኖር እዛ ቦታ እያዘጋጀልን ስለሆነ፥ ዘላለማዊ ቤታችንም ፍጹም ይሆናል። የዛን ሰማያዊ ቤት አንዳች/የትኛውንም ክፍል ምንም አያበላሸውም። እንዲያረክሰው ወይም እንዲያበላሸው እንዲገባ/ለመግባት የሚፈቀድለት አንዳች በፍፁም አይኖርም።

*ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።*

(ራእይ 21፥27)

መንግሥተ ሰማይ የየትኛውም ዓይነትና ገለፃ ኃጢአት እና ኃጢአተኞች የማይደርሱበት ነው። ሰይጣን ከዛ ሰማያዊ ቦታ ለዘላለም ተከልክሎአል/ተወግዶአል:

*ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥*

*ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት [መልአካዊ ሥራዊት] ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ።*

*በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥*

*ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም። ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥*

*ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።*

*ታላቅም ድምጽ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦ አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። ስለዚህ፥ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤ ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።*

*ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።*

(ራእይ 12፥3-4፤ 7-10፤ 12-13)

ያ እባብ፥ ሰይጣን፣ እና የእሱ ርኩሳን ተባባሪዎቹ/የጦር ጓዶቹ ወደ ንጹሑና ቅዱሱ የመንግሥተ ሰማይ የአየር ንብረት ውስጥ አስቀያሚ ራሳቸውን ዳግም በፍፁም አያቆሙም!

ኢጋንንት መንግሥተ ሰማይ መግባት አይችሉም። በ**ያሑዋሕ** ላይ ያመጹትና “*መኖርያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን*” (ይሁዳ 1፥6) የወደቁት መላእክት ወደ መንግሥተ ሰማይ መመለስ አይችሉም።

በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ምንም እጦት/እጥረት የለም። አካባቢውን ፍጹም እንደሆነ ለመጠበቅ ምንም ማብራሪያ አይተውም። (No detail will be left out to keep its environment from being perfect.)

በምድር ላይ የትም እንሂድ፥ የምንኖርበት ቦታ የትም ይሁን የት ወይም ቤቶቻችን እንዴትም ያህል ውድ ቢሆኑ፥ እነርሱን ፍጹም እንደሆኑ ለመጠበቅ ግልፅ ስህተቶችና እንከኖች አሉ። በንጽጽር፥ መንግሥተ ሰማይ የተባለውን ቦታ በመገንባት **ያሑዋሕ** ምንም ስህተቶች አልሠራም/አላደረገም። ክብሮቹ፣ ውበቶቹ፣ እና ድንቆቹ ከሰው የማብራራት ኃይላት በላይ/ባሻገር ናቸው። ሊገለፅ የማችይለው የዛ ውብ ቦታ ግሩም ውበት ለማየት የሚያስደንቅ ነው።

የሚያንጸባርቀው **የያሑዋሕ ልጅ** ብርሃን ነጸብራቅ ከኢያሰጲድ በተሠሩ ግድግዳዎች ላይ፣ ከዕንቁ በተሠሩ ደጆች ላይ፣ የማይቆጠሩ ቤቶች ላይ መሆኑ፣ እና ውቡ የሕይወት ውኃ ወንዝ በጥምረት ማንኛውም አርቲስት በበቂ/በአጥጋቢ ሁኔታ ሊያሳየው/ሊገልፀው ያልቻለው ሁኔታን ፈጥሮአል።

## የተቤዡት ነፍሳት ቤት

መንግሥተ ሰማይ ቋሚ/ዘለቄታዊ ቦታ ነው። ማንኛውም ጠላት የ*ያሑዋሕ*ን ገነት በፍፁም አያሸንፍም። የሕንጻዎቹ መናድ አይኖርም፣ የእቃዎቹ መበላሸት/መበስበስ አይኖርም፣ እና የአትክልቶቹ/ዕፅዋቶቹ መመንመን ወይም መሞት አይኖርም። ምንም ጭስ/ማደናገር ወይም ምንም ጨረር የ*ያሑዋሕ* ገነትን ቅዱስ የአየር ሁኔታ አይበክለውም።

ይህ ቋሚ፣ የሚኖር ቦታ ዘላለማዊ፣ የሚቀጥል/ቀጣይነት-ያለው ከተማ ነው። በሄቲ ቡየል (Hattie Buell) የተጻፈውን መዝሙር እንዘምራለን:

ድንኳን ወይ ጎጆ፥ ለምንድን ነው ምጨነቀው?

እነርሱ እዛ ለእኔ ቤተመንግሥት እየገነቡልኝ ነው፤

ከእርሱ ብሰደድም፥ አሁንም እዘምር ዘንድ ነው፤

ክብር ሁሉ ለ*ያሑዋሕ*፥ የ*ንጉሡ* ልጅ ነኝ።

በዛ በማይነፃፀር ቦታ፥ ቅዱሳን ከብስጭቶች/ቅሬታዎች፣ ከልብ ድካሞች፣ ከአሳዛኝ መከራዎች፣ እና ከአደጋዎች ሁሉ ጣፋጭ እርነት ያገኛሉ። ከእንግዲህ ወዲህ ኀዘን ወይም ወዮ አይኖርም። ከእንግዲህ ወዲህ ሥቃይ አይኖርም። ከእንግዲህ ወዲህ ጩኸት አይሆንም:

*እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና*

(ራእይ 21፥4)

በመንግሥተ ሰማይ ያየኋቸው ደስተኞቹ ዜጎች ከብዙ የተለያዩ ዘመናት እና አገሮች የመጡ ይመስላሉ። ልዩ ልዩ ሕዝቦች ለኔ ግልፅ መሰሉ። ከዛ ያነበብሁትን ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አስታወስሁ።

እነርሱም እንዲህ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ:

*"መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ፥ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥"*

(ራእይ 5፥9)

## *ያሑዋሕ*ን በማመስገን መቀጠር

በደስታ፥ ነፍሴ የ*ያሑዋሕ*ን ግርማ ሞገስ አመሰገነች! የሲኦልን ራእይ/ስለ ሲኦል ራእይ ሳይ የተለማመድኳቸው ኀዘኖች እና የተሠቃየሁበት ጥልቅ ኀዘን አሁን እጅግ የራቀ መሰለ። ይህ የመንግሥተ ሰማይ ራእይ ነበረ።

ጠቅላላ ቤተሰቦች በአንድ ላይ አየሁ። ሁሉም ሰው/እያንዳንዱ ሰው ደስተኛ፥ የሆነ ቦታ እየሄደ፥ የሆነ ነገር እያደረገ፥ ፈገግ እያለ ነበረ። አንድ ብርሃን ያየሁትን እያንዳንዱን ፊት አስውቦታል/አሳምሮታል።

በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ያሉ ቅዱሳን በሙሉ የተያዙ (occupied) ይመስላሉ። እነርሱ ሳያቋርጡ እየሠሩ (ባተሌ ሆነው) ነበረ። እነርሱ *ያሑዋሕ*ን በማመስገን እና ከፍ ከፍ በማድረግ/እጅግ-በማወደስ ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበረ። ዝማሬዎች በሁሉም ከንፈሮች ላይ ነበሩ። የሙዚቃ የአየር ሁኔታ ዋናው ሁኔታ ነበረ።

የፍፃሜ/የመጨረሻ መድረሻችንን አንዳንዶች በስህተት እንደሳሉት፥ በትርፍ ጊዜና በስንፍና ዘላለም አይታለፍም። በደመና ላይ ከመንሳፈፍ በላይ፣ በገና ከመደርደር በላይ፣ ወይም በሕይወት ወንዝ ውስጥ የእግር ጣቶቻችንን ከማወዛወዝ በላይ እናደርጋለን። ጊዜአችን ለ**ያሑዋሕ** በማገልገል ይያዛል። የዚህ አገልግሎት ዓይነት/ተፈጥሮ ምን እንደሆነ ብቻ መናገር አንችልም ፥ ነገር ግን የእርሱ ሕዝብ እንደሚያገለግሉት አንዳች ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

## ዕንቁዎች ነፍሳትን ለሚማርኩ / ነፍሶችን ለሚሰበስቡ

*//የጌታችንና የአዳኛችን የ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ወንጌል በ**መንፈስ ቅዱስ** መሪነት፥ ማቴዎስ 4፥19*

ዕንቁዎች-እያንጸባረቁ፣ እያንጸባረቁ፣ በጣም ውብ ዕንቁዎች-ዕንቁዎች በሁሉም ቦታ ማየት ችዬ ነበረ! አንዳንዶቹ ከኮንክሪት ማዕዘኖች በላይ ግዙፍ የሆኑ ነበሩ። ከእነዚህ ዕንቁዎች አንዳንዶቹ በምድር ላይ ነፍሳትን ይማርኩ ለነበሩ ሰዎች ትልቅ አስደናቂ ቤቶች (*ለመሥሪያ*) ይመስላሉ። በእያንዳንዱ ጊዜ የሆነ ሰው/አንድ ሰው አንድን ነፍስ ወደ **ክርስቶስ** ሲመራ፥ መንግሥተ ሰማይ ለዚያ ታማኝ ክርስቲያን ዕንቁ ታቀርባለች።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

*የጻድቅ ፍሬ የሕይወት ዛፍ ናት፥ ነፍሶችንም የሚሰበስብ እርሱ ጠቢብ ነው።*

(መጽሐፈ ምሳሌ 11፥30)

*ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።*

(ትንቢተ ዳንኤል 12፥3)

በዛ ውብ እና ታላቅ ያሸበረቀ ቦታ እየጠጣሁ ቆሜ ሳለ፥ አንድ እጅግ ግዙፍ፥ ውብ መልአክ በመንገድ ላይ ወደ ታች ሲመጣ አየሁ። በላዩ ላይ የወርቅ ጠርዝ ያለው አንድ ጥቅልል በእጆቹ ይዞ ነበረ።

መልአኩ ጥቅልሉን ከዚህ በፊት አይቼው በማላውቀው በተለየ ሁኔታ ከብራማ እቃ ተሠርቶ በነበረ በአንድ አምድ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠው። ባለ አራት ማዕዘኑ ጠረጴዛ በእርግጥ በብርሃን ያንጸባርቅ ነበረ።

ጥቅልሉ በላዩ ላይ ስም ተጽፎበታል። ከቅዱሳኑ አንዱ ጥቅልሉን አነሣውና ማንበብ ጀመረ።

"**ኢየሱስ** ዋናው ገንቢ ነው" በማለት በመንግሥተ ሰማይ ያለ አንድ ቅዱስ ነገረኝ። "ማን ዕንቁዎቹ እንደሚገባውና የት መሄድ እንዳለባቸው እርሱ ይወስናል። ይህ የያዝሁት ጥቅልል አንድን ሰው ወደ **ኢየሱስ** የመራ፣ ድሆችን የመገበ፣ የተራቆቱትን ያለበሰ - ታላቅ ነገሮችን ለ**ያሑዋሕ** ያደረገ የአንድ ሰው ሪፓርት ነው።"

*የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤*

*አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥*

*በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።*

*ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፡- እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።*

*ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥*

*ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።*

*ጻድቃንም መልሰው ይሉታል፡- ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?*

*እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?*

*ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?*

*ንጉሡም መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።*

*በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፦ እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።*

*እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።*

(ማቴዎስ 25፥31-41፣ 46)

## ቤት ለእያንዳንዱ ሰው

መልአኩ የአቀባበሉን መልእክት ደገመው: "ነይና የ**አምላክ**ሽን ክብር እዪ።"

በ**አዶናይ** (በ**ጌታ**) ምሪት፥ ይህን የመንግሥተ ሰማይ መግለጫ እንዳየሁት እየመዘገብሁ/እየጻፍሁ ነው። የተስፋዎቻችን እና የመሻቶቻችን ትኩረት ዘላለምን ሁሉ ከ**ጌታ**ችን ጋር ለማሳለፍ እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል። መንግሥተ ሰማይ ሕልሞች የሚፈጸሙበት ምድር ነው!

በዚህ ምድር ላይ ሥራዎቻችን እና ድካሞቻችን ከተፈፀሙ በኋላ ይህን ምድር ለቀን እዛ የምንሄድበት ስለሆነ ስለ መንግሥተ ሰማይ በጣም ጓጉቼአለሁ። **ያሑዋሕ** ከተማዋን አዘጋጅቶአል፥ እና **ኢየሱስ** እርሱን ለምናፈቅር ለእኛ እዛ ቦታ እያዘጋጀ ነው።

## ፍጹም ኅብረት

በ**ያሑዋሕ**ና በሰው መሐል ያለ የማይቋረጥ ኅብረት በመንግሥተ ሰማይ ሙሉ በሙሉ ይመለሳል።

አዳምና ሔዋን በኤድን ገነት ሳሉ፥ **ያሑዋሕ** ወደዚህች ምድር ጉብኝቶችን አደረገ። ከእርሱ ጋር የነበረው ኅብረት በኃጢአትና ባለመታዘዝ ከተሰበረ/ከተቋረጠ በኋላ፥ **ያሑዋሕ** ከሰዎች ጋር ኅብረት ለማድረግ ያለውን መሻቱን ማሳየት ቀጠለ።

ለሰዎች ያለው የእርሱ የመጨረሻ የፍቅሩ መግለጫ/ምልክት የራሱን ልጅ በአሰቃቂ መስቀል ላይ ምሕረትየለሽ/ጨካኝ ሞት እንዲሞት መስጠት ነበረ። በ**ክርስቶስ** ሞት እና ትንሣኤ በኩል፥ በ**ያሑዋሕ** እና በሰው መሐል የነበረው ኅብረት በድጋሜ የሚቻል ሆነ።

አሁንም እንኳ፥ የህይወት ሁኔታዎች ከ**ያሑዋሕ** ጋር ያለንን የጠለቀ ጓደኝነት/ወዳጅነት ሊያስታጉለው ይችላል። ነገር ግን፥ በመንግሥተ ሰማይ ምንም የሚያደናቅፉ/የሚያስታጉሉ አይኖሩም። **ከነገሥታት ንጉሥና ከጌታዎች ጌታ** ጋር ፍጹም ጓደኝነትን/ኅብረትን ታውቃላችሁ። ከእርሱ ጋር ኅብረት/ጓደኝነት ፍጹም/ሙሉ ይሆናል። መንግሥተ ሰማይ የሕያው አምላክ መኖሪያ ነው። መንግሥተ ሰማይ ከህዋ ሰማያት በላይ እና ከፕላኔቶችና ጋላክሲዎች(የከዋክብት ክምችቶች) በላይ አልፎ ነው። መንግሥተ ሰማይ "**ያሑዋሕ** የተቤዣቸው" (ትንቢተ ኢሳይያስ 62፥12) ዘላለማዊ ቤት ነው። በ**ክርስቶስ** እምነት በኩል ሁሉም የ**ያሑዋሕ** ልጆች ዘላለማዊ መድረሻ ነው።

በመንግሥተ ሰማይ "መኖሪያ" በተባለው ውስጥ በጣም በትንሽዬ ክፍል ውስጥ እጨናነቃለሁ ብላችሁ መፍራት አያስፈልጋችሁም። በዘመናት የተዋጁት ለክብር ወደ ቤት ሲሰበሰቡ፥ ከብዙዎቹ መኖሪያ ቤቶች፣ ከብዙዎቹ መኖሪያ ቦታዎች፣ አንዱን ለማግኘት ለሁሉም በቂ ቤት/ቦታ ይኖራል፥ **ኢየሱስ** እርሱ ለእኛ በ**አባቱ** ቤት ውስጥ እያዘጋጀልን እንደነበረ ያለውን:

*ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።*

*በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤*

*ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።*

*ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፥ መንገዱንም ታውቃላችሁ።*

(ዮሐንስ 14፥1-4)

መንግሥተ ሰማይ በእርግጥ ለሁሉም ቦታ አላት:

*ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤*

*በታላቅም ድምፅ እየጮሁ። በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።*

*መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ።*

(ራእይ 7፥9-11)

## እንባዎች በመንግሥተ ሰማይ

በአንድ ሁኔታ ላይ መልአኩ ወዳቆመኝና እንዲህ ወዳለኝ ወደ አንድ ልዩ/የተለየ ቦታ ተወሰድሁ:- "**ያሑዋሕ** የእንባዎች ክፍልን እንዳሳይሽ ፈልጎአል።"

ብዙ ጊዜያት በመዝሙሮች ውስጥ በርከት ባሉ ምንባቦች ስለ እንባዎቻችንና **ያሑዋሕ** እንዴት እንደሚጠብቀን /እንደሚያስብልን አንብባችሁ ይሆናል።

መላእክት እንባዎቻችንን ይይዙና በጠርሙስ ውስጥ ያስቀምጣሉ (መዝሙር 56፥8)። ብዙ ጊዜያት ይህ ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ ሽቼአለሁ።

እነዚህን ቃላት እያነበባችሁ ያላችሁ ብዙዎቻችሁ ለምትወዷቸው፣ ለልጆቻችሁ፣ ለጓደኞችሁ ወይም ለትዳር አጋራችሁ፣ ለቤተሰዎቻችሁ ብዙ እንባዎች እንዳለቀሳችሁ አውቃለሁ። በተለይ በመለያየት ወይም በመፋታት ውስጥ ካለፋችሁ፥ ሁሉም ተስፋ እንደሄደ/እንዳለቀ ተሰምቷችኋል። ስላጣችኋቸው ወዳጆቻችሁ አዝናችኋል።

**ያሑዋሕ** የእንባዎች ክፍል እንዳሳየኝ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። በጣም ውብ ነበረ። መልአኩ በር ወዳልነበረው ወደ አንድ እጹብ ድንቅ መግቢያ መንገድ ወሰደኝ።

ውስጡን ስመለከት፥ ክፍሉ ራሱ ትልቅ እንዳልነበረ ማየት ቻልሁ፥ ነገር ግን ከውስጡ የሚያንጸባርቀው ቅድስና እና ኃይል አስገረመኝ/አስደነቀኝ። የመስታወት መደርደሪያዎች ተደርድሮባቸው፥ የውስጡ ግድግዳዎች በብርሃን ያበራሉ።

በመደርደሪያዎቹ ላይ ብዙ ጠርሙሶች ነበሩ፥ አንዳንዶቹ ለሦስት እጅብ ብለዋል እና እንደ ንጹህ ብርጭቅ/መስታወት ይመስላሉ። ከሚያንጸባርቁት ብርጭቆ-መሰል እጅብ ያሉ ጠርሙሶች በታች ዝርግ ሰሃን የመሰለ ጌጥ በላዩ ላይ ስም ተጽፎበት ነበረ። እነዚህ ጠርሙሶች በክፍሉ ውስጥ ብዙ ነበሩ።

ከዛ ክፍሉ ውስጥ የከበረ የሚመስል አንድ ሰው አየሁ። የእርሱ ደማቅ ሐምራዊ ልብሱ በጣም ውብ ነበረ እና እንደ ከፋይ (ቬልቬት) ይመስላል።

ውድ-በሚመስል እቃ የተሠራ እና በሚያስደንቅ ውበት የሚያበራ አንድ ያሸበረቀ ጠረጴዛ፥ ከበሩ ውስጥ ነበረ። ከመጠን በላይ የሆነው ያየሁት ትእይንት አስደነቀኝ!

መጽሐፎች ጠረጴዛው ላይ ተጋድመው ነበር። መጽሐፍቱ በፍጹም አይቼው በማላውቀው እጅግ በጣም ውብ በሆነ ሐር-በሚመስል ጨርቅ ተሰፍተው ነበር። አንዳንዶቹ ዳይመንዶች፣ ዕንቁዎች፣ እና ፈትል በላያቸው ላይ ነበራቸው፤ ሌሎች በላያቸው ላይ አረንጓዴና ሐምራዊ ድንጋዮች ነበሯቸው። ሁሉም ተወሳስበው ተሠርተዋል።

ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፦ "አህ፥ **ያሑዋሕ** ሆይ፥ እነዚህ መጽሐፍት እንዴት ውብ ናቸው!" እኔ መጽሐፍትን እወዳለሁ። እነዚህ መጻሕፍት በተለይ ስበውኛል/ማርከውኛል። እነርሱ እጅግ የሚያምሩ ነበሩ። በትኩረት ስመለከታቸው እጅግ ተደንቄ ነበር።

በዚህ ቅጽበት በክፍሉ ውስጥ ያለው ሰውዬ እንዲህ አለኝ፦ "ነይና እዪ። ይህን ክፍል ላሳይሽ እፈልጋለሁ፣ እና ስለ እንባዎች ላብራራልሽ እፈልጋለሁ። እንደዚህ ክፍል ከሚመስሉ ከብዙ ክፍሎች ይህ አንዱ ብቻ ነው። የዚህ ክፍል ሃላፊ ነኝ።"

እርሱ ሲናገር፥ አንድ ግዙፍ መልአክ በመግቢያው መንገድ በኩል መጣ። የዚህ ሰማያዊ ፍጡር ውበት እና ሞገስ በጣም አስገረመኝ። እርሱ በፊቱ እስከታች ድረስ የወረደ ጠርዙ በወርቅ በሚገባ የተዘጋጀ የሚያበራ ነጭ ልብስ እንደለበሰ ልብ አልሁ። ርዝመቱ 12 ፊት (3.65 ሜትር) የሚያህል ይመስላል እና በጣም ረጅም ክንፎች ነበሩት።

መልአኩ በእጆቹ ትንሽዬ ጎድጓዳ ሣህን ይዟል። ወርቃማው ጎድጓዳ ሣህን በፈሳሽ ተሞልቷል (ራእይ 5፥8 ተመልከቱ)። በክፍሉ ውስጥ ያለው ሰውዬ ይህን ነገረኝ፦ "እርሱ ከምድር/ከመሬት በአንድ ጎድጓዳ ሣህን ውስጥ እንባዎች አሁን አመጣልኝ። በዚህ ምን እንደምናደርግ እንድታዪ እፈልጋለሁ።"

መልአኩ ጎድጓዳ ሣህኑን ከትንሽዬ/ከቁራጭ ወረቀት ጋር አስረከበ። ማስታወሻዋ በጉድጓዳ ሣህን ውስጥ ያለውን የእንባዎችን ባለቤት ሰው ስም ይዛለች።

በክፍሉ ውስጥ ያለው ሰውዬ ማስታወሻዋን አነበበና ጠርሙሶች ተቀምጠውባቸው ከነበሩት ቦታዎች ወደ አንዱ ቦታ ሄደ። ከጠርሙሱ በታች የነበረ ዝርግ ሰአን የመሰለ ጌጥ አነበበ፥ እርሱ ያነበበውም በማስታወሻዋ ላይ ከተጻፈው ሰው ስም ጋር እንደሚመሳሰል አወቅሁ።

ሰውዬው ሙሉ ሊሆን የደረሰውን ጠርሙስ አነሣና ወደ ጎድጓዳ ሣህኑ አመጣው። እርሱም እንባዎቹን ከወርቃማው ጎድጓዳ ሣህን ወደ ጠርሙሱ ውስጥ በማፍሰስ ጨመራቸው።

"እዚህ ምን እንደምናደርግ ላሳይሽ እፈልጋለሁ።" በማለት ሰውዬው ለእኔ ተናገረ። "በምድር ላይ ላሉ ሰዎች ስለዚህ ንገሪያቸው።" ከዛ እርሱ ጠርሙሱን ወደ ጠረጴዛ ላይ ወሰደው፥ ከመጽሐፎች አንዱን አነሣ፥ ከፈተው፥ እና "ተመልከቺ!" አለ።

በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ገጾች ሙሉ በሙሉ ባዶ ነበሩ። የክፍሉ ጠባቂ እንዲህ አለኝ፦ "እነዚህ በምድር ላይ ያሉ የ**ያሑዋሕ** ቅዱሳን ወደ **ያሑዋሕ** ሲጮኹ የሆኑ እንባዎች ናቸው። ምን እንደሚሆን እዪ።"

ከዛ ሰውዬው በመጽሐፉ የመጀመሪያው ገጽ ላይ ከጠርሙሱ ውስጥ አንድ ጠብታ ጠብ አደረገ፥ አንድ ጥቂት የእንባ ጠብታ። እርሱ ሲያደርግ፥ ቃላቶች ወዲያውኑ መታየት ጀመሩ። በድንቅ/በጸጋ የእጅ ጽሑፍ የተጻፉ ውብ ቃላቶች፥ ገጹ ላይ መታየት ጀመሩ። አንድ እንባ ገጹ ላይ ጠብ ባለ በእያንዳንዱ ጊዜ የሙሉ ገጽ ጽሑፈት ታየ። እርሱ ይህን ከገጽ ገጽ፣ ከጊዜ ጊዜ በተደጋጋሚ ማድረግ ቀጠለ።

መጽሐፉን ሲዘጋና ሲናገር፥ ለሰዎች ሁሉ እንዲሁም ለእኔ የሚናገር ይመስላል፦ "እጅግ በጣም ፍጹም ጸሎቶች በምድር ላይ ካሉት ከወንዶችና ከሴቶች ልቦችና ነፍሶች የመጡት በእንባ የታጠቡት ናቸው።"

ቀስተደመና ክንፎች ያሉት መልአክ እንዲህ አለኝ፦ "ነይ እና የ**ያሑዋሕ**ን ክብር እዪ።"

## ያሑዋሕ መጽሐፉን ከፈተ

ወዲያው፥ ሺሆችና ሺሆች ሰዎችና ሰማያዊ ፍጡራን ወዳሉበት ወደ አንድ ግዙፍ ቦታ ተጓጓዝን።

አህ፥ ውብ ነበረ!

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰዎቹ እየደበዘዙ የሚሄዱ መሰሉ፥ እናም የላቀ የያሑዋሕ ክብር መገለጥ በሁሉም ቦታ መታየት ጀመረ። የያሑዋሕ የላቁ/ከፍተኛ ምስጋናዎች ነጎድጓድማ እየሆኑ መጡ።

መልአካዊው መልእክተኛ ወደ ያሑዋሕ ዙፋን ወሰደኝ።

አንድ ግዙፍ ደመና፥ ጭጋግ አየሁ፥ እኔም በደመናው ውስጥ የሕያውን መልክ አየሁ። የያሑዋሕን ፊት ማየት አልቻልሁም፥ ነገር ግን የያሑዋሕን ክብር እና ከዙፋኑ በላይ ቀስተደመና አየሁ። የያሑዋሕን ድምፅ ሰማሁ፥ ድምፁም ለእኔ የተሰማው ዮሐንስ እንደገለጸው እንደዛው ነው: "እንደ ብዙ ውኃም ድምፅና እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፥" ራእይ 14፥2። በዚህ ኀያል ሰፊ ቦታ (arena)፥ ከዙፋኑ አጠገብ ብዙ ፈረሶችን ከጋላቢዎቹ ጋር አየሁ።

ወዲያውኑ፥ በያሑዋሕ ዙፋን ፊት አንድ መጽሐፍ በግዙፍ መሠዊያ ላይ ተቀምጦ አየሁ። መላእክት በእርሱ ፊት ሲሰግዱ አየሁ። በመደነቅ ቆሜ፥ ይህን ሁኔታ አየሁ፥ እናም እንድ ሰው እጅ የሚመስል ከደመናው ወጣና መጽሐፉን ከፈተው።

መጽሐፉን የከፈተው የያሑዋሕ እጅ እንደነበረ በሆነ ሁኔታ አወቁአለሁ።

ተገርሜ፥ ከመጽሐፉ ውስጥ እንድ ጭስ የሚመስል ወደ ላይ ሲወጣ አየሁ። ወዲያው፥ አሽትቼ የማላውቀው እጅግ በጣም ውብ ሽቶ የቆምኩበትን ቦታ በሙሉ ሞላው። ይህ መጽሐፍ የቅዱሳንን ጸሎቶች እንደያዘ እና ያሑዋሕ ከቅዱሳን ልቦች የወጣውን ጩኸቶች ጸሎቶቹን ለመመለስ (ለጸሎቶቹ መልስ ለመስጠት) መላእክቱን ወደ ምድር እየላከ እንደነበረ መልአኩ ነገረኝ። ሁሉም ያሑዋሕን እያመሰገነና ከፍ እያደረገ ነበረ።

ያሑዋሕ መጽሐፉን ሲከፍት፥ ገጾች ከመጽሐፉ ወጡና በፈረሶች ላይ ወደነበሩት መላእክቶች እጆች ውስጥ በረሩ። የእርሱን ድምፅ መስማት እችል ነበር፥ "እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ፥" እየጮኸ እንዲህ አለ፥ "***ሂዱ፥ የእርሷን ጸሎቶች መልሱ! ሂዱ፥ የእርሱን ጸሎቶች መልሱ!***"

*አምላክ ሆይ፥ ሕይወቴን ነገርሁህ፤ እንባዬን እንደ ትእዛዝህ በፊተህ አኖርህ።*

*በጠራሁህ ጊዜ ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤ አንተ አምላኬ እንደ ሆንህ እነሆ፥ አወቅሁ።*

*በእግዚአብሔር ቃሉን አመሰግናለሁ፤ በእግዚአብሔር ቃሉን አከብራለሁ።*

*በእግዚአብሔር ታመንሁ፥ አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?*

*You number my wanderings;*
*Put my tears into Your bottle;*
*Are they not in Your book?*
*When I cry out to You,*
*Then my enemies will turn back;*
*This I know, because God is for me.*
*In God (I will praise His word),*
*In the LORD (I will praise His word), ' In God I have put my trust;*
*I will not be afraid.*
*What can man do to me?*

(መዝሙር 56፥8-11)

ሕያው **የያሑዋሕ ቃል ያሑዋሕ** በእንባዎቻችን ምን እንደሚያደርግ ያብራራልናል። **የአምላካችንን** ክብሩን እና ድንቁን መረዳት ምን ያህል ውብ ነው! የርኅራኄው ተቀባይ መሆን እንዴት ግሩም ነው! እርሱ ስለ እንባዎቻችን እንኳ ያስባል/ይጨነቃል።

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስለ እንባዎቻችን፣ ስለ ሐዘኖቻችን፣ እና **ያሑቫሕ** ለእኛ ስላለው መጽናኛ/ምቾት ይነግሩናል። ይህን አንብቡና ደስ ይበላችሁ:

*የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።*

*ጸሎትህን ሰምቻለሁ፥*

*እንባህንም አይቻለሁ፤ እነሆ፥ እፈውስሃለሁ፤*

(2 ነገሥት 20፥5)

*በጭንቀቴ ደክሜያለሁ፤ ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፥ በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።*

*ዓይኔ ከቍጣ ዕንባ የተነሣ ታወከች፤ ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ አረጀሁ።*

*ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ፥ ከእኔ ራቁ፥ እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና።*

*እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ፤ እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ።*

(መዝሙር 6፥6-9)

*ነፍሴን ከሞት፥ ዓይኔንም ከእንባ፥ እግሬንም ከመሰናከል አድኖአልና።*

(መዝሙር 116፥8)

*በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ።*

*በሄዱ ጊዜ፥ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ፤ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ።*

(መዝሙር 126፥5-6)

*ሞትን ለዘላለም ይውጣል፥ ጌታ እግዚአብሔርም ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፥*

(ኢሳይያስ 25፥8)

*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ድምፅሽን ከልቅሶ ዓይንሽንም ከእንባ ከልክዪ፤ ለሥራሽ ዋጋ ይሆናልና፥ ከጠላትም ምድር ይመለሳሉ።*

(ኤርምያስ 31፥16)

*በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።*

(ራእይ 7፥17)

*እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና*

(ራእይ 21፥4)

*እግዚአብሔርም የተቤዣቸው ይመለሳሉ እየዘመሩም ወደ ጽዮን ይመጣሉ፤ የዘላለም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል፤ ሐሤትንና ደስታን ያገኛሉ፥ ኀዘንና ትካዜም ይሸሻሉ።*

(ኢሳይያስ 35፥10)

ክብር ለ**ያሑዋሕ**፥ መንግሥተ ሰማይ እውን ቦታ ነው! እኛ የእውን እዛ እንሄዳለን። እና፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ስንሄድ በደመና ላይ የምንንሳፈፍ የጭስ እንፋሎቶች አንሆንም።

ስለ መንግሥተ ሰማይ ከአስደናቂ ነገሮች አንዱ **በያሑዋሕ ቃል** ውስጥ ቃል እንደተገባው እንባዎቻችንና ኀዘኖቻችን በዘላለማዊ ደስታ መተካታቸው ነው። ሆኖም ገና፥ ተጨማሪ በጣም ብዙ አለ!

---

# የያሑዋሕ ዙፋን

መንግሥተ ሰማይ እውን ቦታ ነው። መንግሥተ ሰማይ ልክ / ስህተት-የሌለበት መድረሻ ነው። አንድ አላፊ ጠፊ ሕልም አይደለም፥ አንድ የታሰበ ራዕይ አይደለም። **ያሑዋሕ** ብዙዎቹን የመንግሥተ ሰማይ እውነታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል ለሁላችንም ገልፆልናል።

## አንደኛው ሰማይ

አንደኛ፥ አንድ ህዋዊ ሰማይ አለ። ይህ በምድር ዙሪያ ያለው ህዋ ነው። ወፎች የሚበሩበት እና ንፋሶች የሚነፍሱበት ነው። ዝናብ/ካፊያ ወይም በረዶዎች፥ አውሎ ነፋሶች፥ ጭጋጎች፥ እንፋሎቶች፥ እና ደመናዎች የሚሆኑበት/የሚመሰረቱበት ነው። ሰማይ በሐዋርያት ሥራ 1፥11 መልአኩ ሐዋርያትን ለምን "ወደሰማይ እየተመለከታችሁ" ብሎ ሲጠይቃቸው የጠቀሰው ቦታ ነው። **ኢየሱስ**፥ ከ**አባቱ** ጋር ሲነጋገር፥ "ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አነሣና" (ዮሐንስ 17፥1) ፥ ወይም ወደ ሰማይ።

## ሁለተኛው ሰማይ

ከዛ፥ የጠፈር/ቦታ ሰማይ አለ። ይህ የፀሐይ፣ የጨረቃ እና የከዋክብት አካባቢ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሶአል። ጥቂቶቹ እዚህ ቀርበዋል:

*በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፤*

(ዘፍጥረት 22፥17)

*ዓይኖችህን ወደ ሰማይ አንሥተህ አምላክህ እግዚአብሔር ከሰማይ ሁሉ በታች ላሉት አሕዛብ ሁሉ የሰጣቸውን ፀሐይንና ጨረቃን ከዋክብትንና የሰማይን ሠራዊት ሁሉ ባየህ ጊዜ፥ ሰግደህላቸው አምልከሃቸውም እንዳትስት ተጠንቀቅ።*

(ዘዳግም 4፥19)

*በውኑ የሰባቱን ከዋክብት ዘለላ ታስር ዘንድ፥ ወይስ ኦሪዮን የሚባለውን ኮከብ ትፈታ ዘንድ ትችላለህን?*

*ወይስ ማዛሮት የሚባሉትን ከዋክብት በጊዜያቸው ታወጣ ዘንድ፥ ወይስ ድብ የሚባለውን ኮከብ ከልጆቹ ጋር ትመራ ዘንድ ትችላለህን?*

*የሰማይን ሥርዓት ታውቃለህን? በምድርስ ለይ እንዲሠለጥን ልታደርግ ትችላለህን?*

(ኢዮብ 38፥31-33)

*የሰማይም ከዋክብትና ሠራዊቱ ብርሃናቸውን አይሰጡም፥ ፀሐይም በወጣች ጊዜ ትጨልማለች፥ ጨረቃም በብርሃኑ አያበራም።*

(ኢሳይያስ 13፥10)

*ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ።*

(ማቴዎስ 24፥29)

## ሦስተኛው ሰማይ

ነገር ግን፥ የጻድቃን መድረሻ፥ ከህዋ እና በከዋክብት ከተሞሉት ሰማያት አልፎ ነው። ይህ ቦታ ሐዋርያው ጳውሎስ በ 2ኛ ቆሮንቶስ 12፥2 “*ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ።*” በማለት ሲጽፍ የጠቀሰው ነው።

መንግሥተ ሰማይ፥ በዚህ መጽሐፍ ሙሉ ይህን ቃል ስጠቀም፥ እንደ ቅርብ የ**ያሑዋሕ** ሕልውና/መኖር በተደጋጋሚ / ብዙ ጊዜ የተነገረለት አካባቢ ነው:

*ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰራች፥ የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት አልገባምና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ ወደ ሰማይ ገባ።*

(ዕብራውያን 9፥24)

መንግሥተ ሰማይ **ያሑዋሕ** የሚኖርበት ቦታ ነው። **ኢየሱስ** ለመጸለይ ሲያስተምረን፥ “በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ” በማለት ወደ እርሱ እንድንጸልይ አለ (ማቴዎስ 6፥9)።

በ 1ኛ ነገሥት 8፥30፥ መንግሥተ ሰማይ የ**ያሑዋሕ** መኖርያ ቦታ ተብሎ ተጠርቶአል። በ መዝሙር 11፥4 መንግሥተ ሰማይ የ**ያሑዋሕ** ቅዱስ መቅደስ እና የእርሱ ዙፋን ያለበት ቦታ ተብሎአል።

እዛ፥ በ**ያሑዋሕ** መለኮታዊ ግርማ ሞገስ መቅደስ ውስጥ፥ የእርሱ እጅግ በጣም ጥሩ / ከፍተኛ ክብር እጅግ በጣም ጉልህ በሆነ ሁኔታ ተገልጦአል። መንግሥተ ሰማይ የተቀደሰ የብርሃን፣ የደስታ፣ እና የክብር ቦታ ነው። መገኛው የት እንደሆነ በትክክል አናውቅም፥ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ መንግሥተ ሰማይ “እላይ፥” እንደሆነ ተመልክቶአል።

**ሁሉን የሚችል ያሑዋሕ ኤሎሂም**(**አምላክ**) በሰማይ እንደሆነ እናውቃለን። እዛ **እርሱ** እና **ኢየሱስ ክርስቶስ** የቅዱሳን፣ የመላእክት፣ እና የሁሉም አምላኪ ፍጥረታት ማዕከላዊ ትኩረት ናቸው።

እንዴት የከበረ ስብስብ ነው በሰማይ ውስጥ ያለው! መላእክት እዛ ናቸው ምክንያቱም ኢየሱስ:- “መላእክቶች በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ” ብሏል። (ማቴዎስ 18፥10)።

ቅዱሳን እዛ ናቸው ምክንያቱም ኢየሱስ “እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ” በማለት ቃል ገብቶልናል። (ዮሐንስ 14፥3)። በ1ኛ ጴጥሮስ 1፥4 በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ርስት እንደተጠበቀልን ይነግረናል - የማይጠፋ፥ እድፈትም የሌለበት፥ የማያልፍም ርስት።

ቅዱሳን፥ በመንግሥተ ሰማይ ስላደረግሁት ውብ ጉብኝቴ መመስከር ያስደስተኛል። ስላየኋቸው ነገሮችና ስላየኋቸው ሰዎች ለእናንተ ለመንገር በደስታ ስሜቴ ተነክቷል።

## የመንግሥተ ሰማይ ምስጋና/ውዳሴ

የ**ያሑዋሕ** መልአክ የእንባዎችን ክፍል ካሳየኝ በኋላ፥ በመንግሥተ ሰማይ ባደረግሁት ጉብኝቴ ሁሉ ቦጣም በተደጋጋሚ የሰማሁትን የተደጋገመውን ቃል መልአኩ ደገመው: “ነይ እና የ**አምላክ**ሽን ክብር እዩ!”።

የመንግሥተ ሰማይ ብሩሕነት፣ ማራኪ ውበት፣ ግሩም ውበት እጅግ አስደነቀኝ። ካየሁት ከእያንዳንዱ ነገር ሁሉ የሚፈነጥቅ የሚመስለው የክብር ኀያል ብርሃን/ድምቀት በድንቅ አግራሞት ሞላኝ። የዚያ መልካም ምድር ውበትና ፍጹም ደስታ አንድ ሰው ለራሱ እስካላየው ድረስ በአእምሮ ዓይን በትክክል ሊሳል አይችልም።

በዚያ ቅጽበት፥ አንዴ የሆነ ሰው ሲጠቅሰው የሰማኋቸውን ቃላት አሰብሁ:

*የመንግሥተ ሰማይ ብርሃን*

***የኢየሱስ ፊት*** *ነው።*

*የመንግሥተ ሰማይ ደስታ*

***የኢየሱስ ኅልውና/መገኘት*** *ነው።*

*የመንግሥተ ሰማይ ውህደት*

***የኢየሱስ ውዳሴ/ምስጋና*** *ነው።*

*የመንግሥተ ሰማይ አርእስት*

***የኢየሱስ ሥራ*** *ነው።*

*የመንግሥተ ሰማይ ሥራ*

***የኢየሱስ አገልግሎት*** *ነው።*

*የመንግሥተ ሰማይ ሙላት/ሙሉነት*

***ኢየሱስ ራሱ*** *ነው።*

ከመልአኩ ጋር ስሄድ፥ ሁሉም ቦታ ሐሴት፣ ሰላም፣ እና ደስታ መስማት(feel) ችዬ ነበረ። አሳቦቼ በምድር ወዳሉት ቤተሰዎቼ ሄዱ፥ መልአኩ አሳቦቼን ያወቃቸው መሰለ። እርሱ እንዲህ አለኝ:- “**ለያሑዋሕ** መፈጸም ያለብሽ አንድ ተልዕኮ አለሽ። እላይ እዚህ ምን እንዳለ በምድር/በመሬት ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ልትነግሪ ነው። **ያሑዋሕ** የሰማይን የተወሰነ እያሳየሽ ነው፥ ሁሉንም ግን አይደለም። ነይ እና የ**አምላክ**ሽን ክብር እዩ።”

መዳረሻችን ስንደርስ፥ ብዙ፣ ብዙ ድምፆች **ለያሑዋሕ** ምስጋናዎችን/ውዳሴዎችን ሲዘምሩ መስማት ችዬ ነበር።

በመንግሥተ ሰማይ ያሉት የአምላኪዎቹ እጅግ ውብ ሙዚቃ ነፍሴን በደስታ ስሜት ነካት። ሱራፌል እና ቅዱሳን ማለቂያ የሌለው የውዳሴ/የምስጋና መዝሙር በደስታ ተሞልተው ሲዘምሩ አክብሮት እና ክብር በሰፊው የሰማይ ክልል በሙሉ በተደጋጋሚ አስተጋባ።

# ዙፋኑን እየቀረብን

ነፍሴ እጅግ በጣም ደስተኛ ሆና በደስታ ተጓጓዘች። የያሑዋሕን ዙፋን እየቀረብን እንደሆነ በሆነ መንገድ አወቁአለሁ። ያጀበኝ መልአክ ከያሑዋሕ ዙፋን ረጅም ርቀት ሲቀረን ቆመ። እየተካሄዱ ያሉ የድርጊቶችን ሙሉ ትዕይንት እይታ ማየት ችዬ ነበር። ዮሐንስ በራእዩ ያየውን ያንኑ ሁኔታ አየሁ - በራእይ እንዲህ ያብራራውን:

*አየሁም፥ በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም አእላፋት ጊዜ አእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር፥*

(ራእይ 5፥11)

ኦህ፥ የምድር ሰዎች ሆይ፥ ያሑዋሕ ለእኛ ለምናፈቅረው ጠብቆ ያስቀመጠውን ማገናዘብ ብቻ ብትችሉ!

ከፊቴ ያለውን ሁኔታ በደስታ ስሜት በትኩረት ስመለከት፥ የበለጠ ድንቅ የሆነ አንድ ነገር ሆነ። ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በላይ ከፍ ባለ ድምፅ ሺሆችና ሺሆች ድምፆች ያሑዋሕን እያወደሱ መስማት ቻልሁ። ከዛ - የድንቆች ሁሉ ድንቅ - ሁል ጊዜ ለማየት ስመኘው የነበረውን የያሑዋሕ ዙፋን እንዳይ መልአኩ ፈቀደልኝ።

# የከበረው ታላቁ የያሑዋሕ ዙፋን

**የያሑዋሕ ዙፋን** "ረጅምና ከፍ ያለ" ነበረ (ኢሳይያስ 6፥1)። የሕይወት ወንዝ ከዙፋኑ በታች በመውጣት በውበቱና በጥራቱ ይፈስሳል። **የያሑዋሕ ክብር** ዙፋኑን ሸፍኖታል(ጋልሎታል)። መብረቅ፣ ነጎድጓድና ድምፆች በዙፋኑ ዙሪያ ሁሉ የነበሩ ይመስላል። ዮሐንስ፥ ስለ መንግሥተ ሰማይ የነበረውን ራእይ ሲያብራራ፥ እንዲህ አለ:-

*ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፥ እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።*

(ራእይ 4፥5)

"*በመልኩም መረግድን የመሰለ*" ቀስተ ደመና ከዙፋኑ በላይና በዙፋኑ ዙሪያ በቀስተደመና ቅርፅ ሆኖ አየሁ (ራእይ 4፥3)።

በጣም ደማቅ፣ የከበሩት የቀስተደመናው ቀለሞች ከብርሃን ጋር ተቀላቅለው በጣም ደማቅ/አንጸባራቂ ማራኪ ቀለሞችን እያፈሩ ነበር።

በምድር(በመሬት) ላይ ካየሁት ከማንኛውም ነገር ጋር አይገናኝም/አይመሳሰልም ነበር። በደማቁ የሚያበሩ የተለያዩ የብርሃን ቀለሞች ክብርና ኃይል ያመለክታሉ። ብሩህ የውበት ነበልባሎች ከዙፋኑ በመብለጭለጭ ያበራሉ። የክብር አመልማሎዎች(ጮራዎች) ከዙፋኑ ይፈነጠቃሉ። የሰማይ አብዛኛው ግልጽ ይመስላል፥ ከዙፋኑም የሚመጡት እነዚያ ዝነኞቹ አመልማሎዎች በሁሉም የገነት ቦታ(ክፍል) ውስጥ በተንጸባረቀው ብርሃን ተሞልተዋል!

በዚህ ሰማያዊ ሰፊ ክብ ቦታ (heavenly arena) ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየሁ አላውቅም፥ ነገር ግን እኔ እጅግ በመደነቅ ተሞልቼ ነበረ። ወደ መንግሥተ ሰማይ ስለሄዱት ስለ አእላፍ (ሺሆች) እና ገና ስለሚመጡት ስለ ብዙ አእላፍ አሰብሁ። ስለ ያሑዋሕ ቅድስና፣ የኃያል ግርማውን ንጽህና፣ የቃሉን ፍጹምነትም አሰብሁ። ድምፄን ከፍ አድርጌ:- "ኦህ፥ ያሑዋሕ! የአንተን ክብር እና የአንተን ግርማ ሞገስ እና የአንተን ኃይል መመልከት (to behold) እንዴት ድንቅ ነው!" በማለት ጮኽኩ።

እንደ በፊቱ፥ የጌታ መልአክ:- "ከእኔ ጋር ነይ። ላሳይሽ የምፈልጋቸው ሌሎች ብዙ ነገሮች በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ አሉ።" አለኝ።

## የመዛግብት ቤት

ጥንቁቅ መዝገቦች ተጠብቀው ያሉበትን የመዝገቦች ቤት ለማየት በጣም ተደንቄ ነበር። ***ያሑዋሕ*** (**እግዚአብሔር**) **እርሱ** ከፍ የሚልበትንና የሚወደስበትን በምድር ላይ የእያንዳንዱን ቤተክርስቲያን አገልግሎት መዝገቦች እና በቤት ውስጥ ያለን እያንዳንዱን አገልግሎት የሚጠብቁ መላእክቶች እንዳሉት መልአኩ ተናገረ።

**እግዚአብሔር** ከፈቃዱ ውጪ በሆኑ ላይም ደግሞ መዝገቦችን ይጠብቃል። የ***ያሑዋሕ*** መላእክት በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ሰዎች በምን ዓይነት ጠባይ(ሁኔታ) ይሰጣሉ ከሚለው መዝገብ ጋር ጎን ለጎን፥ የሚሰጡትን የገንዘብ መዝገቦች እንዴት እንደሚጠብቁ እርሱ አሳየኝ። ገንዘብ ስላላቸው ሰዎች ነገር ግን ለ**ጌታ** ሥራ መስጠት ስለማይፈልጉ ሰዎች እርሱ ነገረኝ።

**ኢየሱስ** ወደ **ጌታ** መቅደስ ሄዶ ሳለ መብዓውንና መዝገቡን እንዴት በጥንቃቄ እንደተመለከተ(እንደተከታተለ) አስታወስሁ:

*ኢየሱስም በመዝገብ አንጻር ተቀምጦ ሕዝቡ በመዝገብ ውስጥ ገንዘብ እንዴት እንዲጥሉ ያይ ነበር፤ ብዙ ባለ ጠጎችም ብዙ ይጥሉ ነበር፤*

*አንዲትም ድሀ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች።*

*ደቀ መዛሙርቱንም ጠርቶ። እውነት እላችኋለሁ፥ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድሀ መበለት አብልጣ ጣለች፤*

*ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና፥ ይህች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አላቸው።*

(ማርቆስ 12፥41-44)

የመዝገብ መጽሐፎች ተጠብቀው ያሉበትን ክፍል ጨምሮ፥ ብዙ ነገሮች ተገልጠውልኝ ሳሉ፥ እነዚህን ነገሮች መመዝገብ እንዳለብኝ ተነግሮኝ እንደነበረ መልአኩ አስታወሰኝ። በድንግዝግዝ ብቻ አይ ስለነበር፥ ለእኔ ምስጢሮች የነበሩ ብዙ ነገሮች እንደነበሩ እርሱ ተናገረ (1ኛ ቆሮንቶስ 13፥12)። መልአኩ ግን ስላየኋቸው ነገሮች በምድር(በመሬት) ላይ ላሉ ሰዎች ልናገር እንደሆነ በጣም በግልጽ አሳሰበ።

የሰማይ ሌላ ቦታ ስንደርስ፥ በጣም ረጅም በሆነ ኮሪዶር ወደ ታች ተመለከትሁ። ግድግዳዎቹ ከፍ ያሉ(ረጅም) ነበሩ፥ ከፕላቲነምም የተሠሩ ይመስሉ ነበር። ከፍ ያሉ የ***ያሑዋሕ*** ምስጋናዎች/ውዳሴዎች ያለማቋረጥ ሲያስተጋቡ (ሲደውሉ) እሰማ ነበር። ከግድግዳዎቹ በሚንፀባረቀው የብርሃንና የክብር ከፍተኛ ድምቀት ተገርሜ ነበር። እንቆቅልሽ ስለሆነብኝ (ስላልተረዳሁኝ)፥ “ይህ ምንድን ነው?” በማለት ጠየቅሁ። ግድግዳዎቹ በማይሎች ያህል ረጅም መሰሉ፤ የእነርሱን ፍጻሜ(መጨረሻ) ማየት አልቻልሁም።

## የ*ያሑዋሕ* ግምጃ ቤት

እነዚህን ነገሮች እያሳየኝ የነበረው መልአክ እንዲህ አለ፡- “የዚህ ግድግዳ አናት ላይ ተመልከቺ።” በግድግዳው አናት ላይ ግምጃቤት የሚለው ቃል ተቀርፆአል። “እነዚህ ክፍሎች ምንድን ናቸው?” ብዬ ስጠይቅ፥ እነዚህ ክፍሎች ለ***ያሑዋሕ*** ሕዝብ የተቀመጡ በረከቶችን የያዙ እንደሆኑ መልአኩ ነገረኝ!

*መንግሥተ ሰማይ ፍጹም ንፅህና ነው፥ **ያሑዋሕ**ም በምድር ያሉ የ**እርሱ**ን ቅዱሳን ማንጻት ይፈልጋል - የ**እርሱ** ቅዱሳን የሰማይን ሁኔታ(atmosphere) እንዲደሰቱበት።*

*መንግሥተ ሰማይ የደስታ ሙላት ነው፥ **ያሑዋሕ**ም በምድር ላሉት የ**እርሱ** ቅዱሳን ደስታ ለመስጠት ይሻል። ሰማይ ዘላለማዊ ነጻነት ነው፥ **ያሑዋሕ**ም የ**እርሱ** ሕዝብ በምድር ላይ ሳሉ ነጻነት እንዲኖራቸው ሽቶአል። ሰማይ ፍጹም ሙሉነት ነው፥ **ያሑዋሕ**ም እዚህ በምድር(በመሬት) ላይ የ**እርሱ**ን ሕዝብ ለመፈወስ ፈልጎአል። ሰማይ ሙሉ ደኅንነት ነው፥ **ያሑዋሕ**ም የ**እርሱ** ሕዝብ እዚህ በምድር(በመሬት) ላይ ልበሙሉነት(confident) እና ደኅንነት እንዲሰማቸው ፈልጎአል። ሰማይ የእቅድ መሳኪያ( fruition፥ ፍሬ ማፍሪያ) እና ስኬት( fulfillment) ነው፥ **ያሑዋሕ**ም የ**እርሱ** ሕዝብ በምድር ላይ የተሳካላቸው እንዲሆኑ ይሻል።*

ኢየሱስ የያሑዋሕ "ፈቃድ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" ብለን እንድንጸልይ ሲያስተምረን (ማቴዎስ 6፥10)፥ የሰማይ ቅምሻ እዚህ በምድር ላይ እኛ እንዲኖረን ያሑዋሕ እንደሚፈልግ እርሱ ገለጸው!

ቅዱሳን፥ ጌታ የበረከቶች ግምጃቤቶች ለእናንተ ብቻ አለው። እዚህ በምድር ላይ ሳላችሁ እናንተ እነርሱን አሁን እስክትጠይቁና እስክትቀበሏቸው እነርሱ በሰማይ እናንተን እየጠበቁ ነው። ያሑዋሕ እናንተን ለማዳን ይፈልጋል። እርሱ እናንተን ነጻ ለማውጣት ይፈልጋል። እርሱ እናንተን ሊፈውሳችሁ ይፈልጋል። እርሱ "አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም" እንድታውቁ ይፈልጋል (ፊልጵስዩስ 4፥7)። እርሱ ዘለቄታዊ "በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሤት" እንድትለማመዱ ይፈልጋል (1ኛ ጴጥሮስ 1፥8)።

## ፈዋሹ ኢየሱስ (ፈዋሹ ያሕሹዋ)

"የአምላክሽን ክብር ተመልከቺ" በማለት መልአኩ አወጀ። እርሱ ሲሰወር፥ ኢየሱስ (ያሕሹዋ) ከአጠገቤ ቆመ።

ኢየሱስን ተመለከትሁ። ከዚህ በፊት ይሆናል ብዬ ከተገነዘብሁት በላይ አሁን እርሱ ረጅም መስሎአል። እርሱ የለበሰው እጅግ የሚያበራው ድንቅ ግሩም ልብስ በማሸብረቅና ደስ በማሰኘት በእርሱ ላይ ሆኖ አጊጦአል። ነጠላ ጫማዎች የእርሱን ጠባሳ እግሮች (በመስቀል ላይ በምስማር ሲቸነከር የሆነውን) አሞግሰዋል(አሳምረዋል)፥ የእርሱ ፊት እና ጸጉርም የከበሩና ውቦች ነበሩ።

እርሱን አትኩሬ ስመለከት፥ "ኢየሱስ፥ እነዚህ ክፍሎች ምንድን ናቸው?" በማለት ጠየቅሁ።

ጌታ ለኔ አልተናገረም፥ ነገር ግን እርሱ እጁን አወጣና ወደ ግድግዳው አንቀሳቀሰው። በዛ ቅጽበት፥ በግድግዳው ትልቅ ክፍተት ታየ። በክፍተቱ ጠርዞች ዙሪያ ሁሉ ክብር እና ኃይል እና ብርሃን አየሁ። እንደ ማንኛውም ሌላ ዕቃ፥ ይህም ለያሑዋሕ ክብር የሚሰጥ ይመስላል። "ኦህ፥ ጌታ ሆይ፥ ይህ ምንድን ነው?" ብዬ ጮኽኩ።

እርሱም እንዲህ አለኝ፦ "*ልጅ ሆይ፥ እነዚህ ለሕዝቤ ናቸው። እነርሱ(ዕቃዎቹ) በምድር (በመሬት) ላይ ላሉ ኃጢአተኞች ናቸው፥ እነርሱ (በምድር ላይ ያሉት ኃጢአተኞች) ካመኑ ብቻ። እነርሱን(በምድር ላይ ያሉትን ኃጢአተኞች) ሙሉ ለማድረግ እኔ ሞትሁ።*"

ዓይኖቹ ውስጥ ስመለከት፥ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ ሙሉ እንድንሆን እርሱ እንደሞተ ሰዎች እንዲያምኑ እርሱ እንደሚፈልግ አወቅሁ። እርሱ እንዲህ አለ፦ "*በምድር ላይ ላሉ ሰዎች ፈውሶች እየጠበቁ ናቸው። በምድር ላይ የተዓምራትና የፈውሶች ናዳ የሚሆንበት ቀን ይመጣል።*"

በመቀጠል እንዲህ አለ፦ "*ልጄ፥ ማየት እስከምትችዪው ድረስ፥ እነዚህ አቅራቢ ሕንጻዎች፥ ወይም ግምጃቤቶች ናቸው። እዚህ የተቀመጡት በረከቶች በምድር ላይ ያሉትን የአማኞችን እምነት እየተጠባበቁ ነው። እነርሱ ማድረግ ያለባቸው ሁሉ ማመን እና መቀበል ነው - እኔ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆንሁ ማመን እና እኔ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደምችል ማመን፥ እና የእኔን ስጦታዎች መቀበል።*"

"*አንቺ ወደ ምድር ተመልሰሽ ስትሄጂ፥*" እርሱ በግልፅ አሳሰበ፥ "*ፈውሱን የምታደርጊው አንቺ እንዳልሆንሽ አስታውሺ። የሚፈውስ ዕቃው/ሰውዬው/ሴትየዋ አይደለም፤ የምፈውስ እኔ ነኝ። ብቻ ቃሌን ተናገሩና ጸልዩ፥ እኔም ፈውሱን አደርጋለሁ። እኔ ላደርገው እንደምችል እመኑ።*"

"ክብር ለያሑዋሕ! ሃሌ ሉያ! አመሰግንሃለሁ ኢየሱስ!" ብዬ ጮኽኩ። ኢየሱስ እጁን ወደታች አደረገ፥ በግድግዳው የነበረውም ክፍተት ተዘጋ።

ከዚያ እኔና መልአኩ እጅግ በፈጣን ፍጥነት ወደ ሌላ ቦታ ተጓዝን። እዚህም፥ በያሑዋሕ ሕዝብ የሚደረገውን ሙዚቃውንና የሚጮኹትን ክብሮች መስማት ችዬአለሁ። መልአኩ እንዲህ አለ፦ "ልጅ ሆይ፥ ብዙ ነገሮችን እንዳሳይሽ በጌታ ታዝዤአለሁ። ስለእነዚህ ነገሮች ሕዝቡን(ለሰዎች) ንገሪያቸው።"

-------------------------------------------------------

# በፊት፣ አሁን፣ እና በኋላ

በራእዬ በዚህ ጊዜ ላይ፥ የጌታ መልአክ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ለማወቅ ሽቼአቸው የነበሩ ነገሮችን ይገልጽልኝ ጀመረ። እርሱ ስለ ታላቅ ምስጢር ይነግረኝ ጀመር።

እርሱ እንዲህ አለ:- "**ያሑዋሕ** ተናግሮአል፥ እኔም በፊት፣ አሁን፣ እና በኋላን ላሳይሽ ነው። ላሳይሽ ያልኳቸው ነገሮች ታላቅ መደነቅን ይሰጡሻል። አንድ ሰው ዳግም ሲወለድ ምን እንደሚሆን ልገልፅልሽ ነው። በመዝገብ ክፍሎቹ ውስጥ የአንድ ሰው ኃጢአቶች እንዴት በበጉ ደም ታጥበው እንደሚነጹ አሳይሻለሁ።"

"ዳግም የተወለደ አንድ ሰው በምድር (በመሬት) ላይ ሲሞትና የእርሱ ነፍስ ወደ መንግሥተ ሰማይ ስትመጣ ምን እንደሚሆን ላሳይሽ ነው። ነይ እና የ**አምላክ**ሽን ክብር እዪ።"

እጅግ በከፍተኛ የፍጥነት መጠን ከሰማይ ተጓዝን፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ተመልሰን በምድር (በመሬት) ላይ ነበርን። መሬትን እንደ በራእይ ማየት ችዬ ነበረ፥ መልአኩም:- "ተመልከቺና ተከታተዪ።" አለኝ።

ራእዩ በፊቴ እንዲያልፍ መልአኩ ሲፈቅድ፥ በአገሩ ውስጥ አንድ ውብ ትንሽዬ ቤተክርስቲያን አየሁ። በስነ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ቤተ ክርስቲያኗ የቱ ጋር እንደነበረች አሁን አላውቅም፥ ነገር ግን በአገሩ ውስጥ ወጣ ያለች የገጠር ቤተክርስቲያን ናት።

በ**ያሑዋሕ** መልአክ እርዳታ፥ ወደ ሕንጻው ውስጥ እንድመለከት ተፈቅዶልኝ ነበረ። ወደ ሰላሳ የሚጠጉ ሰዎች መደገፊያ ባላቸው አግዳሚ ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ማየት ችዬ ነበር። በመሠዊያው ያለው ፓስተር (እረኛ) በዚህ ምንባብ ላይ እየሰበከ ነበር:

*እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፥*

*ቀርቦም ሳለ ጥሩት፤*

*ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው፤*

*ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፥*

*ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ።*

(ኢሳይያስ 55፥6-7)

ይህን ሁኔታ በትኩረት ስመለከት፥ አንድ ኃያል መልአክ በቤተክርስቲያኑ ላይ ቆሞ አየሁ። ከአጠገቤ የነበረው አስጎብኚ መልአክ እንዲህ አለ:- "በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ላይ አንድ ረጅም መልአክ ተመድቦአል። ይህ መልአክ በሁሉም የዚያ ቤተክርስቲያን መልአኮች ላይ ሃላፊ ነው።"

## መላእክት በቤተ ክርስቲያን

ሁለት መላእክት መጻሕፍት ይዘው ከቤተክርስቲያኑ በር ውጭ ቆሙ። ሰዎች ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሲገቡና ሲወጡ ማየት ችዬአለሁ።

ከዛ አስጎብኚ መልአኬ በእጁ ምልክት ሰጠኝ፥ ጣሪያው ወደኋላ የተጠቀለለ መሰለ፥ እኔም የቤተ ክርስቲያኑን ውስጥ ማየት ቻልሁ።

በመሠዊያው ላይ ሁለት መላእክት በፓስተሩ ሁለቱም ጎኖች በኩል ቆሙ። ከእነዚያ ሁለት መላእክት ባሻገር ሌሎች ሁለት መላእክት ነበሩ። ይህ ደግሞ በመሠዊያው ዙሪያ አራት መላእክት እንደሆኑ ያደርጋል።

ሁለት መላእክት ከምዕመናኑ ጀርባ በቤተ ክርስቲያኑ ኋላ ላይ ቆሙ። ሁለት ተጨማሪ መላእክት በአጋማሹ መተላለፊያ ቆሙ፥ ከመሠዊያውም አቅራቢያ ሌሎች ተጨማሪ ሁለት መላእክት ቆሙ። ስለዚህ ጥቂት መላእክት ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ነበሩ። ከእነርሱም በርከት ያሉት በእጃቸው ጥቅልሎችና እስክሪፕቶዎች ይዘዋል። መልአኩ፡- "ምን እንደሆነ አሳይሻለሁ።" አለኝ።

ፓስተሩ(እረኛው) መናገር ጀመረ፥ አስተናጋጆቹም መብዓውን መቀበል ጀመሩ። መብዓው እየተሠበሠበ ሳለ፥ ሰዎቹ ሲሰጡ የሰዎቹን ሁኔታዎች(attitudes፥አኳኋኖች) መላእክቱ መዘገቡ። መላእክቱ የሰጪዎቹን አሳቦች መዘገቡ - ለ**ጌታ** ሥራ መስጠታቸው የቆጫቸው (ቅር ያሰኛቸው፥ ፈቃደኛ ባለመሆን) መሆኑ፥ ወይም መብዓውን መስጠታቸውን ከተደሰቱበት (ደስ ከተሰኙበት) እና እንደ አምልኮ ሥራ ከተመለከቱት። መላእክቱ ሁሉንም በመመዝገቢያ መጽሐፎቻቸው ውስጥ ጻፉት።

ከዚያ ከመሠዊያው ፊት ያሉት ሁለቱ ትላልቅ መላእክት ወደ ሌሎቹ መላእክት ራሶቻቸውን ወደታችና ወደላይ በማድረግ ነቅነቅ አደረጉ።

የመላእክቶቹ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ላሉት ሰዎች አይታዩም ነበር፥ እኔ ግን ሁሉንም በግልፅ ማየት ችዬ ነበር። ከዚያ አስጎብኚዬ እንዲህ አለኝ፡- "ሌላ ነገር ላሳይሽ እፈልጋለሁ። በቅርበት ተመልከቺ፥ አንቺም ትባረኪያለሽ።"

ወዲያውኑ፥ ተንቀሳቅሼ ከፓስተሩ ኋላ የሆንሁ መሰለ። እርሱ በስድስተኛው ቁጥር ላይ "እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፥ ቀርቦም ሳለ ጥሩት፤" እየሰበከ ሳለ - የሰማያዊ ፍጡራን ሠራዊት ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ማየት ችዬ ነበር። አገልግሎቱ እየተከናወነ ባለበት በሁሉም ጊዜ፥ መላእክቱ እየተደሰቱ ነበረ። አገልጋዩ ያንን መልእክት ሲሰብክ ተቀብቶ ነበረ። ከመላእክቶቹ አንዱ እሳት የሚመስል ነገር የአገልጋዩ ራስ ላይ እያፈሰሰ ነበረ። የ**ያሑዋሕ** ክብሮች ከሰባኪው አፍ እየመጣ ነበረ።

በቤተክርስቲያኑ በስተጀርባ፥ አንድ በር ተከፈተ፥ በጣም የሰከረ አንድ ሰው እየተንገዳገደ ገባ። ወደ አጋማሹ መተላለፊያ እንዲህ እያለ መጣ፡- "ሰባኪ፥ አንተ እያናገርከው ያለው እኔ ነኝ። **ጌታ** ያስፈልገኛል። መዳን ያስፈልገኛል። እኔ የአልኮል ሱሰኛ ነኝ።" ሰውዬው በፊተኛው መሠዊያ ላይ በጉልበቶቹ ወደቀና ወደ ያሑዋሕ መጮኽ ጀመረ።

ከዲያቆናቱ ሁለቱ ሊያገለግሉት ወደ መሠዊያው ሄዱ። ክንዶቻቸውን በሰውዬው ዙሪያ አድርገው፡- "ከ**ያሑዋሕ** ጋር ጉዳይ ማለትህ ነው? መዳን የእውን ትፈልጋለህ?" ብለው ጠየቁት።

ሰውዬውም፡- "አዎን፥ መዳን እፈልጋለሁ።" አለ።

"እኔ የአልኮል መጠጥ ሱሰኛ ነኝ። ነጻ መውጣት ያስፈልገኛል።"

## አንድ ነፍስ ዳነ

ተጨማሪ ሁለት መላእክት ወዲያውኑ መጡ። እነርሱ በእጃቸው ጥቅልሎች ነበራቸው፥ እነርሱም ሰውዬው ያለውን መጻፍ ጀመሩ። ከዚያ ዲያቆኖቹ በድኅነት ሂደት ውስጥ የመሩት ጀመር። ይህ ሰው በኃጢአት እንደተሞላ አየሁ።

ነገር ግን፥ ዲያቆኖቹ ከእርሱ ጋር ሲጸልዩ፥ ከመላእክቱ አንዱ ልቡን ነካው፥ እንደ ዝናብ ደመና የጨለመ ጭስም ከደረቱ ውስጥ በፍጥነት ወጣ።

ይህን ሳይ፥ ከልብ ስለሚወጡ ክፉ(ግም፥ እርጉም፥ መጥፎ) ኃጢአቶች የሚያወሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስታወስሁ:

*መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል፥ ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ክፉ ነገርን ያወጣል።*

(ማቴዎስ 12፥35)

*ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይመነጫል፤ ሰውንም የሚያረክሰው ይህ ነው፤ ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ማመንዘር፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና ስም ማጉደፍ ከልብ ይመነጫልና።*

(ማቴዎስ 15፥18-19 NIV)

ሰውዬው እጆቹን ወደላይ ከፍ አድርጎ ወደ **ያሑዋሕ** መጸለይ ሲጀምር፥ በዙሪያው ሁሉ ተጠምጥመው የነበሩ ሰፊ፣ ጥቁር ማሰሪያዎች አየሁ። እርሱ ለሁሉም የኃጢአት ዓይነቶች እስራት ውስጥ ነበር፥ በተለይ ግን ለአልኮል(ለሚያሰክር መጠጥ) ሱስና ለስካር። አንድ ዲያቆን ለእርሱ እንዲህ አለው፦ "**ያሑዋሕ** ይቅር ሊልህ እንዲችል እና አንተ **በበጉ ደም** መታጠብ እንድትችል፥ እነዚህን ኃጢአቶች ለ**ያሑዋሕ** መናዘዝ አለብህ።"

እርሱ ኃጢአቶቹን መናዘዝ ሲጀምር፥ አንድ መልአክ ነካው። ከመልአኩ እጆች እሳት ሲወጣ ማየት ችዬአለሁ። እስራቶቹ ከሰውዬው መሰባበርና በፍጥነት ተበጣጥሰው መውደቅ ጀመሩ።

ይህ ለሰውዬው እጅግ ታላቅ ነጻነት ሰጠው። እርሱም እጆቹን አነሣና **ጌታን** አመሰገነ። እርሱ ቆመ፥ የ**ያሑዋሕ** ክብር ወደታች በእርሱ ላይ ሲመጣ አየሁም። **ጌታ** ሰውዬውን ረጋ እንዳደረገው አውቃለሁ፥ ምክንያቱም እርሱ ለ**ጌታ** ምስጋናዎችን መጮኽ ጀመረ።

ከዚያ ሁለቱ ኀያል መላእክት እርስ በእርሳቸው ተመለካከቱና ራሳቸውን ወደታችና ወደላይ ነቀነቁ። እኛ ወደነበርንበት ተመልሰው በአየር ውስጥ መጡና፥ "ነይ እና የ**ያሑዋሕ**ን ክብር እዪ።" አሉ።

## በድጋሜ በመዛግብቱ ቤት

ከሁለቱ መላእክት ጋር በመሆን ተመልሰን ወደ ሰማይ በጣም በፍጥነት ተጓዝን። በደጁ ውስጥ ከገባን በኋላ፥ ከወርቅ የተሠራ መሆኑ በሚታይ በአንድ ውብ መንገድ ላይ ወደታች ተጓዝን። እጅግ ውብ(ማራኪ) ወደ ሆነ ክፍል በፍጥነት ተጓጉዘን ነበር።

መልአኩ፦ "ነዪና እዚህ ምን እንደምናደርግ እዪ።" አለ። ወደ ሌሎች ብዙ ክፍሎች የተመራንበት ረጅሙ ኮሪዶር ገብተንበት ከነበረው ኮሪዶር ጋር ተመሳሳይ ነበረ። "በሰማይ ውስጥ ብዙ እንደነዚህ ክፍሎች አሉ። እነዚህ የመዝገብ ክፍሎች ይባላሉ። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ምን እንደሚካሄድ ታያለሽ።" አለ መልአኩ።

መልአኩ፦ "በምድር ላይ አሁን ክርስቲያን ሆኖ የተለወጠ የአንድ ሰውን ስም ወደያዘ ክፍል ልንሄድ ነው።"

በክፍሉ ውስጥ መላእክት ከምድር በፍጥነት ሄደው በተጠቀለለ ወረቀት (scroll) ላይ የተጻፈውን ሪፖርት ለሌላ መልአክ ሲሰጡ አየሁ።

በርከት ያሉ መሰላሎች የባለአራት ማዕዘኑ ክፍል ግድግዳዎችን ተደግፈው ተዘርግተው ነበር። ሼልፎች ግድግዳዎቹን ሸፍነዋቸዋል፥ ሁሉም መጽሐፎችም ሼልፎቹ ላይ ነበሩ። ሁኔታው በምድር ላይ ያለን ቤተመጻሕፍ(ላይብረሪ) አስታወሰኝ።

ሌሎች መላእክት ለያሑዋሕ እየዘመሩና ያሑዋሕን እያወደሱ ከትልቅ ዴስክ ፊት ለፊት በመስመር/ተሰልፈው ቆመዋል። ዴስኩ ርዝመቱ ስምንት ፊት ስፋቱም አራት ፊት ያኽል ነበረ። በጠጣር ወርቅ የተሸፈነ፥ እኩል ርዝመት ያለው ባለአራት ማዕዘን ክፍተት (A square cutout) በዴስኩ መሐል ነበረ። በጣም ውብ ነበረ። ቅጠሎችና ፍሬዎች ተቀርፀውበት ነበር።

አንድ ሰው በፍጹም አስቦት የማያውቀው እጅግ በጣም ውብ ዴስክ ነበረ። በምድር(በመሬት) ላይ እንደሱ አይነት አንዳች ነገር ወይም እሱን የሚመስል ፎቶ በፍጹም አይቼ አላውቅም። በክፍሉ ውስጥ ባለው በ**ያሑዋሕ** ክብር እና አስደናቂ ውበት(ኃይለ ግርማ) ተማረክሁ(ተሳብሁ)።

መላእክት በመሰላሎቹ ላይ ወደላይና ወደታች ይወጡና ይወርዱ ነበር። እነርሱ ያለማቋረጥ መጽሐፎችን ከሼልፎች ላይ ያወርዱ እና ወደ ትክክለኛው ቦታቸው ይመልሱ ነበር። በርከት ያሉ መላእክት ከመሬት ሌሎች ክፍሎች ሪፖርቶችን ይዘው በቅርበት ቆመው ነበር።

ግድግዳው ላይ የነበሩት አንዳንዶቹ መጻሕፍት የተለያዩ ቀለሞች ነበሯቸው። ከሼልፉ ያወረዱትን መጽሐፍ ይዘው በቤተክርስቲያኑ ከነበሩት መላእክት ሁለቱን ተሰልፈው ቆመው አየኋቸው። መጽሐፉ በምድር ላይ አሁን ዳግም ሲወለድ ያየሁትን የዛኑ ሰውዬ መዝገብ ይዟል።

ከእኔ ጋር የነበረው መልአክ፡- “በቤተክርስቲያኑ አገልግሎት የነበሩትን ሁለቱን መላእክት አየሻቸው?” አለ።

“አዎ።”

“በእጃቸው ያለውን መጽሐፍ አየሽ?”

“አዎ።”

“ያ መጽሐፈ እጅግ በቅርቡ የዳነው ሰውዬ መዝገብ መጽሐፍ ነው። እነርሱ ከሼልፎቹ ፈልገው አመጡት። አሁን እነርሱ ሃላፊ ወደሆነው መልአክ መሄድ አለባቸው።”

በእያንዳንዱ የመዝገብ ክፍል ውስጥ ሃላፊ የሆነ አንድ መልአክ አለ። እዛ ክፍል የሚገባም ወይም ከዛ ክፍል የሚወጣ ማንኛውም ነገር በዛ መልአክ በኩል ማለፍ አለበት። ሁሉም የሚደረገው ለ**ያሑዋሕ** ክብር በሥርዓት ነው።

እነዚህ ነገሮች ሲሆኑ ማየቴ አስገርሞኝ ነበር። ሃላፊ የነበረው መልአክ ከእኔ የማብራራት አቅም በላይ የሆነ አንጸባራቂ የራስ ልብስ አድርጎ ነበር። እርሱ ወርቃማ ጸጉር እና ብዙ ወርቅ በላዩ ላይ ያለበት የሚያንጸባርቅ ነጭ ልብስ(ቀሚስ) ነበረው። ይህ እጹብ ድንቅ መልአክ ከአንድ ክንፉ ጫፍ እስከ ሌላኛው ክንፉ ጫፍ ድረስ አስራ ሁለት ፊት (3.66 ሜትር) የሚያህል ስፋት ነበረው። ይህ መልአክ ከዚህ በፊት በፍጹም ያላየሁት እጅግ በጣም ውቡ መልአክ ነበረ። መልአኩ የዚያ ክፍል ዋና መዝገብ ጠባቂ ነበረ።

ሃላፊ የነበረው መልአክ ተመለከተኝና ወደ አጠገቡ እንድመጣ ምልክት አሳየኝ። የ**ያሑዋሕ** ኃይል አንቀሳቀሰኝ፥ እኔም ወዲያውኑ በመልአኩ ቀኝ በኩል ቆሜ ነበር።

እርሱም፡- “በምድር ላይ አንድ ሰው ዳግም ሲወለድ ምን እንደሚሆን እንድናሳይሽ እዚህ እንድትሆኚ ተፈቅዶልሻል። አንቺ በምድር ላይ ላሉት ሰዎች ልትነግሪ ነው።” አለኝ። (ስለ ዳግም ውልደት፤ የያሑዋሕ ቃል እና ልጅ፥ የነገሥታት ንጉሥ የጌታዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እኛን ለማዳን ጊዜውም ሲደርስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ለእኛ ድነት መሥዋዕት ለመሆን ከብጽዕት ድንግል ማርያም በቤተልሔም የተወለደው፣ ፍጥረታትን ሰማይንም ምድርንም የሚታየውንም የማይታየውንም ዓለማትን ሁሉ የፈጠረው የያሑዋሕ ቃል፣ በሥጋ የተገለጠው የአብ ቃል የአብ ልጅ፣ ስለእኛ ብሎ በቀራንዮ በመስቀል ላይ የተሰቀለው፣ ከኃጢአታችን ሁሉ የሚያነጻንን ቅዱስ ደሙን ያፈሰሰው የያሑዋሕ በግ፣ ስለሰዎች ሁሉ ብሎ ደም ግባት አልባ እስኪሆን ድረስ የተገረፈው የተደበደበው የተሡቃየው የተቸነከረው የእሾኽ አክሊል የደፋው እርቃኑን የሆነው፣ የሞተው፣ በጎልጎታ የተቀበረው፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣው፣ በአርባኛውም ቀን ወደ አባቱ ያሑዋሕ አብ ያረገው፣ በኃያሉ ያሑዋሕም ቀኝ በክብር በኃይል የተቀመጠው፣ ስለእኛም የሚማልደው ጠበቃችን፣ ዳግምም በክብር በእርሱ አምላክነት ጌታነት ቤዛነት መንገድነት እውነትነት ሕይወትነት አዳኝነት መሥዋዕትነት በመስቀል ላይ ስለኛ ብሎ እንደሞተ በሦስተኛውም ቀን ከሞት እንድተነሣ ያመኑና እንደቃሉ ቃሉን እያደረጉ በአባቱ ፈቃድ በቅድስና የሚኖሩ ቅዱሳንን ወደ ክቡር ቅዱስ አባቱና ወደ ቅዱስ መንግሥቱ ለመውሰድ የሚመጣው፥ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ፣ መልካም እረኛ፣ የድኅነት ተስፋ፣ በሰውና በያሑዋሕ መሐል በከፈለው የደም መሥዋዕት የእርቅ መንገድ የሆነው ፣ ውብ አድርጎ የፈጠረን፣ ፍቅር ቅዱስ ፈጣሪያችን የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ (የናዝሬቱ ያሕሹዋ ሐማሺያክ) በምሥራቹ የተናገረውን በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥቂቶቹን ተመልከቱ፥ ዮሐንስ 3፣ ማርቆስ 16፥16፣ ሮሜ 10፥4-13፣ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2- 4)

አስገራሚነቱ ከቃላት በላይ አስደነቀኝ!

## መዛግብትን መጠበቅ

ወደ ውጭ ከፊት ለፊቴ ስመለከት፥ ከፍ ያሉት የ**ያሑዋሕ** ምስጋናዎች ዙሪያውን ሁሉ ወደ ላይ እየሄዱ ነበረ። ደወሎቹን ያላየኋቸው ቢሆንም እንኳን፥ ደወሎች ሲያቃጭሉ እሰማ ነበር። በደስታ የተሞሉ፣ የሚስቁ፣ የከበሩ፣ ደስተኛ መላእክት በእጃቸው መጻሕፍት ይዘው ኀላፊ የነበረውን መልአክ ለማናገር እየጠበቁ ቆሙ።

ስለ **ያሑዋሕ** ድንቅ ኃይል እና የከበሩ ሥራዎቹ በድጋሜ በአዲስ መልኩ **ያሑዋሕ**ን ማመስገንና በኃይል እያገነንሁ ማወደስ ጀመርሁ።

“ከዴስኩ ፊት ለፊት ያሉትን ሁለቱን መላእክት ታያቸዋለሽ?” የሚያጅበኝ መልአክ ጠየቀኝ።

“አዎ፥” ብዬ መለስሁ።

“ይህ ሰው ዳግም ሲወለድ እነርሱ ተገኝተው ነበረ።”

እርሱ ከጥቅልሉ ውስጥ አንድ መልእክት ስቦ አወጣ፤ መልእክቱ በመጽሐፉ ውስጥ እንደ ልዩ ሁኔታ ነበረ። በወረቀቱ ላይ ወይም በጥቅልሉ ላይ ምን ተጽፎ እንደነበረ ማየት አልቻልሁም። ከዛ መልአኩ ጥቅልሉን ሲያሳየኝ፥ “እዚህ ምን እንደተጻፈ ተመልከቺ፥” አለ።

መልእክቱ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ነበር ተጽፎ የነበረው፥ ውብም ነበር። የአገሩን ስም፣ የግዛቱን ስም፣ የአገሩን ስም፣ የከተማውን ስም፣ እና የከተማውን ስም አየሁ።

መልአኩ የፓስተሩን(የእረኛውን) ስም እና ምን ያህል ሰዎች ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንደነበሩ አሳየኝ። እርሱ የአገልግሎቱን ሥርዓት አሳየኝ። የተቀረጸው በጠቅላላ ተጽፎ ነበረ። በቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ውስጥ የተሳተፉትን አገልጋዮች እና የተወሰደውን መብዓ ዝርዝሮች አሳየኝ።

ድኅነቱን በምድር(በመሬት) ላይ ያየኹለት ሰውዬ ስም በወረቀት ላይ ተጽፎ ነበረ። የሰውዬን ነፍስ ለማዳን የተሰበከው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች(የወንጌል፥ የመልካም ዜና) መልእክት እና እርሱ ዳግም እስከተወለደበት ድረስ ያለው ትክክለኛው ሰዓት ትክክለኛው ሰከንድ ይህ ሁሉ እዚያ ተጽፎ ነበር። “ክብር ለያሑዋሕ!” ብዬ ጮኽሁ።

የጽሕፈቱ ማብራሪያ ሰውዬው የኃጢአተኞችን ጸሎት (the Sinner's Prayer) ወደጸለየበትና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታና አዳኝ ሲቀበል ያለበት ነጥብ ሲደርስ፥ መልአኩ ወደ ሁለቱ መልእክተኛ መልአኮች ተመለከተና፦ “ይህ ሰው በዚህ ሰዓትና በዚህ ጊዜ ዳግም ተወልዶ እንደነበረ ምስክሮች ነበራችሁ (አይታችኋል)?” ብሎ ጠየቀ።

እነርሱም፦ “አዎ፥ እኛ ምስክሮች ነበርን። እኛ እዚያ ነበርን። እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታና አዳኝ ተቀብሎአል። ይህ ሲሆን እኛ አይተናል።” አሉ።

በዚያ ቅፅበት ወደላይ የወጣው የክብሩ፣ የምስጋናዎች፣ እና የጩኸቶች ከፍተኛ ድምፅ እጅግ አስገራሚ ነበረ። የሰማይ ሁሉ ያሑዋሕን እጅግ በከፍተኛው እያወደሰ/እያመሰገነ ነበር።

ከዚያ መልአኩ በያዘው መጽሐፍ ውስጥ የሆነ ነገር ጻፈና ገጾቹን ዘጋቻው። መጽሐፉ በጣም ወፍራም ነበረ። እርሱ፦ “ከበስተኋላሽ ተመልከቺ።” አለኝ። ብዙ ሰዎች፣ የተቤዡ ቅዱሳን፥ ነጭ ልብስ ለብሰውና በደማቁ ተውበው አየሁ።

## የኢየሱስ ደም

ከሁሉ በላይ እጅግ ከፍ ያለው የልዑል ያሑዋሕ የተቤዡት ነፍሳት ይህንን መዝሙር እየዘመሩ ነበረ:

*ኦህ፥ ምንም ነገር ግን የኢየሱስ ደም ብቻ ኃጢአቶቼን አጥቦ ማራቅ ይችላል።*

*ኦህ፥ ምንም ነገር ግን የኢየሱስ ደም ብቻ ዛሬ ሙሉ ሊያደርገኝ ይችላል።*

*ኦህ፥ ምንም ነገር ግን የኢየሱስ ደም ብቻ ዛሬ ሊያነጻኝ ይችላል።*

*እኔ በበጉ ደም*

*ተቤዥቻለሁ።*

ሳስተውል፥ የሰውዬው መጽሐፍ ከሚደሰቱት ቅዱሳን ለአንዱ ተሰጠው። ከገጽ ገጽ የቀደሙት ጽሑፎች ታጠቡ (ታጥበው ተወግደው ነበር)። እነርሱ ገጾቹን አንድ በአንድ ከፍ አደረጓቸው፥ እያንዳንዱ ገጽም **በኢየሱስ ደም** እንደታጠበ ማየት ችዬ ነበር። የዚህ ሰውዬ ኃጢአቶች ምንም አልቀረም። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከኢሳይያስ ወደ እኔ መጣ:

*መተላለፍህን። ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህንም አላስብም።*

(ኢሳይያስ 43፥25)

"አህ፥ **ያሑዋሕ**፥ **ቃልሕ** አሁንም መግጠሙ እንዴት ውብ ነው። የሰው ኃጢአት **በበጉ ደም** መታጠቡ።" በማለት አሰብሁ።

ስመለከት፥ መጽሐፉ ለሌላ መልአክ ተሰጠ። ይህ ሰማያዊ ፍጡር ረጅም ውብ ጸጉር ነበረው። መልአኩ በያዘው ዝርግ ትሪ ላይ መጽሐፉ ተቀምጦ ነበር። መልአኮቹ እርስ በርሳቸው ሰላምታ ተሰጣጡ፥ የክብር ጩኸቶችም ወደ ላይ ወጡ።

እኔን ያጀበኝ መልአክ እንዲህ አለ፦ "ነይ እና የ**አምላክ**ሽን ክብር እዪ።" እኔም ከእርሱ ጋር በሰማይ ኮሪደሮች ውስጥ እጅግ በኃይለኛ ፍጥነት መጓዝ ጀመርሁ።

## የበጉ የሕይወት መጽሐፍ

በድጋሜ ከ**ያሑዋሕ** ዙራን ፊት ቆምሁ። የተወደዳችሁ ሆይ፥ ቀንደመለከቶች እየተነፉ ነበረ፥ የመለከቶች ድምፅም እየጮኸ ነበር። የክብር ደመና፣ የሺኪናሕ ክብር በዙፋኑ ዙሪያ ያለውን ክልል በሙሉ አበራው።

እዛ ብዙ ነጎድጓድና መብረቃዊ ብልጭልጭታ ነበረ። "ክብር ለ**ያሑዋሕ**! ሃሌ ሉያ!" የሚሉ የእጅግ ብዙ ሰዎችን ድምፆች መስማት ችዬ ነበር።

ይህን ኀያል ሁኔታ ተመለከትሁ። መልአኩ መጽሐፉን በ**ያሑዋሕ** መሠዊያ ላይ ሲያኖረውና ዝቅ ብሎ ሲንበረከክም አየሁ። **የያሑዋሕ ድምፅ** ከፍ ባለ ሁኔታ በአየር ውስጥ አስተጋባ፥ ሆኖም እያንዳንዱን **ቃል** ተረዳሁ። **ያሑዋሕ** ፦ "***ሌላ ነፍስ በልጄ ደም ተዋጀ። ሌላ ሰው በልጄ ደም በኩል የዘላለም ድኅነትን ተቀበለ።***" አለ።

ሁሉም የሰማይ ደወሎች እየደወሉ/እያቃጨሉ ነበረ! ሁሉም የሰማይ ሕዝብ እየጮኸ ነበረ! ጎንበስ ብዬ ሰገድሁና **ያሑዋሕ**ን ማመስገን ጀመርሁ።

**በያሑዋሕ መሠዊያ** ላይ **የበጉን** የሕይወት መጽሐፍ (ራእይ 21፥27) አየሁ፥ ከዛ ደመና ውስጥ አንድ እጅ ወጥቶ በመልአኩ የተቀመጠውን መጽሐፍ ሲከፍተው አየሁ። ከዛ የሰውዬው ስም **በበጉ የሕይወት መጽሐፍ** ውስጥ ተጻፈ። ክብር ለ**ያሑዋሕ** ይሁን! ቅዱሳን፥ የእኛም ስም ደግሞ በእርግጥ **በበጉ** የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎአል።

ይህን ኀያል ሁኔታ ስመለከት፥ የ**ያሑዋሕ** መልአክ፦ "ነይ እና የ**ያሑዋሕ**ን ክብር እዪ።" አለ። ወዲያውኑ፥ በብርሃን ፍጥነት በድጋሜ ከሰማይ ውጭ ተወሰድሁ። ከመልአኩ ጋር ስሄድ፥ ከኢሳይያስ ይህን አንቀጽ አሰብሁ፦

*በስምህም የምጠራህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እኔ እንደ ሆንሁ ታውቅ ዘንድ በጨለማ የነበረችውን መዝገብ በስውርም የተደበቀችውን ሀብት እሰጥሃለሁ።*

*ስለ ባሪያዬ ስለ ያዕቆብ፥ ስለ መረጥሁትም ስለ እስራኤል ብዬ በስምህ ጠርቼሃለሁ፤ በቅጽል ስምህ ጠራሁህ፥ አንተ ግን አላወቅኸኝም።*

(ኢሳይያስ 45፥3-4)

## የሕይወት ወንዝ

በራእዬ ቀጣይ ሁኔታ፥ የሕያው ያሑዋሕን ቅዱሳን ጌታ በሕይወት ወንዝ በኩል ሲወስዳቸው ተመለከትሁ። አህ፥ የሕይወት ወንዝ ከያሑዋሕና ከበጉ ዙፋን ይፈስሳል (ራእይ 22፥1)። ቅዱሳኑ በሕይወት ወንዝ ውስጥ ሲያልፉ:- "ክብር ለያሑዋሕ!" እያሉ ሲጮኹ መስማት ችዬ ነበር።

ማንም በፍጹም ያላየው እጅግ በጣም ነጭ፣ እጅግ በጣም ውብ/ማራኪ የሆኑ ልብሶችን የለበሱ የማይቆጠሩ (እጅግ ብዙ) የቅዱሳን ስብስብ አየሁ። ዮሐንስ ይህን እንደጻፈ አስታወስሁ:

*ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ። እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ።*

*እኔም። ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት። አለኝም። እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ።*

(ራእይ 7፥13-14)

## ከዙፋኑ ፊት

ከያሑዋሕ ዙፋን ፊት በድጋሜ ሄጄ ክቡር፣ አስደናቂ ሁኔታን እንዳይ ተፈቀደልኝ። ከያሑዋሕ ዙፋን ፊት ስቆም የመለከቶችን ድምፅ እሰማ ነበር። የተሰማኝን የመደነቅና የደስታ ሁኔታ በቃላት ለማብራራት አልቻልሁም።

ከማንኛውም ተገቢ ማብራሪያ ባሻገር በልብሶች ተውበው አስራ ሁለት መላእክት እያገለገሉ ከዙፋኑ ፊት ቆሙ። የምነግራችሁ ምርጡ በደረት ልብሳቸው ላይ፥ የተጣበቁ የከበሩ የድንጋይ ፈርጦች አሏቸው። በራሳቸው(በጭንቅላታቸው) ላይ ከከበሩ ቀለማት የተውጣጣ የሆነ ዓይነት ሰማያዊ እቃ ነበራቸው። የረጅም ልብሳቸውን(ቀሚሳቸውን) ጠርዝ ወርቅ አስውቦታል።

በያሑዋሕ ፊት ለመቆም ቅዱሳኑ አንድ በአንድ ሲመጡ፥ የመለከቶች ጩኸት አስታወቀ። የማይገመት የቅዱሳን፣ የመላእክት፣ እና የሰማያዊ ፍጡራን ቁጥር እጅግ ሰፊ(ግዙፍ) ስብስብ ሠራ። ሁሉም ያሑዋሕን እያከበሩ (እያወደሱና እያመለኩ) ነበረ።

## የተቤዡት ሰዎች

በዘመናት ሁሉ የተቤዡት የከበሩና ውቦች ነበሩ። እነርሱ እውን ሰዎች ነበሩ - የጭስ ትንፋሾች ወይም በህዋ/አየር ላይ የሚንሳፈፉ ደመናዎች አልነበሩም/አይደሉም።

ሁሉም ቦታ ተመለከትሁ፥ የያሑዋሕ መላእክት ያሑዋሕን ያለማቋረጥ የእርሱን እጅግ አስደናቂ ውበት/ኀያል ግርማ ሲያወድሱ ተመለከትሁ።

ከዙፋኑ ፊት ቆሜ፥ አንድ ታላቅ ድምፅ እንዲህ ሲል ሰማሁ:-

*እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤*

(ራእይ 21፥3)

በመብረቅ ብልጭልጭታ፣ በነጎድጓድ፣ እና በድምፆች የተሞላ የክብር ደመና አየሁ። ስመለከት፥ የያሑዋሕ እጅ ከደመናው ወጥቶ የቅዱሳንን እንባዎች ከዓይኖቻቸው ላይ ማበስ ሲጀምር አየሁ። ቃሉ "ያሑዋሕ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል" ይላል። (ራእይ 21፥4)

ያሑዋሕ:-

*ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ...እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ።* ሲል ሰማሁ። (ራእይ 21፥4-5)

ያሑዋሕ ለተሰበሰቡት ቅዱሳን እንዲህ አለ:- "***ስማችሁ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ አያለሁ። ወደ ጌታ ደስታ እንኳን ደህና መጣችሁ።***" በድጋሜ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወደ አእምሮዬ መጣ

*መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።*

(ማቴዎስ 25፥21)

በዛ ቃል ጌታ እጅግ ውብ/አስደናቂ የወርቅ ዘውዶችን የእርሱ በሆኑት የሁሉም ንጹሐን ራሶች ላይ አኖረ።

የያሑዋሕ በረከቶች ለሁሉም የተቤዡት መፍሰስ እንደሚቀጥሉ አውቄአለሁ። እነርሱ(የያሑዋሕ በረከቶች) በፍጹም እንደማያልቁ አውቄአለሁ!

---

# የመንግሥተ ሰማይ ግምጃ ቤቶች

እርሱ እንዳደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ (ያሕሹዋ ሐማሺያክ) መንግሥተ ሰማይን የገለጸልኝ ማደላደያ ሊሰጠኝ ነው ብዬ አምናለሁ። እኔ በብዙ ወደ ሲኦል ጉብኝቶች ውስጥ እንደነበርሁ፥ እና ሲኦል እጅግ አስከፊ መሆኑን እንደተለማመድሁ/እንዳወቅሁ እርሱ ስለሚያውቅ መንግሥተ ሰማይን የማየት በረከት ሰጠኝ።

ወደ መንግሥተ ሰማይ ከሆኑት ጉብኝቶቼ በአንዱ፥ የያሑዋሕን ግምጃቤቶች እንድመለከት ተደርጎ ነበር። የጌታ መልአክ እንዲህ አለኝ:- "ነይ እና የአምላክሽን ክብር እዩ።"

መልአኩ በጣም ውብ እና ረጅም ነበረ። ባለ ቀስተደመና-ቀለም ክንፎቹ እንደ ትሪያንግሎች(ባለ ሦስት ጎኖች) ተቀርጸዋል። ያሑዋሕ ትእዛዛት እንደሰጠው፥ እና የመንግሥተ ሰማይን አንዳንድ ክፍሎች ሊያሳየኝ እንደሆነ ነገረኝ።

ወደላይ ወደ ከፍታ በህዋ ውስጥ መሄድ ጀመርን በድጋሜም ወደሰማይ በሚወስደው መግቢያ ውስጥ ሄድን። የፍሬ ዛፎች በውብ ፍሬዎች ተሞልተው(ውብ ፍሬዎች ተሸክመው) አየሁ። ቤተሰዎች ውብ ልብሶች ለብሰው ያሑዋሕን(እግዚአብሔርን) እያመሰገኑ በኮረብታው/በተራራው ጥግ ወደላይና ወደታች ሲመላለሱ አየሁ።

አካባቢው ፈጽማችሁ ልትሰሙት በምትፈልጉት እጅግ በጣም ውብ በሆነ ሙዚቃ ተሞልቶአል። ሰማያዊ ሙዚቃ የደስታ መግለጫ ነው። ሰማያዊ ሙዚቃ የደስታ መግለጫ፤ የሐሤት ማስረጃ ነው።

በዚህ በመሬት ላይ ውብ ሙዚቃ የሠሩና ያከናወኑ እጹብ ድንቅ ዘማሪዎችና ግርማ ያላቸው ማራኪ የሙዚቃ ቡድኖች ሰምቼአለሁ። ነገር ግን፥ ቅዱሳን ሆይ፥ እዚህ ታች ያለ ምንም እዚያ ካለው የሙዚቃና የዝማሬ ግሩምነትና ውበት ጋር ሊነፃፀር አይችልም።

ሰማይ በዝርዝር የተዘጋጀ ረቂቅ ሙዚቃዊ ቅንብር ነበረ። ከቻላችሁ፥ አስቡ፥ ፍጹም የጠሩ ሚሊየኖች ድምፆች፥ የሰማይን ጣዕመዜማዎች በጣፋጭነት ሲዘምሩ! ከድምፅ የወጣ( off-key) አንድም አልነበረም። ሁሉም በፍጹም ውህደት ነበረ።

ባለ ክር መሣሪያዎች፥ ከመለከቶችና ከሌላ ዓይነቶች የሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር በመሆን ውብ እጀባ አቅርበዋል። ሁሉም(የሙዚቃ መሣሪያዎቹ) በሐሤት መንፈስ ያሑዋሕን እያመሰገኑ ከነበሩት ከተቤዡት ቅዱሳን ድምፆች ጋር ተቀይጠዋል።

የመሣሪያዎቹ የድምፅ ቃና፥ እንደ ዝማሬዎቹ ድምፆች፥ በሁሉን ቻዩ በያሑዋሕ ኃይል ነጽተዋል ፍጹምም ተደርገዋል።

አህ፥ ለ**ያሑዋሕ** የሚቀርቡትን ድንቅ ምስጋናዎች መስማት አስደናቂ ነበር። በምድር(በመሬት) ላይ ጥራት አልባ ቃና ወይም ድምፅ የሆኑ ድምፆች በሰማይ በውብ ውህደት ይዘምራሉ። በዚያ ሁላችንም ደስተኞች እንሆናለን። እዚህ ባለ አስር-ሺህ-ድምፅ ዘማሪዎች እንኳ እጹብ ድንቅና ልብ ከሚነካው ከ**ያሑዋሕ** የመንግሥተ ሰማይ ከተማ ሙዚቃ ጋር ሲነፃፀር ይደበዝዛል!

በሞገድ ላይ ሞገድ የሆኑ ሊታመኑ የማይችሉ (unbelievable) የምስጋና መዝሙሮች በመንግሥተ ሰማይ ገጸምድር ላይና በመንግሥተ ሰማይ ጎዳናዎች በኩል ማዕበል ሆኗል።

በጣም ሁሉን-ያጠቃለለ ከመሆኑ የተነሣ ለሆነ ያህል ጊዜ ስለ ሌላ ነገር መስማት ወይም ማሰብ አልቻልሁም።

በመጨረሻ፥ መልአኩ:- "ነይ እና የ**ያሑዋሕ**ን ክብር እዩ።" አለ።

ሊታሰብ የሚችል እጅግ በጣም አረንጓዴ ሳር ባለው ቦታ ውስጥ ከእርሱ ጋር መሄዴን አስታውሳለሁ። በሳሩ አንዳንድ ቦታዎች እጅብ ያሉ ግዙፍ አበባዎች ነበሩ። አበባዎቹ ውቦች ነበሩ እናም በመጠኑ እንደ ጽጌረዳዎች ይመስላሉ። እያንዳንዱ ተክል ከውብ የአበባ ቅጠሎች የተሠራ ቢያንስ አንድ እምቡጥ(አበባ) አለው። እና፥ ቅዱሳን ሆይ፥ አበባዎቹ እየዘመሩ ያሉ ይመስላሉ!

## የመንግሥተ ሰማይ ፈረሶች

ከመልአኩ ጋር ስጓዝ፥ ውብ ነጫጭ ፈረሶች የነበሩበትን አንድ ቦታ አለፍን። ስለ ፈረሶች እና **ኢየሱስ (ያሕሹዋ)** እንዴት አንድ ቀን ነጭ ፈረሶችን የሚጋልቡ የሰማይ ሠራዊቶችን እየመራ ነጭ ፈረስ ላይ እንደሚቀመጥ በራእይ ማንበቤን አስታወስሁ:

*ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም።*

*ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፥ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፥ ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው፤*

*በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል፥ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።*

*በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር።*

(ራእይ 19፥11-14)

እነዚህ ፈረሶች እንደ እብነ በረድ (marble chess pieces) እጹብ አስገራሚዎች ይመስላሉ። እነርሱ ከትልቅ ቋጥኝ የተቀረጹ ግዙፍ ሐውልቶች ይመስላሉ፥ ነገር ግን እውን እና በህይወት ያሉ ነበሩ። ኮቴዎቻቸው ግዙፍ ነበሩ። እነርሱ ንጹህ ነጭ እና በጣም ሞገሳም (ለንጉሣዊ የሚሆኑ) ነበሩ።

የሚያምር ውብ ቀሚስ የለበሰች አንዲት ሴት ፈገግ እያለች ለ**ያሑዋሕ** ውዳሴ በሚሆን ጉልበቶቻቸውን በርከክ እንዲያደርጉ ፈረሶቹን እያሳየቻቸው እያነጋገረቻቸው ነበር። ሁሉም በአንድ ጊዜ ቀኝ ጉልበታቸውን አንበረከኩና **ያሑዋሕ**ን አመሰገኑ!

"አህ፥ እንዴት ውብ!" ብዬ አሰብሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እያንዳንዱ ፍጥረት በሰማይም በምድርም **ያሑዋሕ**ን እንደሚያከብሩና እንደሚያመሰግኑ ማንበቤን አስታወስሁ:

*ቃሌ ከአፌ በጽድቅ ወጥታለች፥ አትመለስም። ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ።*

(ኢሳይያስ 45፥23)

*እኔ ሕያው ነኝ፥ ይላል ጌታ፥ ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል መላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና።*

(ወደ ሮሜ 14፥11)

*በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤*

*ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥*

*መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።*

(ፊልጵስዩስ 2፥9-11)

*በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ። በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ።*

(ራእይ 5፥13)

ሰላም፥ ሐሴት፥ እና ደስታ ሁሉም ቦታ ነበረ። ሰዎች ያሑዋሕን ሲያመሰግኑ/ሲያወድሱ መስማት ችዬ ነበር።

በድንገት፥ መልአኩን ከእኔ ጋር ማየት አልቻልሁም፥ ኢየሱስ (ያሕሹዋ) ግን ቆመ። ቁመቱ ለኔ በጣም ረጅም መሰለኝ፥ እርሱም ከሌሎቹ ልብሶች ልዩ የሆነ ልብስ ለብሶአል።

የእርሱ ልብ የሚነኩ ዓይኖቹ በጣም ውብ ነበሩ። እርሱ በንጽሕና-የተስተካከለ የሚመስል ጢም እና በጣም ወፍራም ጸጉር ነበረው። እርሱን እየተመለከትሁ በዓይኖቹ ውስጥ ያለው ርኅራኄ ከአንድ ጸሐፊ ማብራሪያ እጅግ በላይ መሆኑን ማሰቤን አስታወስሁ። የቡሩኩ አዳኝ እጅግ መልካምነት (ኀያል ፍቅር) አክብሮታዊ-ድንቅ እና ድንቅ ነበረ።

በውስጤ ያለ ሁሉም ነገር እርሱን (የነገሥታት ንጉሥ እና የጌታዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያሕሹዋ ሐማሺያክን) ለማመስገን፣ ለማምለክ፣ እና በፊቱ ለመስገድ ፈለገ። ክብር እና ኃይል በዙሪያው ሁሉ በሙላት ከብቦታል።

## የፈውስ ግምጃ ቤቶች

የኢየሱስ ዓይኖች በተቸገረ እይታ ትኩረታቸው እንደተያዘ አስተዋልሁ። “ኢየሱስ፥ ምንድን ነው?” ብዬ ጠየቅሁ።

“***ልጄ፥ ተመልከቺ!***”

ግዙፍ ክፍተት ወዳየሁበት ወደ አንድ ሕንጻ እርሱ እጁን አወዛወዘ። ከክፍተቱ፥ ክብር እና የኃይል-ማዕበሎች እና የኃይል ማዕበሎች በኀይል ወጡ።

እርሱን በድጋሜ ጠየቅሁት:- “ኢየሱስ፥ ይህ ምንድን ነው?”

“***ልጄ፥ በእነዚህ ግምጃቤቶች ውስጥ ያሉትን ፈውሶች አየሽ?***”

“አዎ፥ ጌታ ሆይ።”

“***እነዚህ ሁሉ በረከቶች የያሑዋሕን ሕዝብ ይጠብቃሉ (ይጠባበቃሉ)።***”

በዚህ ህይወት ያሉት ሥቃዮች በእርግጥ አሳዛኞች ናቸው። ምን ያህል ሕመም፣ በሽታ፣ አካላዊ መከራ/ሥቃይ፣ አካለ ጎዶሎነት፣ እና ተመሳሳይ በሽታዎች ነው እዚህ ሰዎች የሚሠቃዩት!

ያን ሁሉም ቦታ ታዩታላችሁ። በማንኛውም ሆስፒታል ወይም ዋና የሕክምና ማዕከል ኮሪደሮች ላይ ወደላይና ወደታች ብቻ ተመላለሱ። የተላላፊ በሽታ ክፍሎችን (በሆስፒታል ውስጥ)፣ የአእምሮ ጤንነት ክፍሎችን፣ ብርቱ የክብካቤ ፋሲሊቲዎችን (አገልግሎቶችን)፣ የድንገተኛ አደጋ ክፍሎችን፣ እና በጣም አስጊ ሥቃይ ውስጥ እና ሊሸከሙት የማይችሉት የአካልና የአእምሮ ሥቃይ/ጭንቀት ውስጥ ያሉ ሰዎችን የሚንከባከቡ ሌሎች ቦታዎችን ጎብኙ።

በሽታ/ህመም በዔድን ገነት ውስጥ የአዳምና የሔዋን የመውደቅ ውጤት ነው። በሽታ ኃጢአት ከሚያስከትላቸው ውጤቶች አንዱ ነው። አንዳንዶች በሽታን እንደ ጠንቅ፣ እንደ አሳዛኝ የሰዎች ሁኔታ፣ ወይም እንደ አንድ የተለመደ ተፈጥሯዊ ክፍል ብቻ ያዩታል። በእውነታው፥ በሽታ የሰይጣን እርግማን ነው።

## ፈውስ በመንግሥት ሰማይ

ለፈውስ ፍላጎት በጣም ብዙ ነው። በሽታ/ህመም የ**ያሑዋሕ**ን ፈቃድ ማበላሸት ነው። በሽታ በ**ያሑዋሕ** ኢኮነሚ ውስጥ ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ባህሪይ ነው። በሽታ ከ**ያሑዋሕ** አልተነሣም፤ በሽታ ከሰማይ አልመጣም። ኃጢአት ከመልካም/ከጥሩ ምንጭ ሳይሆን ከክፉ ምንጭ ነው።

ወደ መንግሥተ ሰማይ ስንሄድ፥ ሁሉም ህመም፣ በሽታ፣ እና ሥቃይ ለዘላለም ይጠፋል። ስለ አካላችን የመጨረሻ መዳን ጳውሎስ ጽፎአል:

*ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።*

*የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና።*

*For I consider that the sufferings of this present time are not worthy to be compared with the glory which shall be revealed in us.*
*For the earnest expectation of the creation eagerly waits for the revealing of the sons of God.*
(ሮሜ 8፥18-19)

በዚህ ህይወት ሊደርስ የሚችለው እጅግ አስከፊው አካላዊ ሥቃይ ከዚህ ህይወት በኋላ ከሚሆነው እጅግ በጣም ድንቅ ክብር ጋር ለመነጻጸር አይመጥንም። በመንግሥተ ሰማይ በፍጹም አካላት፥ ያለ ምንም ሥቃይ ወይም ያለ ምንም አካላዊ መከራ/ደዌ በ**ክርስቶስ** እናርፋለን።

አሁንም፥ እርሱ ደግሞ አሁን እንድንፈወስ ይፈልጋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ**ያሑዋሕ** ስሞች አንዱ **ያሑዋሕ-ሮፍኤሐ** (**Adonai Roph'ekha**) ነው፥ ትርጉሙም "**ፈዋሽህ ያሑዋሕ** / **ፈዋሻችን ያሑዋሕ**።" ማለት ነው። **ያሑዋሕ** ልዩ የፈውስ ቃል ኪዳን ከሕዝቡ ጋር አድርጎአል። እርሱ ለእሥራኤል ቃል ገብቶአል:

*አንተ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ ብትሰማ፥ በፊቱም የሚበጀውን ብታደርግ፥ ትእዛዙንም ብታደምጥ፥ ሥርዓቱንም ሁሉ ብትጠብቅ፥ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላደርስብህም፤ እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና አለ።*

(ዘጸዓት 15፥26)

በሽታ የኃጢአት እርግማን አካል ቢሆንም፥ **ኢየሱስ እርሱ** ለኃጢአት ባደረገው ሥርየት በኩል እርግማኑን ለአማኞች አንስቶአል። **ክርስቶስ** የተሠቃየው ቁስሎቹና ሰንበሮቹ ለኃጢአት ዋጋ ከፍሎአል። **እርሱ**(**ያሕሹዋ ሐማሺያክ ኢየሱስ ክርስቶስ**) የእኛ አዳኝ ሆነ። ሆኖም፥ የ**እርሱ** ሥቃይ ለኃጢአት ከመክፈል ብቻ በላይ አድርጎአል: **ኢየሱስ**ን እንደ ፈዋሽ መሥርቶና እውነተኛነቱን አረጋግጦአል!

*እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።*

(ኢሳይያስ 53፥5)

*ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ [ኢየሱስ] ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤*

(1ኛ ጴጥሮስ 2፥24)

## ፈውስ ለዛሬ ነው

**ክርስቶስ ኢየሱስ** ከሐዋርያት ወደ ሰማይ ውስጥ ሲሄድ የ**ክርስቶስ** የፈውስ አገልግሎት አልተቋረጠም። የሐዋርያት ሥራ "**ኢየሱስ** ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ" ቀጣይ ነው። (ሥራ ፲፥፲)።

**ኢየሱስ** (**ያሕሹዋ**) በመሬት ላይ አንድ የፈውስ አገልግሎት አርአያ አደራጅቶአል እና ፈውስ የመንግሥቱ ጥቅሞች አንድ አካል እንደሆነ አስተምሮአል። **እርሱ** ወደ **አባቱ** ከመመለሱ በፊት፥ ሄደው ሕሙማንን እንዲፈውሱ **ኢየሱስ** አማኞችን አዟቸዋል። **እርሱ** እንዲህ አለ:-

*ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥*

*የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።*

(ማርቆስ 16፥17-18)

ኢየሱስ (ያሕሹዋ) ደግሞ ይህን ነግሮናል፦

*እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።*

*ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።*

*ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ።*

(ዮሐንስ 14፥13-15)

ክርስቶስ የተሰወረ ይመስል ነበር፥ እኔም ከመልአኩ ጋር በግምጃቤቶቹ መሐል እየተራመድሁ ነበር። "በጣም ብዙ ግምጃቤቶች፥ ጌታ ሆይ።" ብዬ አሰብሁ።

ኢየሱስ ለመንፈሴ ተናገረ: "***ልጄ ሆይ፥ በመሬት ላይ ለአንድ ሰው ስትጸልዩ፥ ለእነርሱ በስሜ ጸልዩላቸው። ይሄን አስታውሺ ፈውሱን አንቺ አታደርጊም - እኔ ነኝ የማደርገው። ዓይን ወይም እግር እንድፈውስ እኔን ጠይቂኝ፥ እኔም አደርገዋለሁ። የዞረ/የተጣመመ እጅና እግር እንዲቃና ወይም የታመሙ አካላትን እንድረውስ ጠይቂኝ፥ እኔም እፈውሳቸዋለሁ።***"

"***እኔ እንዳደርገው የምትፈልጊውን ማንኛውንም፥ በስሜ ጠይቂ፥ እኔም አደርገዋለሁ። በእነዚህ ግምጃቤቶች ውስጥ እየጠበቁ ያሉ መልሶች አሉኝ።***"

በእነዚህ ግምጃቤቶች ውስጥ ያሉት በረከቶች በመሬት ላይ ላሉ ለእርሱ ሕዝብ እና በመሬት ላይ ላሉ ኃጢአተኞች እንደነበረ ኢየሱስ አጉልቶ ተናገረ። በዚህ ዓለም ላይ በጣም በቅርቡ የፈውሶች ናዳ (ብዙ ፈውሶች) እንደሚሆን ኢየሱስ እንደተናገረ አስታወስሁ።

በመሬት ላይ አሁን እየሆኑ ስላሉት ፈውሶች አሰብሁ፥ እና ይህን አሰብሁ "ጌታ ሆይ፥ የእኛን አካላት ለመጠገን አንተ እንዴት ድንቅ ነህ!"

እያረጀን ስንመጣ አካላችን መጨረስ (wear out) ወይም መበላሸት (deteriorate) ይጀምራል። ያ የኃጢአት ተፈጥሯዊ ውጤት ነው፥ እኛም ከእነዚህ ውጤቶች በፍጹም ሙሉ በሙሉ ነጻ መሆን አንችልም። ነገር ግን ያሑዋሕ የመጨረሻ ዘመኖቻችንን የአልጋ ቁራኛ ወይም አጥጋቢ-ያልሆንን ሆነን እንድናሳልፍ አይሻም። ንቁና ፍሬያማ ሆነን እንድንቆይ እርሱ ይፈልጋል። እኛ ሙሉ እንድንሆን ኢየሱስ ሞተ።

የያሑዋሕ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እኛ ከሲኦል እንድንን ዘንድ እርሱ ደሙን(የራሱን) አፈሰሰ። ኢየሱስ ክርስቶስ (ያሕሹዋ ሐማሺያክ) የያሑዋሕ ልጅ እንደሆነ ካመንን፥ ተስፋ አለን። ለነፍሳችን ተስፋው በኢየሱስ ነው።

ለአካላቶቻችን ፈውስ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሠቃይቶአል። ለሙሉነትና ለደኅንነት/ለጥሩነት የእኛ መብት፣ የእኛ በረከት፣ እና የእኛ ተስፋ በኢየሱስ ነው። ለእኛ አካል ደኅና መሆን እርሱ ተስፋ ነው።

ቅዱሳን፥ የአልተወሰዱ/የአልተጠየቁ በረከቶች ግምጃቤቶች በሰማይ ውስጥ አሉ። እነርሱ (ያልተወሰዱት በረከቶች) በእምነትና በኢየሱስ ስም በሚጠይቁ በያሑዋሕ ልጆች ለመወሰድ ዝግጁ ናቸው!

እርሱ በመሬት ላይ ሳለ፥ አንዴ ጌታ፦ "ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና" ብሎአል (ዮሐንስ 14፥2)። እርሱ እያዘጋጀው ያለው ቦታ በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ነው። ብዙ ውብ ነገሮች ያሉበት ውብ ቦታ ነው።

በዚህ መጽሐፍ እኔ ምስክርነቴን ስሰጥ እና ስለ መንግሥተ ሰማይ ስናገር፥ የዛ ቦታ አሳቦች ነፍሴን በጥልቅ የደስታ ስሜት ያነቃቁታል። ልጆቹ ለሆንን ለእኛ ስለሰጠን ውብ ቃል ያሑዋሕን አመስግኑ!

-------------------------------------------------------

# ትእዛዝ በመንግሥተ ሰማይ

መንግሥተ ሰማይ ሥራ-የሚበዛበት (ባተሌ) ቦታ ነው። ሰማይ በእንቅስቃሴዎችና በሚያስደንቅ ጉጉት ተሞልቶአል። መላእክት ሁል ጊዜ ነገሮችን እየሠሩ ነው። እነርሱ ሁል ጊዜ በጠቃሚ፣ ታታሪ ሥራዎች (enterprises) ተሰማርተዋል።

የዚህ መጽሐፍ አንዱ አላማ መላእክት በመንግሥተ ሰማይ ሲሠሩ እንዴት እንዳየኋቸው ለእናንተ ለመንገር ነው። እነርሱ ደስተኛ እና ሐሴተኛ ናቸው - በፍጹም አይደክሙም በፍጹም አያዝኑም። እነርሱ ሁል ጊዜ ያሑዋሕን እያወደሱ ናቸው።

የተቤዡት ቅዱሳንም በመንግሥተ ሰማይ ባተሌ ናቸው። እነርሱ ሁል ጊዜ የሚሠሩት ሥራ አላቸው። በትክክል ቅዱሳኑ ሁሉ በምን ዓይነት ሥራ እንደተሰማሩ አላውቅም። ነገር ግን በዛ መልካም ውብ ምድር ማንም ሥራ ፈት እንዳልሆነ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ። ቅዱሳን በሥራ ዓይነቶች ባተሌ ናቸው በምድር ማንም በፍጹም ያልተለማመደው። እነርሱ ሥራዎችን በማነቃቃት፣ ደስ በማሰኘት፥ በመፈፀም ተሳትፈዋል።

እነርሱ ያለማቋረጥ/በቀጣይነት ያሑዋሕን እያወደሱ/እያከበሩ እና ያሑዋሕ ለእነርሱ እንዲሠሩ የወሰነላቸውን ነገሮች እያደረጉ ነው።

ከሪፖርቶች ጋር ከመሬት የሚበርሩ መላእክትን ሳይ፥ እነርሱ ከዓለም ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ ውስጥ እየመጡ ነበር። እነርሱ በብዙ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶችና በብዙ የጸሎት ስብሰባዎች/ጉባኤዎች ላይ ነበሩ።

በመሬት ላይ ነገሮቹን እየተመለከትሁ/እየተከታተልሁ እያለ፥ እነርሱ ሁል ጊዜ በእጃቸው ጥቅልል የሚመስሉ የወርቅ ጠርዝ ያላቸው ነጭ የወረቀት ቁራጮች ይይዛሉ። ከዛ እነርሱ ወደተወሰኑ/ወደአንዳንድ የመንግሥተ ሰማይ ክልሎች ይመለሱና ሪፖርቶቻቸውን ለሌሎች መላእክት ያካፍላሉ።

## የመንግሥተ ሰማይ ሕዝብ

በመንግሥተ ሰማይ በአንድ ክልል፥ ውብ፣ የከበሩ ነጭ ልብሶች የለበሱ ቅዱሳን ወንዶች አየሁ። ወዲያውኑ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አሰብሁ:

*አክሊልን እንደ ለበሰ ሙሽራ፥ በጌጥ ሽልማትዋም እንዳጌጠች ሙሽራ፥ የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፥ የጽድቅንም መጐናጸፊያ ደርቦልኛልና በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፥ ነፍሴም በአምላኬ ሐሤት ታደርጋለች።*

(ኢሳይያስ 61፥10)

በሰማይ ያየኋቸው ሰዎች ልዩ የፊት ቅርፅ (የተለያየ መልክ) ነበራቸው እና ከሁሉም የምድር ሕዝቦች ነበሩ።

መጽሐፍ ቅዱስ:

*ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤* ይላል

(ራእይ 7፥9)

በእኔ ላይ ዘለቄታዊ መገረም ያኖረው ሌላው ነገር መንግሥተ ሰማይ ሥርአትን የጠበቀ ቦታ የመሆኑ እውነት ነበረ። የተሠራው ሁሉም ነገር በዝርዝር/በጥንቃቄ፣ በትክክል/በተስማሚ፣ እና እጅግ በከበረ ዲግሪ/አኳኋን ነበረ የተሠራው። ምንም/የትኛውም ሥራ መናኛ አልነበረም፤ ምንም/የትኛውም ዕቃ/ምርት አነስተኛ አልነበረም፤ ምንም/የትኛውም እንቅስቃሴ ተራ/አማካይ-ጥራት ያለው አልነበረም።

ቤተሰዎች በተቀደሱት ተራሮች ላይ እየተራመዱና ያሑዋሕን እያመሰገኑ ሳይ፥ ያ እጅግ ውብ እይታ ነበረ። የእነርሱ ሐሴት እና ደስታዎች ያለቁጥጥር እና ያለ ገደብ ነበረ። እነርሱ ሁልጊዜ በአዶናይ (በጌታ) ፊት የሚሄዱና ግሩም ሥራዎችን የሚሠሩ ይመስላሉ።

በግልም ሆነ በቡድን የሚሠራ እያንዳንዱ ነገር ሥርአቱን በጠበቀ መልክ ነበረ የሚሠራው። መንግሥተ ሰማይ ካለመጣራትና ፍጹም ካለመሆን ሙሉ በሙሉ የጠራ ነበረ። መንግሥተ ሰማይ በእያንዳንዱ የቃሉ ትርጉም/መረዳት ፍጹም ነበረ። እዚህ በምድር ላይ የምናውቃቸው/የለመድናቸው ማስተካከያዎች እና ለውጦች/ቅያሬዎች በያሑዋሕ (በእግዚአብሔር) ገነት አይታወቁም። ፍጹም ደስታና ሰላም እዛ ያሉትን የሁሉንም ልቦች፣ ነፍሶች፣ እና አካላት ሞልተዋል።

## ፍጹም ትእዛዝ

መለኮታዊ፥ ፍጹም ትእዛዝ እና አላማ በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ የሚሆነውን ሁሉንም ያስረዳል።

መላእከትና ቅዱሳን ሁለቱም እጅግ በከበረ መልካም፣ በሚያስደስት አገልግሎት በቀጣይነት ተሰማርተዋል። ማንም ሥራ ፈት አይደለም። ማንም ደብሮት በፍጹም አያውቅም።

የያሑዋሕ ልጆች፣ እንዲሁም መላእክትና ሁሉም ሰማያዊ ፍጥረታት፥ በቀንም በሌሊት ለዘላለም እርሱን ያገለግሉታል።

ከቅዱሳን ትንሣኤ በኋላ አዲስ ሰማያዊ አካላት ስንቀበል፥ እኛ አይደክመንም ወይም ደካማ አንሆንም። ድካምን(ከባድ ድካምን) በፍጹም አናውቅም። ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ፣ የከበሩ አካላቶቻችን ጥንካሬያቸውን በፍጹም አያጡም። በዘላለም፥ ሰዓት ታግዷል እና ሁኔታዎችም አእምሮን፣ ፈቃድን፣ ወይም አካልን አያጠፉም።

በመንግሥተ ሰማይ ቅጥሮችና ደስታዎች ለመሰማራት፥ ሰማያዊ ተፈጥሮ የግድ ሊኖረን ይገባል። ዳግም ስንወለድ የሚሆነውም ይህ ነው - "ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች" (2ኛ ጴጥሮስ 1፥4) ፥ ጴጥሮስ እንዳብራራው፡-

በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል። ከክፉ ምኞት የተነሣ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል።

(2ኛ ጴጥሮስ 1፥3-4 NIV)

የመንግሥተ ሰማይ የሕንፃ ጥበብ የተነደፈውና የተገነባው በዘላለም ውስጥ በዘላለማዊው አምላክ ነው። በአንድ ክፍል ያየሁት የመንግሥተ ሰማይ ከተማን ጠቅላላ ማዕዘን የሚመስል ነው። ሕንፃዎቹ በጣም ግዙፍ ነበሩ። በእያንዳንዱ ሕንፃ አናት ከጥግ እስከ ጥግ ላይም ከብዙ የከበሩ የድንጋይ ፈርጦች የተሠራ እጅግ ግዙፍ፣ አስደናቂ ዘውድ ነበረ። በአንዳቸውም ውስጥ ስላልገባሁ እነዚያን ግርማ ሞገስ ያላቸው ታላቅ ሕንፃዎች ምን ያህል ሰዎች እንደያዟቸው አላውቅም። ሕንጻዎቹ ግን በምድር ላይ ካያችሁት ከማንኛውም እጅግ በላይ ሁሉም ግርማ ያላቸውና ሰፊ ነበሩ።

በምድር ላይ ለኢየሱስ ስንሠራ/ስንጥር በሰማይ ውስጥ መዝገብ እያኖርን እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት እንደተናገሩት አሰብሁ (ሉቃስ 18፥22)።

በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ። ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን፤

አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ።

(ራእይ 11፥16-18)

እነሆ፥ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና

(ሉቃስ 6፥23)

እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።

(ራእይ 22፥12)

## የያሑዋሕ ሰረገላዎች

ወደ ሌላኛው የመንግሥተ ሰማይ ክፍል ስንንቀሳቀስ፥ የአዶናይ (የጌታ) መልአክ እንዲህ አለኝ:- “ነይ እና የአምላክሽን ክብር እዩ።”

መልአኩ የያሑዋሕን ሰረገላዎች አሳየኝ። የሰረገላዎቹ መንኰራኵሮች በጣም ግዙፍ ስለነበሩ ለመግለፅ አዳጋች ነው። እነሱ በዕንቁዎች በደማቅ ቀይ የከበሩ ድንጋዮችና በመረግዶች አጊጠው ነበረ።

እያንዳንዱ ሰረገላ በእያንዳንዱ ጎኑ ቢያንስ ሁለት መንኰራኵሮች ነበሩት። የሰረገላዎቹ የፊት በኩል እንደ የበረዶ ላይ ጋሪ ዝቅ ያሉና ክፍት ነበሩ። እነርሱ በእሳት ላይ ያሉ ይመስሉ ነበር፥ ነገር ግን በፍጹም አልጠፉም ነበር።

## ጥራት ያላቸው አካላት

በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ያየኋቸው ሰዎች ሁሉ መልክ/ሁኔታ የከበረና ውብ ነበረ። አንድም ሰው ጠባሳ የለውም፥ እነርሱ ሁሉም ብሩህ ደስተኛ እና ውብ/የሚያምሩ ይመስላሉ።

ሰዎች እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ:- “መቼም፥ የጭስ እንፋሎት ልንሆን ነው በቃ።” አይደለም፥ የጭስ እንፋሎት ልትሆኑ አይደለም። እናንተ አካላዊ ቅርጽና መልክ ይኖራችኋል።

መጽሐፍ ቅዱስ በዙፋኑ ዙሪያ ሽማግሌዎች እንዳሉ ይናገራል:

*በዙፋኑ ዙሪያም ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር።*

(ራእይ 4፥4)

በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ያሉት ፓትርያርኮች/አባቶች ሞተው ከእኛ በፊት እዛ የሄዱ የያሑዋሕ ውብ ቅዱሳን ናቸው። ያሑዋሕ የዘላለም ሕይወት ሰጥቷቸዋል። ከትንሣኤ በኋላ የእነርሱን(የራሳቸውን) አዲስ፣ የከበሩ አካላት ሲቀበሉ እነርሱ ወደፊት የሚሆኑትን አይቻለሁ።

ቅዱሳን፥ በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ለማመን በሚያስቸግር መልኩ እናንተ ደስተኛ ትሆናላችሁ። በመንግሥተ ሰማይ ሳለሁ፥ የቤት ትዝታዎች እርቀው ነበር። እዛ ምንም ኅዘን የለም፣ ምንም ኅዘን (ምንም ከባድ ጭንቀት) የለም፣ ምንም ከባድ ኀዘን የለም። በአዶናይ (በጌታ) ደስታ ተደስቼ ነበረ በእርሱ ውበትም ተደንቄ ነበር።

በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ምንም ጨለማ የለም። እዛ በሁሉም ቦታ ክብር እና ብርታት እና ኃይል ብቻ ነበረ፥ በተለይ ዙፋኑን ስትቀርቡ። የሕይወት ውሃ ወንዝ ከዙፋኑ በታች ይወጣ ነበረ። ውብ ነበረ እንደ ብርጭቆ ባሕርም ይመስላል:

*በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ።*

(ራእይ 22፥1)

እየሄድሁ እያለ መልአኩ እንዲህ አለ:- “ነይ እና የያሑዋሕን ክብር እዩ።”

ቅዱሳን፥ የያሑዋሕ ከፍተኛ ምስጋናዎችና ሙዚቃ በኃይልና በድምፅ የሚያድጉ ወደሚመስልበት ቦታ እጅግ በከፍተኛ ፍጥነት በመልአኩ ተወስጄ ነበር። በሕይወታችሁ ሁሉ ልትሰሙት የምትፈልጉት እጅግ በጣም ውብ ሙዚቃ ነው። የደስታና የጩኸት ድምፆች በሁሉም ቦታ ነበሩ።

የያሑዋሕ መልአክ እንዲህ አለ:- “ዙፋኑን እየቀረብን ነው።” እኔም እንዲህ ብዬ አሰብሁ:- “ኦህ፥ ያሑዋሕ፥ እንዴት የከበረ፥ እንዴት ውብ!”

## ያሑዋሕ ሲናገር

ያሑዋሕ ሲናገር፥ እያንዳንዳቸው ርዝመታቸው ከአስራ ሁለት እስከ አስራ አምስት ፊት የሆነ አስራ ሁለት በጣም ረጃጅም መላእክት ከዙፋኑ ፊት ለፊት የቆሙ መሰለ። መለከታቸውን እንዴት ይነፉታል!

ውብ የከበሩ የድንጋይ ፈርጦች የልብሳቸውን የፊት በኩል አስጊጠውታል። በሙዚቃ እና በሚሉትና በሚያደርጓቸው ነገሮች ሁሉ ሁኔታውን አነሣሥተውታል። አዶናይ (ጌታ) እንዲናገር መንገድ የሚያዘጋጁ ይመስላሉ።

አዶናይ ሲናገር ወይም መልእክት ሲያውጅ ወፍራም ደመና ኀይለኛውን ዙፋን ሲከብበው ማየት ችዬ ነበር።

*ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፥ እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።*

(ራእይ 4፥5)

ከዚያ ኃይል ከዙፋኑ ፊተኛ በኩል በግዙፍ ደመና ማዕበል ይወጣ ነበር። በዙፋኑ መሐል፥ ሁሉን ቻይ ያሑዋሕ በክብር ደመና ውስጥ ይኖራል።

ያሑዋሕ ሲናገር፥ ድምፁ "እንደ ብዙ ውኃዎች" ነው (ራእይ 14፥2) ፥ እኔ ግን እያንዳንዱን ቃል ተረዳሁ።

አንዴ ያሑዋሕ ስለ ልጁ ደም መናገር ጀመረ። የእርሱ ልጅ ደም በምድር ላሉ ሰዎች ሁሉ እንዴት እንደፈሰሰ እርሱ ተናገረ።

የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም (የልጁ የያሕሹዋ ሐማሺያክ ደም) ከኃጢአት ሁሉ ሊያነጻን እንደሚችል እርሱ ተናገረ (1ኛ ዮሐንስ 1፥7) ፥ እርሱም ይህንን ግብዣ ረዘም አደረገው:

*የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።*

(ራእይ 22፥17)

*የልጁ ደም የፈሰሰው ወንዶችና ሴቶችን ከኃጢአታቸው ሊያድናቸው እንደሆነ እግዚአብሔር ተናገረ። ለእኛ የዘላለም ሕይወት ለመስጠት ልጁን በመስቀል ላይ ማኖሩ ከሁሉም የተገባው እንደነበረ፥ እና የልጁ ደም እኛን ለማዳን ዋጋውን እንደከፈለ እርሱ ተናገረ።*

*በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።*

(ኤፌሶን 1፥7)

*እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።*

*whom we have redemption through His blood, the forgiveness of sins.*

*(ቆላስያስ 1፥14)*

*ኢየሱስ ክርስቶስ. . .ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥*

(ራእይ 1፥5)

በመንግሥተ ሰማይ ሳለሁ፥ የያሑዋሕን ድምፅ መስማት እጅግ አጓጊና የሚያስደንቅ የሚያስደስት ነበረ። የያሑዋሕ ድምፅ ኀያል ጠንካራ ቢሆንም ትሑትና ወዳጃዊ ደስ የሚል ማራኪ ነበረ። እርሱ የተናገረውን ሁሉንም መረዳት ችዬ ነበረ።

"ያሑዋሕ ሆይ፥ አንተ እንዴት ውብ ነህ! አንተ ሁሉንም አዘጋጅተሃል። አንተ ሁሉንም ለኛ ሠርተሃል፥ ጌታ ሆይ! ለምናፈቅርህ ለእኛ አንተ ያዘጋጀኸውን ነገሮች ለማሰብ መጀመር እንኳ አንችልም።" ማሰቤን ቀጠልሁ። (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥9)።

## መንግሥተ ሰማይ፣ እውን ቦታ

“መንግሥተ ሰማይ እውን መሆኗን። እነዚህ ሰዎች እውን መሆናቸውን። እነዚህ መላእክት እውን መሆናቸውን። ይህ ሁሉ ውብ እና እውን መሆኑን፥ እና አዶናይን ማገልገል እንደቀጠልሁ የሆነ ቀንም ይህን እንደምወርስ።” ማሰብ መቀጠሌን አስታወስሁ።

ስለ መንግሥተ ሰማይ እና የያሑዋሕን በጣም ድንቅነት ማውራት ለኔ በጣም ደስታ ነው። እርሱን ማገልገል ስለመቻሌ በልቤ ሁሉ አመሰግነዋለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሴን ከመጥፎ ሲኦል ስላዳናት ያሑዋሕን አመሰግናለሁ። እኔ ዳግም የተወለድሁ፣ በደሙ የታጠብሁ የንጉሡ ልጅ በመሆኔ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታዬ በመሆኑ ያሑዋሕን አመሰግናለሁ!

አንተ/አንቺ ዳግም ካልተወለድህ/ሽ፥ ከኃጢአቶችህ/ሽ መዳን ያስፈልግሃል/ግሻል። ኢየሱስ ክርስቶስ (ያሕሹዋ ሐማሺያክ) ወደ ልብህ/ሽ ውስጥ እንዲመጣና ነፍስህን/ሽን እንዲያድናት ኢየሱስ ክርስቶስን መጠየቅ ያስፈልግሃል/ግሻል።

እርሱ የያሑዋሕ ልጅ እንደሆነ እመን/ኚ። ያሑዋሕ አብ ወደዚህ ምድር እንደላከው፥ ከድንግል ማርያም እንደተወለደ፥ እርሱም እኛን ከሲኦል ሊያድን የተላከው ቅዱሱ የያሑዋሕ ልጅ እንደሆነ እመን/ኚ። ከሁሉ በላይ፥ ኢየሱስ (ያሕሹዋ) ለኃጢአቶችህ/ሽ ብቸኛው ተቀባይነት ያለውን መሥዋዕት እርሱ በመስቀል ላይ ሲሞት ኢየሱስ (ያሕሹዋ) እንደከፈለ እመን/ኚ።

--------------------------------------------------------

# ሕፃናት ላይ ምን ይሆናል

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ኢየሱስ ስለሕፃናት ተናግሯል፡፡ "*ሕፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና አለ፤*" (ማቴዎስ 19፡14) ኢየሱስ እነዚህንም ነገሮች ተናግሯል፡-

"*እንዲህም አለ፡- እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው።*" (ማቴዎስ 18፡3-4)

ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናግሯል፡-

> "*እውነት እላችኋለሁ፤ የያሑዋሕን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው።*" (ማርቆስ 10፡15)
>
> "*እንደዚህ ካሉ ሕፃናት አንዱን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን እንጂ እኔን አይቀበልም አላቸው።*" (ማርቆስ 9፡37)

በብሉይ ኪዳን ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

> "*ይህን ለልጆቻችሁ ንገሩ፤ ልጆቻችሁም ለልጆቻቸው፥ ልጆቻቸውም ለኋለኛው ትውልድ ይንገሩ።*" (ኢዩኤል 1፡3)

ይህኛው የገነት ክፍል የእውነት ብዙዎችን ያስደምማል፡፡ ብዙ ሰዎች ይህን አጥላልተውታል፥ ነገር ግን ያሑዋሕ እንዳሳየኝ አውቃለሁ፡፡ በአንዱ የገነት ጉብኝቴ ጊዜ ነው የሆነው፡፡

ታላቅ የቀስተደመና ቀለም ከነበረው ታላቅ መልአክ ጋር ነበርሁ፥ ባለሦስት ማዕዘን ቅርጽ ክንፎችም ነበሩት፡፡ መልአኩ ነጭ አብረቅራቂ ልብስ ለብሷል፥ ጸጉሩም እንደ ተፈተለ ወርቅ ነበር፡፡ ገጽታው ያማረና የከበረ ነበር፡፡ ብርሃንና ኃይል በላዩ ሞልቶ ነበር፡፡

"*ነይና የያሑዋሕን ክብር እዩ፡፡ የያሑዋሕ ልጆች ወዴት እንደሚሄዱና ሲሞቱ በእነርሱ ምን እንደሚሆን ላሳይሽ እንደሚገባኝ ነግሮኛል፡፡*" አለኝ፡፡

አሁን አንድ ነገር ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲኦልን ሲያሳየኝ፥ ልጆችን በጭራሽ አላየሁም፡፡ ምንም የማስታውሳቸው ሕፃናት ልጆች ወይም ጨቅላዎች አልነበሩም፡፡

ይህ ከሌሎች ሰዎች መላምቶች ጋር ላይስማማ ይችላል፥ ነገር ግን የያሑዋሕ መልአክ ስለሲኦልና ስለገነት ሕፃናትም በሞቱ ጊዜ ወዴት እንደሚሄዱ የነገረኝን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ያሑዋሕን እያወደስሁና ከመልአኩ ጋር እየተጓዝሁ ነበር፡፡ ስንቆምና መልአኩ "*እነዚህን ነገሮች ላሳይሽ እፈልጋለሁ፥*" ሲለኝ ከህዋ በላይ ነበርን፡፡

## እያስታወስኩ

ከጌታ መልአክ ጋር ሳለሁ፥ አሁን የማላስታውሳቸው ብዙ ነገሮች ሆነዋል፡፡ አንዳንዶቹን እንዳስታውስ አልተፈቀደልኝም፡፡ በገነት ጉዞዬ ብዙ ክስተቶች ተከናውነዋል-እንዳያቸው የተደረጉ ነገር ግን የማላስታውሳቸው ነገሮች፡፡ ሆኖም ግን፥ እንዳስታውሳቸው የተፈቀዱልኝ ነገሮች ስለገነት እንድነግራችሁ እኔን ለማነሳሳት በቂ ናቸው!

ዳንኤል የእነዚህ ራዕዮችና ሕልሞች ሙሉ መረዳት ነበረው፡፡ ሆኖም ግን፥ ጌታ ወደ ገነት ሲወስደኝ-ኡ-ድንቅ የሆነ ክብርና ኃይል በዚያ ነበረ! ለእኔ ያልተብራሩልኝ ነገሮች እየሆኑ ነበር፥ እናም ደግሞ ወደ ተወሰኑ የገነት ክፍሎች ብቻ ነበር የተወሰድሁት፡፡ ለእኔ በጣም አስደናቂው ክፍል ለሕፃናትና ለትናንሽ ልጆች የሆነው ነው፡፡

# ያልተወለዱ ልጆች

የ**ያሑዋሕ** መልአክ "*መጥተሽ እዪ፥*" ሲለኝ፥ እጁን በአየር ላይ አንቀሳቀሰና፥ የሆስፒታል እይታ ተገለጠ፡፡ አንድ ሴት በማዋለጃ ክፍል ውስጥ ልጅ ስትወልድ አየሁ፡፡

የ**ያሑዋሕ** መልአክ እንዲህ አለኝ፦ "*ጽንሱ ጨንግፎባታል፥ ገና ሦስት ወሩ ነው፡፡*"

ሁኔታውን ስመለከት፥ ሁለት የተዋቡ መላእክት በአልጋዋ አጠገብ መጡ፡፡ በእጆቻቸው በነጭ እምነበረድና እንቁ የተሠራ ቅርጫት የሚመስል ነገር ይዘዋል፡፡ ካየኋቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ የተዋበ ነገር ነበር፡፡ መሀሉ ላይ ይከፈትና በዳርና ዳር ይዘጋል፡፡

መላእክቱ **ያሑዋሕ**ን እያወደሱ ነበር፡፡ እሰማቸው ነበር፡፡ ሴትየዋ ጭንገፋ ሲሆንባት፥ የሕፃኑ መንፈስ፥ ልክ እንደ ትነት፥ ከዚያ ትንሽ፥ ጩጩ ልጅ ወጣ፡፡ የ**ያሑዋሕ** መላእክት ያዙት፥ በቅርጫቱ ውስጥ ከተቱት፥ ክዳኑን ከደኑና እጆቻቸውን ወደ ሰማይ አነሱ፡፡ መላእክቱ ሃሌሉያ (**ያሑዋሕ**ን አወድሱት) እያሉ መጮህ ጀመሩ፡፡ አወጁት እንደ **የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ** ከፍ አደረጉት፥ እንደ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ **ፈጣሪ**፡፡ "*ለያሑዋሕ ክብር ይሁን!*" ጮሁ፡፡

አልፈውን ሲሄዱ፥ በድጋሚ "*መጥተሽ እዪ*" አሉኝ፡፡

በመግቢያዎቹ ወደ ገነት ተመለስን፡፡ ኦ! ይህ የገነት እጅግ የተዋበው ስፍራ ይመስላል! ወደዚህኛው የገነት ክፍልም ሆነ በዚህኛው በር መጥቼ አላውቅም፡፡

ከመላእክት ጋር ወደ ተለያዩ የገነት ክፍሎች ስሄድ አስታውሳለሁ፡፡ አብሮኝ ከነበረው መልአክ ጋር ነበርሁ፡፡ በጣም ወደ ላይ ስለወጣን (የ**አብ**) ዙፋኑ በድጋሚ ይታየኝ ነበር፥ እንዲሁም ለ**ያሑዋሕ** ጩኸቶችንና ውዳሴዎች መስማት እችል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በዙፋኑ የግራኛው ክፍል የቀረብን ይመስላል፡፡

በዚህ አቅጣጫ ስመጣና "*ኦ አምላክ ሆይ፥ እንዴት ውብ ነህ፡፡ እንዴት ድንቅ ነህ፡፡*" እያልኩ ሳስብ አስታውሳለሁ፡፡ የ**ያሑዋሕ** ከፍ ያሉ ውዳሴዎች ክብሩና ጩኸቶቹ በየቦታው ነበሩ፡፡

ታውቃላችሁ ቅዱሱ መጽሐፍ ስለመላእክት አብዝቶ ይናገራል፡፡ አንዳንድ ምሳሌዎች እነዚሁላችሁ፦

> "*ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ ያሑዋሕን ባርኩ።*" (መዝሙር 103:20)
>
> "*የያሑዋሕ መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥ ያድናቸውማል።*" (መዝሙር 34:7)
>
> "*እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ።*" (ማቴዎስ 28:2-3)

**ኢየሱስ** በመላእክት ወደ ገነት ስለመወሰድ ተናግሯል፤

> "*ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ።*" (ሉቃስ 16:22)

# የ**ያሑዋሕ** መላእክት

**በጌታ ቃል** ውስጥ መላእክትን አስመልክቶ ብዙ ጥቅሶች አሉ፡፡ **ቃሉ** ነገሮችን እንዴት እየደጋገመ እንደሚያረጋግጣቸው እያሰብሁ ነበር፡፡ ነገር ግን ለአንድ ሰው መገለጥ ሲሰጠው፥ የበለጠ ብርሃን ያበራለታል፡፡

በ**ያሑዋሕ** ቀዳሚ ጥሪዬ ሕልሞች፥ ራዕዮችና መገለጦች ናቸው፡፡ የእኔ ምስክርነት እኔ የ**ያሑዋሕ** የእጁ ሥራ መሆኔ ብቻ ነው፥ እናም ይህን ስለልጆች ያለውን ታሪክ መናገር እወዳለሁ፡፡

ኦ፥ ያየነው ክብር እንዲሁም የሰማናቸው የውዳሴ ድምጾች! በዙፋኑ ዙሪያ መብረቅና ነጎድጓድ ቀስተደመናም ነበር፡፡ ዙፋኑን በሸፈነው የክብር ደመና ውስጥ የአንድ ሰው ምስል ነበር፡፡

መላእክቱ ወደ ዙፋኑ ያመጡትን ቅርጫት አስቀምጠው ሰገዱ፡፡ የክንፎቻቸው ጫፎች ወደ ላይ ወጡ፡፡ "ክብር!" እና "ሃሌሉያ!" እንዲሁም "**ያሑዋሕ**ን አመስግኑት!" የሚሉ ጩኸቶች በመላው ገነት አስተጋባ፡፡

በድጋሚ በግዙፍ ትዕይንት ቦታ ውስጥ ያለን ይመስላል፡፡ ረዣዥም መላእክት የሆነ ነገር እንደሚያስተዋውቅ መለከቶችን እየነፉ ነበር፡፡

አሁን፥ ያሑዋሕን አላየሁትም፥ ነገር ግን ልክ ሙሴ እንዳየው ያሑዋሕን የሚመስል አየሁ፡፡ (ዘጸአት 33፡17-23 ያለውን ተመልከቱ) ከዚያም አንድ እጅ ቅርጫቱን ሲከፍት አየሁ፡፡ **የያሑዋሕ እጅ** ምስል እንደነበረ እርግጠኛ ነበርሁ፡፡

የተወደዳችሁ ሆይ፥ እላችኋለሁ፥ የያሑዋሕን ክብሩንና ኃይሉን ለእኔ እንደገለጠለኝ ብቻ እንኳን ብታዩት! ኃይሉ የሚያፈዝና የተዋበ የሚደንቅም ነው!

ያ እጅ ከደመናው ውስጥ ሲወጣና ቅርጫቱን ሲከፍት አየሁ፡፡ ያቺን ትንሽ ነፍስ ከቅርጫቱ ውስጥ አውጥቶ በመሠዊያው ላይ አስቀመጣት፡፡ ከዚያም እጆች በዚያች ትንሽ ነፍስ ላይ ሲሠሩ አየሁ፡፡

ሥራው ሲያልቅና ሲፈጸም፥ እጅግ የተዋበ፥ ፍጹም የሆነ የሰው አምሳል መፈጠር ጀመረ፡፡ አይቼው የማላውቀው በጣም የተዋበ ወጣት ወንድ እስኪሆን ድረስ አደገ፡፡

## በያሑዋሕ እንክብካቤ ውስጥ

በገነት ምንም ጉድለቶችም ሆኑ የኃጢአት ምልክቶች የሉም፡፡ ስለአዳም ፍጥረት የተጻፉት ጥቅሶች መጡብኝ፡፡ ከዚያም ጌታ እንዲህ አለ፡ "*በዚህ ቦታ ምንም ፍጹም ያልሆኑ ነገሮች የሉም፡፡ በመጨረሻው አዳም የታጡት ነገሮች ሁሉ በመጀመሪያው አዳም ተመልሰዋል፡፡*"

ይህ የእኔ ጥብቅ እምነት ነው ብቸኞቹ በገነት ያሉት የኃጢአት ምልክቶች በኢየሱስ እጅና እግር ላይ ያሉት ቁስሎች ናቸው፡፡ ይህ **ክቡር ጌታችን** ስለእኛ መቤዠት የከፈለው ዋጋ ሆኖ ከዘላለም እስከዘላለም ሲታወስ ይኖራል፡፡

ከዚያም የያሑዋሕ ራስ እንደሆነ በውስጤ የተረዳሁትን ነገር አየሁ-እንደ በግ ጸጉር ይመስል ነበር፡፡ (ራዕይ 1፡14) በዚህ ትንሽ ልጅ ላይ ጌታ እፍ ሲልበት አስደናቂ ለውጥ ሆነ፥ ከዚያም ሙሉ የሆነ ፍጹም ፍጥረት ሆነ፡፡

መላእክቱ መጮህና ያሑዋሕን ማወደስ ጀመሩ፡፡ ይህን ታላቅ የያሑዋሕ ኃይል መገለጥ ስመለከት ሳለሁ በጨቅላዎችና በልጆች ላይ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄዬ ከውስጤ በኖ ጠፋ፡፡ አሁን ያለመጠራጠር በ**ያሑዋሕ እጅ** ውስጥ እንዳሉ አውቃሁ፥ ወደ ፍጹምነት እየተሠሩ!

ከዚያ እኔና መልአኩ ወደ ላይ መሄድ ጀመርን፥ በገነት ወዳለ ቦታ ወደ ላይ፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት ፍራፍሬዎች በላያቸው ላይ ያሉባቸው የተዋቡ ዛፎች ነበሩ፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት አበቦችን አየሁ፡፡ ብዙ ዓይነት ወፎች ማየት እችል ነበር-አንዳንዶቹ እኛ አይተናቸው የማናውቃቸው ናቸው፡፡ አ፥ የገነት ውበት የማይገለጽ ነው!

እስከ ሌላ ስፍራ ድረስ ወደ ላይ ወጣን፡፡ የክብር ጩኸቶች ይሰሙኝ ነበር፡፡ ረዥም፥ ነጭ ልብስ የለበሰ መልአክ በበሩ አጠገብ ቆሞ ነበር፡፡ ከጠረጴዛ (ዴስክ) ጀርባ ነበር፡፡ ከዴስኩ ውስጥ ወርቃማ መጽሐፍ አወጣና ለሌላ መልአክ ሰጠው፡፡

መጽሐፉን የተቀበለው መልአክ ከፈተው፥ አንጸባራቂ፥ አብረቅራቂ የብርሃን ጨረሮች ከውስጡ ወጥተው መብለጭለጭ ጀመሩ፡፡ እኩል በአንድ ጊዜ የሚለቀቁ ርችቶችን አስታወሰኝ፡፡

## ሰማያዊ ዳግም ኅብረት (ሰማያዊ ዳግም አንድነት)

ንጉሥ ዳዊት ትናንሽ ልጆች በማንኛውም ምክንያት ያለጊዜያቸው ሲሞቱ ምን እንደሚከሰት በደንብ ያውቅ ነበር፥ ነፍሳቸው ወደ ገነት ነው የምትሄደው፥ አንድ ቀን ከአማኝ ቤተሰቦቻቸው ጋር በሚገናኙበት በዚያ፡፡ ያለጋብቻ ከቤርሳቤህ በዝሙት የወለደው ጨቅላ ልጁ ሲሞት፥ ዳዊት ከልቡ ንስሐ ገባ ያሑዋሕም ይቀር እንዳለው እርግጠኛ ነበር፡፡ (መዝሙር 32፡5) ምክንያቱም ዳዊት ለዘላለም ከያሑዋሕ ጋር እንደሚያሳልፍ በማወቁ ሰላምን አግኝቷል (መዝሙር 23፡6)፡፡ እናም ጨቅላ ልጁን ዳግም እንደሚያይ (2ኛ ሳሙኤል 12፡23)፥ ቤርሳቤህን በኀዘኗ ጊዜ ሊያጽናናት ችሎ ነበር፡፡

የታሪኩ መጽሐፍ ቁዱሳዊው ገለጻ ይኸውላችሁ፡-

*ዳዊትም ናታንን፡ ያሑዋሕን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን፡ ያሑዋሕ ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፤ አትሞትም። ነገር ግን በዚህ ነገር ለያሑዋሕ ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል አለው። ዳዊትም ስለ ሕፃኑ ያሑዋሕን ለመነ፤ ዳዊትም ጾመ፥ ገብቶም በመሬት ላይ ተኛ። የቤቱም ሽማግሌዎች ተነሥተው ከምድር ያነሡት ዘንድ በአጠገቡ ቆሙ፤ እርሱ ግን እንቢ አለ፥ ከእነርሱም ጋር እንጀራ አልበላም። በሰባተኛውም ቀን ሕፃኑ ሞተ። የዳዊትም ባሪያዎች፡ ሕፃኑ በሕይወት ሳለ ብንነግረው አልሰማንም፤ ይልቁንስ ሕፃኑ እንደ ሞተ ብንነግረው እንዴት ይሆን? በነፍሱ ክፉ ያደርጋል ብለው ሕፃኑ እንደ ሞተ ይነግሩት ዘንድ ፈሩ። ዳዊትም ባሪያዎቹ በሹክሹክታ ሲነጋገሩ ባየ ጊዜ ዳዊት ሕፃኑ እንደ ሞተ አወቀ፤ ዳዊትም ባሪያዎቹን። ሕፃኑ ሞቶአል? አላቸው። እነርሱም፡ ሞቶአል አሉት። ከምድር ተነሥቶ ታጠበ፥ ተቀባም፥ ልብሱንም ለወጠ፤ ወደ ያሑዋሕም ቤት ገብቶ ሰገደ። ወደ ቤቱም መጣ። እንጀራ አምጡልኝ አለ፤ በፊቱም አቀረቡለት፥ በላም። ባሪያዎቹም፡ ይህ ያደረግኸው ነገር ምንድር ነው? በሕይወት ሳለ ስለ ሕፃኑ ጾምህና አለቀስህ፤ ከሞተ በኋላ ግን ተነሥተህ እንጀራ በላህ አሉት። እርሱም፡ ሕፃኑ ሕያው ሳለ፡ ያሑዋሕ ይምረኝ፥ ሕፃኑም በሕይወት ይኖር እንደ ሆነ ማን ያውቃል? ብዬ ጾምሁ አለቀስሁም። አሁን ግን ሞቶአል፤ የምጾመው ስለ ምንድር ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን? እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም አለ። ዳዊትም ሚስቱን ቤርሳቤህን አጽናናት፥ ወደ እርስዋም ገባ፥ ከእርስዋም ጋር ተኛ፤ ወንድ ልጅም ወለደች፥ ስሙንም ሰሎሞን ብሎ ጠራው። ያሑዋሕም ወደደው፤* (2ኛ ሳሙኤል 12፡13-14፤ 16-24)

የ**ያሑዋሕ** መልአክ እንዲህ አለኝ፡- "ከመወለዱ ጀምሮ አንድ ሕፃን ዘላለማዊ ነፍስ ነው፥ አንድ ሕፃን ውርጃ ቢፈጸምበት ወይም ቢጨነግፍ አልያም ደግሞ በሆነ ምክንያት ቢሞት፥ **ያሑዋሕ** ስለሁኔታው ያውቃል፡፡ መላእክቱን ስለእነርሱ አዝዟቸዋል፡፡

"ትንሿን ነፍሳቸውን ወደ ገነት እናመጣታለን፥ እናም **ያሑዋሕ** ፍጹም ያደርጋቸዋል፡፡ ሕፃን ውርጃ ይፈጸምበትም በተፈጥሮ ይሙትም ለውጥ የለውም፡፡ ታላቅ በሆነው በ**ያሑዋሕ** እጅ ውብና ሙሉ ተደርጎ ይሠራል፡፡

"የሕፃኑ ቤተሰቦች በ**ክርስቶስ ኢየሱስ** በቅድስና ቢኖሩ፥ ወደ ገነት ሲመጡ፥ ከውዶቻቸው ጋር ዳግም ይገናኛሉ፡፡ በክብር ደጃፎች ላይ ያገኟቸዋል!"

-----------------------------------------------------------

# በዙፋኑ ዙሪያ ማምለክ

አሁን፥ የገነት ራዕዬን በመጽሐፍ ስለመጻፍ እድል **ያሑዋሕ**ን አመሰግናለሁ፡፡ ያለማቋረጥ በልቤ ውስጥ ይነዳል፡፡ ብዙ ሰዎች ይህን ምስክርነት እንድጽፍና ለሌሎች **ያሑዋሕ** የሰጠኝን የገነት ራዕይ እንዳካፍል አበረታተውኛል፡፡

ባገለገልኩባቸው ብዙ ቤተክርስቲያኖች፥ የገነት ራዕዬን አካፍያለሁ፥ በሲኦል የነበረኝንም ገጠመኝ እንዲሁ፡፡

በገነት ያየኋቸውን አንዳንድ ራዕዮች ለእናንተ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ገነት የእውነት እንደሆነ እንድታውቁ እፈልጋለሁ፡፡ ከእናንተ በፊት ወደ ገነት የሄደ፥ ያጣችሁት ወዳጅ ቢኖር፥ ያ ሰው በክብር ደጃፎች ላይ ይጠብቃችኋል፡፡ ልባችሁን ላበረታታ እፈልጋለሁ፥ ምክንያቱም በ**ኢየሱስ ክርስቶስ** የተባረከ ተስፋ ስላለን ነው፡፡ በዚያ ስፍራን ሊያዘጋጅልን ወደ ገነት ሄዷል፡፡

በገነት ያየኋቸው መላእክት ግዙፍና ኃያል ይመስላሉ! አንጸባራቂ፥ የሚያብለጨልጩ፥ ብዙ የብርሃን መጠኖችን የሚረጩ ልብሶችን ለብሰዋል፡፡ ኃያልና ግልጽ ነበሩ፡፡ አዕምሮአቸው **ያሑዋሕ**ን በመታዘዝ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በእንቁዎቹ ደጃፎች ላይ ያየኋቸው ታላላቅ መላእክት ጠባቂ መላእክት እንደነበሩ ለእኔ ግልጽ ነበር፡፡

ከመላእክቱ አጠገብ ያሉትን ሰይፎች ሳይ፥ "*ክብር ለ**ያሑዋሕ** ይሁን! ሃሌሉያ! **ያሑዋሕ** በእርግጥም ልጆቹን ይጠብቃል*" ብዬ አሰብሁ፡፡

## የ**ያሑዋሕ** መላእክት

ታውቃላችሁ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመላእክት በብዛት ያወራል፥ ስለመላእክት የሚጠቅሱ ብዙ ክፍሎች አሉት፡፡ አንዳንዴ የ**ያሑዋሕ** ቃል ደጋግሞ የሚያረጋግጣቸውን ነገሮች ቸል ብለን ለማለፍ መሞከራችን ያስገርማል፡፡ ለአንድ ሰው መገለጥ (ራዕይ) ሲሰጥ፥ በጉዳዩ ላይ የበለጠ ብርሃንን ያበራል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለመላእክት ከሚጠቅሳቸው ውስጥ የተወሰኑ ምሳሌዎች እነሆ፡

> *በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለአንተ ያዝዛቸዋልና፤ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል።* (መዝሙር 91፡11-12)
>
> *እርሱም አለኝ። አካሄዴን በፊቱ ያደረግሁለት ያሑዋሕ መልአኩን ከአንተ ጋር ይልካል፥ መንገድህንም ያቀናል። ለልጄም ከወገኖቼ ከአባቴም ቤት ሚስትን ትወስዳለህ፤* (ዘፍጥረት 24:40)
>
> *ሌላም ብርቱ መልአክ ደመና ተጐናጽፎ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤ በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ነበረ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ እግሮቹም እንደ እሳት ዓምዶች ነበሩ፥* (ራእይ 10:1)
>
> *ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች።* (ራእይ 18:1)
>
> *ከሙታንስ ሲነሡ በሰማያት እንዳሉ መላእክት ይሆናሉ እንጂ ሊያገቡም፥ ሊጋቡምም።* (ማርቆስ 12:25)
>
> *ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአክ ታየው።* (ሉቃስ 22:43)
>
> *ኩቶ ለማን ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?* (ዕብራውያን 1:14)
>
> *እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በያሑዋሕ መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።* (ሉቃስ 15:10)

በድጋሚ በገነት ደጅ እንድገባ ተፈቅዶልኝ ነበር፥ እናም አስታውሳለሁ በዚያ ባለው የሰላምና የሀሴት ስሜት ተሞልቼ ነበር፡፡ ኦ፥ የከበረው ዝማሬና ውዳሴ! ቅዱሳን፥ ማንም ሰው በደንብ አድርጎ ይገልጸዋል ብዬ አላስብም፥ ምክንያቱም መሬት መቼም ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ደስታ ተሰምቷት አያውቅም፡፡ ከኤደን ጀምሮ፥ ምድር ፈጽሞ ሰላምን፥ ሀሴትንና በገነት ያለውን እረፍት ተለማምዳ አታውቅም፡፡

በገነት ምንም በሽታ የለም፡፡ በገነት የአካል ጉዳተኞች ወንበር (ዊልቸር) የለም፡፡ በገነት አካል ጉዳተኞች የሉም፡፡ በገነት ምንም ህመም የለም፡፡ ሁሉም ፍጹምና ያማረ ነው፡፡ ምንም ሙስና ያለበት የለም፡፡ ምንም ውሸት የለም፡፡ ኃጢአት የለም፥ ምክንያቱም ያሑዋሕ አንድ ኃጢአት እንኳ ወደ ገነት እንዲገባ አይፈቅድም፡፡

## ታላቁ ድንቅ

መልአኩ እየመራኝ፥ ቶሎ ቶሎ ሄድን፡፡ ከህይወት ወንዝ አጠገብ በበቀሉ ብዙ የፍራፍሬ ዛፎች አጠገብ አለፍን፡፡ እያንዳንዳቸው በፍራፍሬ የታጨቁ ነበሩ፡፡

መንገዳችንን ስንቀጥል፥ እኛም የሙዚቃው አካል ወደመሆን የመጣን ይመስላል፡፡ በገነት በሁሉም ጊዜ፥ ዜማ ይሰማኝ ነበር፥ ደግሞም ሁል ጊዜ አዲስ ነው፡፡ የውዳሴ ዜማ ለያሑዋሕ ክብርና ውዳሴ በቀጣይነት ሲወጣ ሰማሁ፡፡

የያሑዋሕ መልአክ እንዲህ አለኝ: "*የያሑዋሕን አምልኮ ለማየት ወደ ያሑዋሕ ዙፋን እየሄድን ነው፡፡*" በመንገዱ ላይ፥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከመላዋ ገነት እየመጡ ነበር፡፡ **የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ**ን ለማምለክ እየሄዱ ነው፡፡

## አምልኮ በመንግሥተ ሰማይ

መንገዳችንን ስንቀጥል፥ መቶዎቹ ወደ ሺሆች የተለወጡ መሰለ፥ ሺሆቹ ደግሞ ወደ የማይቆጠር ሠራዊት፡፡ ከተለያዩ የገነት ክፍሎች መጡ፡፡ ዮሐንስ ወደ ገለጸው ትልቅ የትዕይንት ስፍራ የሚመስል አካባቢ መጣን፡፡

> *ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፥ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ፤ ተቀምጦም የነበረው በመልኩ የኢያስጲድንና የሰርዲኖን ዕንቍ ይመስል ነበር። በመልኩም መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ። ዙሪያውም ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር። ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት*

*መብራቶች ይበሩ ነበር፥ እነርሱም ሰባቱ የያሑዋሕ መናፍስት ናቸው። በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ። ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፡- ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል፤ እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።* (ራእ. 4፡2-5፤ 10-11)

እንዲሁም ደመናዎቹ! እጅግ የተዋቡ ደመናዎች በዙፋኑ ውስጥና ዙሪያ ይንሳፈፉ ነበር፡፡ አቶሚክ ቦምብ ሲፈነዳ እንደሚፈጥረው የጅብ ጥላ የመሰለ ቅርጽ መስለው፥ እያንዳንዱ ደመና በክብርና በተዋቡ ቀለማት የተደባለቁ ነበሩ፡፡

ከነዚህ ሁሉ በላይ አስደናቂ ደመና ቦ ቅርጽ ሠርቶ ይገኛል፡፡ የያሑዋሕን ኃይል ጥልቅት ለማሰብ ያማይቻል ነገር ነው፡፡

በደመናዎቹ ውስጥ ያየሁት የሰው ምስል የያሑዋሕ ምሳሌ እንደሆነ በልቤ አውቄ ነበር፡፡

*ያሑዋሕም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በያሑዋሕ መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።* (ዘፍ.1.27)

ያሑዋሕ የምድርን ትቢያ ወስዶ ሰውን ሠራ፡፡ የነበረውን የያሑዋሕ ህልውና አስቡት፤

*ያሑዋሕ አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።* (ዘፍ.2:7)

ከዚያም አዳም ብቻውን ስለነበረ - “*አዳምም ለእንስሳት ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው፤ ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር።*” (ዘፍ. 2፡20) ያሑዋሕ ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ከተተው፡፡ ያሑዋሕም የአዳምን ጎን ከፈተና፥ አንድ የጎድን አጥንት ወሰደ፥ ከዚያም ከእርሱ ሴትን አዘጋጀ፡፡ ያሑዋሕ ሔዋንን ሠራት፥ የአዳም የህይወት ዘመን አጋርና ጥንድ፥ እንዲህ በያሑዋሕ ምሳሌ የተሠራች፡፡ (ዘፍ. 1፡27) ሰው በያሑዋሕ መልክ በመፈጠር ምን ዓይነት ክብር ነው የተሰጠው!

## ለንጉሡ ተዘጋጁ

የገነት አምልኮ ምስክርነቶች የያሑዋሕን ውበትና ቅድስና ያሳያሉ፡፡ ወደ መሰብሰቢያ ቦታ ስንደርስ፥ ሰዎችንና መላእክትን በየቦታው ማየት እችል ነበር፡፡ ሁሉም ነገር በስርዓት የሚደረግ በመሆኑ ተገርሜ ነበር፡፡ በየቦታው፥ ሰዎችና መላእክት ያሑዋሕን ያወድሳሉ፡፡

የህይወት ወንዝ ከያሑዋሕ ዙፋን ወጥቶ ይፈስሳል፡፡ እንደ ብርጭቆ ባሕር ነበር፥ ኩልል (ጥርት) እንዳለ ባሕር፥ ነገር ግን ይፈስ ነበር፡፡

ከዚያም ቅዱሳን፥ በድጋሚ ፈረሶችን አየሁ፡፡ ትልቅ፥ ነጭ፥ አስገራሚ የሆኑት ፈረሶች ከእምነበረድ የተሠሩ ነው የሚመስሉት፡፡ የተዋቡና በአንዳቸውም ላይ ምንም ዓይነት እንከን የሌለባቸው ነበሩ፡፡ ያጌጡ ነበሩ፥ ልክ እንደ ቼዝ ጠጠሮች (chess pieces)፥ ነገር ግን የእውነት አካላዊ ነበሩ፡፡ በፈረሶቹ ጀርባ ላይ ያሉት ብርድልብሶች በወርቅ ጥለቶች ጠርዛቸው ያጌጡ ነበሩ፡፡ በአፋቸውም ውስጥ ወርቃማ ልጓም ነበረ፡፡ በእግሮቻቸውና በጭራቸው ላይ ጭምር ጌጦች ነበሩ፡፡ እነዚህ ፈረሶች በዙፋኑ ፊት በተጠንቀቅ ቆመዋል፡፡

በዙፋኑ ፊት የቆሙት መላእክት መለከትና ባለቀንድ የዜማ እቃዎች በእጆቻቸው እንዳሉ አስተዋልሁ፡፡ እንደፈሳሽ የሆነው፥ የሚያበሩት ልብሶቻቸው በወርቅ ያጌጡና በትላልቅ የከበሩ ቀያይ ድንጋዮች በተለያየ ዓይነት እጅግ የበዙ ድንጋዮች አሸብርቋል፡፡

በድንገት፥ ብዙ የዜማ እቃዎችን አየሁ፡፡ ልታዩአቸው ከምትገምቷቸው በላይ በጣም አስደናቂ መሣሪያዎች ነበሩ፡፡ ኦ፥ የገነት ውበት! ብዙ በገናዎች ነበሩ፡፡ በእነዚህ የዜማ እቃዎች ላይ ማን እንደተሾመ ለማየት ፈለግሁ፡፡

“ኦ፥ የገነት ውበት! ሃሌሉያ!” ብዬ አሰብሁ፡፡

## ለማምለክ መጠራት

ከዚያም ቅዱሳን፥ *መንፈስ ቅዱስ* አንድ ነገር በግልጽ አሳየኝ፡፡ በተሰበሰቡት ፈረሶች መሀከል የነበረችው ሴት ተነሥታ ቆመች፡፡ ከዚያም በዙፋኑ ፊትለትፊት የነበሩት መላእክት፥ እያንዳንዱ በተርታ በአጠገቡ ያለውን መለከቱን ወይም ቀንደመለከቱን አንሥቶ መንፋት ጀመረ፡፡ እነዚህን ቀንደመለከቶች ሲነፉ-ኦ፥ ወደ ላይ የወጣው የሀሴትና የከፍተኛ ውዳሴ ድምጽ! አንድ ሰው በገነት ጮክ ብሎ አወጀ፡

*አሁን የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታን በምድር ላሉ ሰዎች ስለከበረ ሥራዎቹና የከበረ ኃይሉ የምናመልክበት ጊዜ ነው፡፡*

*ከፍ ያለ ውዳሴ የሚሰጥበት ጊዜ ነው፥ በመዝሙርና በሽብሸባ እርሱን ለማምለክ፥ በዜማ እርሱን ለማምለክ፥ እንዲሁም ስለመልካምነቱ እርሱን ለማምለክ፡፡*

*እርሱ አምላክ ነው፡፡ እርሱ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ነው፡፡ እርሱ የሰው ልጆች አዳኝ ነው፡፡*

እነርሱም እነዚህን ነገሩች ሲያውጁ፥ ቅዱሳን፥ መለከቶቹ እየተሰሙ ነበር! ከዚያም ጥቅልሉን ሲያነብ የነበረው መልአክ አቆመ፥ ከዚያም ምልክት ተሰጠ፡፡

ወዲያውኑ፥ እነዚያ አስደናቂ ፈረሶች ሁሉም በጉልበታቸው ሰገዱ፡፡ አንገቶቻቸው ሁሉ በመደዳ ለጌታ ስም ውዳሴን በመስጠት ዝቅ አሉ፡

> *ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥*
>
> (ፊልጲስዩስ 2:10)
>
> በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ፡- በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ። (ራእ.5:13)

ከዚያም ፈረሶቹ በጌታ ፊት መሽከርከርና በኋላ እግሮቻቸው መፈናጠር (መቆም) ጀመሩ፡፡ ያሑዋሕን ለማግነንና ለማወደስ ለማምለክም የተለያዩ ብዙ ነገሮችን አደረጉ፡፡ ኦ፥ ብቻ ብታዩት ኖሮ! እናም ያሑዋሕ ለእርሱ ባቀረቡት አምልኮ ደስ ተሰኝቶ ነበር፡፡

## ለውዳሴ መነቃቂያ

ቅዱሳን፥ ያሑዋሕ(እግዚአብሔር) ውዳሴያችንን ምን ያህል እንደሚወድ ያስተዋልነው አይመስለኝም፡፡ በፈተናዎች፥ የልብ ህመምና ኀዘን ውስጥ ስናልፍ፥ ያሑዋሕ እንድናወድሰው ይፈልጋል፡፡ ልናወድሰው ይገባል፥ ስለኀዘኑ ወይም ስለፈተናው አይደለም፥ ነገር ግን ስለምንወደው ነው፡፡

ስናወድሰው፥ ለእራሳችን ሳይሆን ስለእርሱ ስንል እንዲህ ልናደርግ ይገባል፡፡ ለእኛ ስላደረጋቸው ታላላቅ ሥራዎች ስናወድሰው፥ ትኩረታችንን ከራሳችን ወደ ያሑዋሕ እናዞራለን፡፡ ወደ ውዳሴ በመግባት ሂደት ውስጥ፥ ከፊታችን ያሉትን ችግሮች ሊፈታቸው የሚችለው እርሱ ብቻ እንደሆነ ወደ ማስተዋል እንመጣለን፥ እናም እኛን ለመርዳት እንደሚመጣ ልናምነው እንችላለን፡፡ ስለዚህ፥ ጌታን ስናወድስና ስናመልከው የእውነትም ተጠቃሚዎች ልንሆን እንችላለን፡፡

## የውዳሴ ክብሮች

በዚያ ሰዓት፥ ሰማያውያን መሳሪያ ተጫዋቾች ሁሉ መጫወት ጀመሩ፥ ከዚያም ሌሎች የአምልኮ ቡድኖች መጡ፡፡ ሺኾች ድምጾች ለኢየሱስ ክብርና ውዳሴ ዘመሩ፡፡ የከበሩ ጩኸቶች ድምጽ ወጣ፡፡ በመላዋ ገነት ደወል ነበር፡፡ ለሰዓታት በሚመስል፥ ውዳሴ ለያሑዋሕ ያቃጭል ነበር!

ለያሑዋሕ(እግዚአብሔር) የሆነን ውዳሴ መስማትና በዚህ ውዳሴ መሀል መሆን ምንኛ ያማረ ነው! በዚያ፥ በሚያስተጋባው፥ አስደናቂው ድምጽ፥ መሀል ምድር ሩቅ የሆነች መሰለችኝ፡፡ ኀዘኖችና ችግሮች እጅግ የራቁ መሰለኝ፡፡ የሲኦል አስፈሪ ነገሮች እጅግ የራቁ መሰለኝ፡፡

## ከያሑዋሕ የተሰጠኝ ሥራ

ሆኖም ግን፥ ለያሑዋሕ የሆነ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ በውስጤ ለራሴ አውቅ ነበር፡፡ የያሑዋሕ መልአክ ነካኝ፥ እናም ብርታት ወደ ውስጤ መጣ፡፡

እንዲህ አለኝ: "ልጅ፥ ያሑዋሕ እነዚህን ነገሮች እንድታዩ የፈቀደልሽ እንድትናገሪያቸውና እንድትመዘግቢያቸው ነው፡፡ መገለጦችና ራዕዮች እንዲሁም ህልሞች ለአንቺ የተሰጡሽ በምድር ያሉ ሰዎች 'ያሑዋሕ ለሚወዱትና ትእዛዙን ለሚጠብቁት … ለእነርሱ ያዘጋጀውን' እንድታሳውቂ ነው፡፡" (ዘዳግም 7:9፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 2:9)

ከዚያ ቅዱሳን፥ የያሑዋሕን ድምጽ ሰማሁ! የንግግሩ ድምጽ ብቻ በልዩ ስሜት አጥለቀለቀኝ፡፡ ድምጹ እንደነጎድጓድ ነበር፥ ነገር ግን የሚለውን እረዳው ነበር፡፡

በፊቴ ተደፍቼ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶችን ጌታ ማምለክና ማወደስ ጀመርሁ፡፡

## ሰማያዊ ጥቅሶች

ወደ ምድር ተመልሼና ያሑዋሕ ያሳየኝን ነገሮች እያሰላሰልሁ ሳለ፥ በያሑዋሕ ቃል ውስጥ ተመለከትሁ፡፡ በገለጥሁበት ቦታ ሁሉ ስለገነትና ስለያሑዋሕ ግርማዊነት የማነብ መሰለኝ፡፡

ከነዚያም ጥቂቶቹን ጥቅሶች ላካፍላችሁ እፈልጋሁ:

> *አንተ ብቻ ያሑዋሕ ነህ፤ ሰማዩንና የሰማያት ሰማይን ሠራዊታቸውንም ሁሉ፥ ምድሩንና በእርስዋ ላይ ያሉትን ሁሉ፥ ባሕሮቹንና በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ፥ ፈጥረሃል፥ ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል፤ የሰማዩም ሠራዊት ለአንተ ይሰግዳሉ።* (ነህ.9:6)
>
> *ያሑዋሕ በሰማያት ከፍ ከፍ አይልምን? ከዋክብትም እንዴት ከፍ ከፍ እንዳሉ ተመልከት። … እንዳያይ የጠቈረ ደመና ጋርዶታል፤ በሰማይ ክበብ ላይ ይራመዳል ብለሃል።* (ኢዮ.22:12)
>
> *ያሑዋሕ ከመቅደሱ ከፍታ ሆኖ ተመልክቶአልና፥ ከሰማይ ሆኖ ምድርን አይቶአልና፤* (መዝ.102:19)
>
> *ያሑዋሕ ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።* (መዝ.103:19)
>
> *የያሑዋሕን ስም ያመስግኑ፤ ስሙ ብቻውን ከፍ ከፍ ብሎአልና፥ ምስጋናውም በሰማይና በምድር ላይ ነው።* (መዝ.148:13)
>
> *ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው ያሑዋሕ ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥* (ዕብ.12:22)

---

# ቅዱሳን ፍጥረታት በገነት

ይህ በእኔ የደረሰ እውነተኛ ገጠመኝ ነው፡፡ አሁንም በድጋሚ፥ የጌታ መልአክ ወደ እኔ መጣና እንዲህ አለኝ: "*እነሆ የአምላክሽ ክብር፡፡*"

በቅጽበት ገነት ወዳረፈችበት ስፍራና ወደ ገነት ደጆች ተወሰድሁ፡፡ እያንዳንዱ መግቢያ በውስጡ የእደጥበብ ሥራ ባለው በተዋበ ፈርጥ የተሠራ ነበር፡፡ የገነት ውበት የሚያስደምም ነው! የህይወትን ወንዝ አለፍን፥ እናም በወንዙ ዳርቻዎች ሰዎች ሲጮሁና ያሑዋሕን ሲያወድሱ ይሰማኝ ነበር፡፡ በራእይ ምዕራፍ አራት ላይ እንደተገለጸው ወደ ያሑዋሕ ዙፋን ፊት ተወሰድሁ፡፡ ኦ፥ ምን ዓይነት ጩኸት ምን ዓይነት አምልኮ!

ቅዱሳን፥ የያሑዋሕን ዙፋን በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው ሆኖ አየሁት፡፡ በዙሪያው ቀስተደመና አለ፡፡ በክብር ደመናና

በያሑዋሕ ክብር ብርሃን ተሸፍኗል፡፡ ድምጾችን ሰማሁ፥ መብረቆችን አየሁ፥ እንዲሁም ነጎድጓድንም ሰማሁ፡፡ የያሑዋሕን ኃይል መለኮታዊ መገለጥ አየሁ!

> *ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፥ እነርሱም ሰባቱ የያሑዋሕ መናፍስት ናቸው። በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።* (ራእይ 4:5-6)

ስመለከት፥በዙፋኑ ፊት የበዙትን የመላእክትን ድምጾች ሰማሁ፡፡ በዚያ የነበሩት የመላእክት ቁጥር የማይገመት ነበር፡፡ ከዚያም የሰማይ እንስሳትንና ሽማግሌዎቹን አየሁ፡፡ አራቱ እንስሳትና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ነበሩ፡፡ ይህ ትእይንትም እንዲሁ በዮሐንስ ራዕይ ላይ ተገልጿል፡

> *አየሁም፥ በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም አእላፋት ጊዜ አእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር፥* (ራእይ 5:11)

> *መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለያሑዋሕም እየሰገዱ፡* (ራእይ 7:11)

## አራቱ እንስሳት

ወደ ያሑዋሕ ዙፋን ባደረግሁት በዚህኛው ጉዞዬ፥ በያሑዋሕ ዙፋን ፊት ያሉትን አራቱን እንስሳት አየሁ፡፡ እነዚህ በዙፋኑ ዙሪያ ያየኋቸው እንስሳት በያሑዋሕ ቃል ውስጥ የተጻፉት ናቸው፡፡

ሁሉም ሰማያውያኑ እንስሳት ትላልቅ ዓይኖች ነበሯቸው፥ በፊት ለፊታቸውና በጀርባቸው፡፡ ከፊታቸውም ከጀርባቸውም ማየት ይችላሉ፡፡ በጣም ግዙፍ ነበሩ በምድርም እንደ እነርሱ ዓይነት አላየሁም፡፡

እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አላቸው፡፡ አንዱ የአንበሳ መልክ አለው፡፡ ሁለተኛው የጥጃ መልክ አለው፡፡

ሦስተኛው እንስሳ የሰው ገጽ አለው፡፡ ከቻላችሁ አስቡት፥ ባለ ስድስት ክንፍ እጅግ ረዥም እንስሳ፡፡ የሰው ፊት አለው፡፡ አራተኛው እንስሳ እንደ ሚበርር ንስር ነበር፡፡

እነዚህ አስደናቂ ፍጥረቶች ያለማቋረጥ “ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ጌታ ሁሉንቻይ አምላክ” እያሉ ይጮኻሉ፡፡

ከዚህ በፊት በማንኛውም መልኩ ሊመስላቸው የሚችል ፍጥረት አይቼ አላውቅም፥ ለእኔ እንግዳ ነው የሆኑብኝ፡፡ ቢሆንም፥ ያሑዋሕ እነዚህን በገነት ያሉ ቅዱሳን ፍጥረታት እንደፈጠራቸው አውቃለሁ፡፡ ያሑዋሕን ስለታላቅ አደራረጎቹና ስለታላቅ ኃይሉ አወድሰዋለው፡፡ ያሑዋሕ ድንቅ አምልክ ነው! እነዚህን ፍጥረታት ሁሉንቻዩን ያሑዋሕ ማምለክና ማወደስ ሲጀምሩ አየኋቸው፡፡

ይህን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ፥ እነዚህን ሰማያዊያን የያሑዋሕ ፍጥረታት በራእዬ ውስጥ ካየሁ በኋላ፥ ስለነርሱ አጠናሁና ስላየሁት ነገር የዮሐንስን አስደናቂ ገለጻ አገኘሁ፡፡ እንዲህ ነው ዮሐንስ የገለጻቸው፡

> *በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ። ፊተኛውም እንስሳ አንበሳን ይመስላል፥ ሁለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስላል፥ ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው፥ አራተኛውም እንስሳ የሚበረውን ንስር ይመስላል። አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው፥ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፤* (ራእይ 4:6-8)

## የአራቱ እንስሳት ተግባሮች

መጽሐፍ ቅዱስ ስለእነዚህ እንስሳትና ስለተግባራቸው ይነግረናል፡፡ ያለማቋረጥ ለያሑዋሕ ውዳሴና ክብርን ይሰጣሉ፡፡ ከሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ጋር፥ ዋና ሥራቸው ያሑዋሕን ማምለክ ነው፡

*አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው፥ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፤ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም። እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ፥ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፡- ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል፡ እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።* (ራእ. 4፡8-11)

*መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለያሑዋሕ ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።* (ራእ. 5፡9-10)

*አየሁም፥ በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም እእላፋት ጊዜ እእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር፥ በታላቅም ድምፅ፡- የታረደው በግ ኃይልና ባለ ጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ። በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ፡- በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ። አራቱም እንስሶች፡- አሜን አሉ፥ ሽማግሌዎቹም ወድቀው ሰገዱ።* (ራእ. 5፡11-14)

*ሀያ አራቱም ሽማግሌዎችና አራቱ እንስሶች በፊታቸው ተደፍተው በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለያሑዋሕ፡- አሜን፥ ሃሌ ሉያ እያሉ ሰገዱለት። ድምፅም፡-ባሪያዎቹ ሁሉ እርሱንም የምትፈሩት ታናናሾችና ታላላቆች ሆይ፥ አምላካችንን አመስግኑ ሲል ከዙፋኑ ወጣ። እንደ ብዙ ሕዝብም ድምፅ፥ እንደ ብዙ ውኃዎችም ድምፅ፥ እንደ ብርቱም ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ድምፅ ሰማሁ እንዲህ ሲል፡- ሃሌ ሉያ፤ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሦአልና።* (ራእ. 19፡4-6)

ሌሎችም የአራቱ እንስሳት ተግባራት በራዕይ ላይ ተገልጸዋል፡

*መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፥ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።* (ራእ. 5፡8)

*በጉም ከሰባቱ ማኅተም አንዱን በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ከአራቱም እንስሶች አንዱ ነጐድጓድ በሚመስል ድምፅ፡- መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ።* (ራእ. 6፡1)

*ሰባቱንም መቅሠፍት የያዙ ሰባቱ መላእክት ከመቅደሱ ወጡ፤ ከተልባ እግርም የተሠራ ጥሩ የጌጥ ልብስ ለበሱ ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጠቁ። ከአራቱም እንስሶች አንዱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የሚኖር የያሑዋሕ ቍጣ የሞላባቸውን ሰባት የወርቅ ጽዋዎች ለሰባቱ መላእክት ሰጣቸው። ከያሑዋሕም ክብርና ከኃይሉ ጢስ በመቅደሱ ሞላበት፥ የሰባቱ መላእክት ሰባቱ መቅሰፍት እስኪፈጸሙ ድረስ አንድ እንኳ ወደ መቅደሱ ይገባ ዘንድ አልቻለም።* (ራእ. 15፡6-8)

የማይቆጠሩ ብዙሃን መላእክት ጌታን ማምለክ ሲጀምሩ አየሁ፡፡ በዙፋኑ ዙሪያ ያሉት ሽማግሌዎች ሲቀላቀሉ የማይረሳን ትዕይነት ሰማሁ ተለማመድሁም፡፡ እኔ ራሴ ንጉሡን በማምለክ ተቀላቀልሁ፥ "ኦ፥ የሁሉንቻዩን አምላክ ኃይል ማየት እንዴት የከበረ ነው!" ብዬ እያሰብሁ፡፡

---

# የመንግሥተ ሰማይ ክብሮች

ኢየሱስ ክርስቶስ ገነትን ሲገልጥልኝ፥ ለአስር ጉብኝቶች ያህል በሁሉንቻዩ ያሑዋሕ ኃይል ወደዚያ ተወስጃለሁ፡፡ ይህ የሆነው ሲኦልን ካሳየኝ በኋላ ወዲያው ነበር፡፡

መለኮታዊ ጉብኝቱ የጀመረው በፋሲካ ወቅት ነበር፡፡ ኢየሱስ ከሌሊቱ 8 ሰዓት እስከ 11 ሰዓት ድረስ፥ እርሱን የገፉት (ያልተቀበሉት) ፍጻሜያቸው ምን እንደሆነ እያሳየኝ በየምሽቱ ይገለጥልኝ ነበር፡፡ ገነትን ከማየቴ አስቀድሞ፥ ወደ ምድር እንብርት

ወሰደኝና የሙታንን መገኛ (ማደሪያ) አሳየኝ፡፡ “የሲኦል መለኮታዊ መገለጥ” (Devine Revelation of Hell) የሚል መጽሐፍ ጽፌአለሁ፥ በዚያ ውስጥ በሲኦል ስለነበረኝ ገጠመኝ ጽፌአለሁ፡፡ ወደ ፍርኀት ጥልቅ ከተደረጉ ከነዚያ ሠላሳ ጉዞዎች በኋላ፥ ለአስር ቀናት ጌታ ገነትንና ክብሯን አሳይቶኛል፡፡ በተጨማሪም፥ ከጌታ ሌሎች ብዙ ጉብኝቶች ነበሩ፡፡

ይህ ለእኔ የሆነ እውነተኛ ገጠመኝ ነው፡፡ የህያው አምላክ መንፈስ እየነገርኋችሁ ያለውን ሁሉ ገልጾልኛል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በእነዚህ ጉዞዎች ሲወስደኝ፥ በጣም ተደንቄ ነበር ምክንያቱም በገነት፥ ለቅሶ የለም፥ ሞት የለም፥ መሞት የለም፥ ሀዘን የለም፡፡ በገነት ሀሴት፥ ሰላም፥ ደስታ ነው ያለው፥ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በየቦታ አሉ፡፡

እንዲሁም በሺሆች በዚያ ባሉት የያሑዋሕ መላእክት ተደንቄያለሁ፡፡ አንዳንዶቹ ክንፎች አሏቸው፤ አንዳንዶቹ የላቸውም፡፡

በሁሉም ጉዞዎቼ መላእክቱ ሁልጊዜም በሥራ የተጠመዱ እንደሆኑ አየሁ፡፡ መላእክቱ ያለማቋረጥ ሥራዎችን እየሠሩና ትናንሽ (ዝርዝር) ነገሮችን እንኳን በትኩረት ይፈጽማሉ፡፡ እያንዳንዱ መልአክ የራሱ የሆነ ተግባር የተለየ ሥራ እንዳለው ነው የታየኝ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ግዴታቸውን በደስታ እየፈጸሙ ሁልጊዜ ያሑዋሕን እያወደሱ ሥራቸውን ይሠራሉ፡፡

ሁሉም መላእክት ያለማቋረጥ በተመደበላቸው ሥራ ተጠምደዋል፡፡ ለምሳሌ፥ አዲስ ነፍሶች ወደ ገነት ሲመጡ፥ መላእክት ይቀበሏቸውና ወዲያው በሕይወት ውኃ ወንዝ በኩል ይመሯቸዋል፡፡ መላእክቱ ሌሎች መላእክት የመዳንን ካባ ወደ ሚደርቡላቸው ቦታ ይወስዷቸዋል፥ ይህም የጽድቅ ቀሚስ (ልብስ) ነው፡፡ ከዚያም መሪዎቹ መላእክት ወደ አክሊሎች ክፍል ይወስዷቸዋል፥ በዚያም እያንዳንዱ አክሊል ይጠልቅለታል፡፡

እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚሆኑት፥ በተዋበና ፍጹም በሆነ ቅደም ተከተል ነው፡፡ መላእክቱ እነዚህን ነገሮች ሲያደርጉ ፍጹም ደስተኞች ናቸው፡፡

በገነት ደውሎችን አላየሁም፥ ነገር ግን ያለማቋረጥ ሲደውሉ ሰምቻለሁ፡፡ በምድር አንዲት ነፍስ እንደዳነች ወዲያው በዚህ ደውል እንደሚጮህ ተነግሮኛል፡፡ ይህ “የገነት ክብሮች” ይባላል፡፡

## የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች በገነት

በሁሉም የገነት ጉብኝቶቼ፥ የተዋቡ ጠረጴዛዎችን እንዳየሁ አስተዋልሁ፡፡ እንዴት በአግባቡ እንደምገልጻቸው አላውቅም፡፡

በምድር ላይ አንዳንድ ጊዜ በ*[እንግሊዝ ንግሥት]* ቪክቶሪያ ዘመን የነበሩ በእያንዳንዱ ክፍላቸው ላይ ስነጥበብ የሞላባቸው ሌሎች ቅርጾች ያሏቸው እቃዎችን (ጠረጴዛ፣ ወንበር የመሳሰሉትን) አይቻለሁ፡፡ እናንተም ምናልባት እንደዚህ የተዋቡ እቃዎችን አይታችሁ ይሆናል፥ ልክ ግድግዳ ጥግ እንዳለ ጠረጴዛ ዓይነት ወይም የአበባ ማስቀመጫ አልያም መጽሐፍ የተቀመጠበት ጠረጴዛ ዓይነት፡፡ በገነት እንደነዚህ ዓይነት ጠረጴዛዎችን በየቦታው አይቻለሁ፥ ያው እነዚህ በልዩ ሁኔታ ድንቅ ቅርጽና አሠራር ያላቸው ከመሆናቸው በቀር፡፡

እንዲሁም መጽሐፍትና ሌሎች ነገሮች በየቦታው ነበሩ፡፡

## ሰማያዊ መዝገብ

ቅዱሳን፥ ሁልጊዜ ገንዘብ ስትሰጡ፥ አስራት ስትከፍሉ፥ ለያሑዋሕ ክብር የምትሠሩት ሥራ ሁሉ በገነት ስለሚመዘገብ ተጠንቀቁ፡፡ ይህን በደንብ ነው የማስታውሰው ምክንያቱም ጌታ ታላቅ ክብሩንና ኃይሉን ሲያሳየኝ፥ ፈጽሞ ከአዕምሮዬ ውስጥ እንዳይጠፋ አድርጎ ነው፡፡

በጉዞዎቼ ጊዜ፥ ብዙ መላእክት ከምድር ከሁሉም ስፍራ ዘገባ (ሪፖርት) ይዘው ወደ ገነት እንደሚመጡ አስተውያለሁ፡፡ በቦታው ወደተሾመ የመዝገብ መልአክ ወደ ሆነ ክፍል ይዘውት ይገባሉ፡፡ መልክተኛው መልአክ መልዕክቱን ያነባል፥ መዝጋቢው መልአክ ደግሞ ይጠይቃል፥ “*አንተ ምስክር ነህ? ይህ ነገር ሲሆን አይተሀል?*” ዘገባው (ሪፖርቱ) ሲረጋገጥ፥ በመጽሐፍ ውስጥ ይጠረዛል፡፡ እነዚህ መጽሐፍት በኋላ ላይ ወደ ያሑዋሕ ዙፋን ይወሰዳሉ፡፡ ነገር ግን ከዚያ በፊት ልዩ በሆነ ስርዓት ውስጥ ማለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

የጌታ መንፈስ ያለማቋረጥ በገነት ውስጥ ሲንቀሳቀስ በግልጽ አይቼዋለሁ፡፡ በምድር ካለ ከማንኛውም ነገር በላይ ነው፡፡ በምድር

ያሉ ነገሮች በገነት ካሉ ነገሮች የተቀዱ ናቸው፥ ነገር ግን በምድር ያሉት በሰማይ ካለው ጥላዊ ነጸብራቆች ብቻ ናቸው፡፡ የማይታመኑ ዜማዎች፥ የማይገቱ ውዳሴዎች፥ እንዲሁም ምድር በሰማይ እንዳሉ ፈጽማ የማትገምታቸው የከበሩ ነገሮች፡፡

ያሑዋሕ ሰዎች እንዲያወድሱት ይፈልጋል፡፡ ከዘፍጥረት መጀመሪያ እስከ ራዕይ መዝጊያ፥ ያሑዋሕ ቤተሰቦች እንዲወድዱት ፍላጎቶን ግለጿል፡፡

ይህን መጽሐፍ ስታነቡ፥ ገነት ያሑዋሕ ለሚወዱት ያዘጋጃት ስፍራ እንደሆነች አስታውሱ፡፡ አንድ ቀን ወደዚያ እሄዳለሁ፡፡ አንድ ቀን ዳግም የተወለዳችሁ ከሆናችሁ፥ ኃጢአታችሁን ከተናዘዛችሁ (ንስሐ ከገባችሁ)፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በልባችሁ ካለ፥ እናንተም ወደዚያ ትሄዳላችሁ፡፡

በከበረ ደሙ ኃጢአቶቻችሁን ሊያጥባላችሁ ይችላል፡፡ ስለበጉ ደም ልንገራችሁ፥ ስለከበረው የኢየሱስ ደም፡፡

## የሚያነፃው ደም

አስቀድሜ፥ ስለመዝገብ ክፍል ጠቅሻለሁ፥ አሁን ግን ሌላ ምስል ላሳያችሁ እፈልጋለሁ፡፡ በመዝገብ ክፍሉ ውስጥ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው መላእክት ተቀምጠዋል፡፡ ከፊትለፊታቸው የወርቅ ባልዲዎች አሉ፡፡ ይህም ደግሞ "የገነት ክብሮች" አካል ነው፡፡

ከመላእክቱ ፊትለፊት በአንድ ላይ ተጠርዘው የተደረደሩ መጻሕፍት አሉ፡፡ በመጻሐፍቱ ላይ ያሉት አንዳንዶቹ ምልክቶች (ጽሑፎች) ከምድር የሆኑ መልዕክቶች ይመስላሉ፡፡ እያንዳንዱ መልዕክት በረዥም መዝጋቢ መልአክ ይገመገማሉ፡፡

ከምድር መልዕክት ይዘው የመጡ ሌሎች ሁለት መላእክትን አየሁ፡፡ አንድ ሰው ዳግም ሲወለድ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ልቡ ተቀብሎ ከኃጢአቱ የእውነት ሲድን፥ ሁል ጊዜም አዲስ መልዕክት አለ፡፡ አንድ ሰው ከኃጢአቶቹ እውነት ንስሐ ገብቶ ኢየሱስ አዳኙና ጌታው እንዲሆን ሲጠይቅ፥ ያ ሰው ህይወቱን ለጌታ እንደሰጠ ይመዘገባል፡፡

ባለወርቃማ ባልዲዎቹ መላእክት እያንዳንዳቸው ከድርድሩ ውስጥ አንዳንዳ መጻሕፍት ወሰዱ፡፡ እያንዳንዱ መልአክ በደም የተነከረ ልብስ የሚመስል በእጁ ይዟል፡፡ ቀዩ ጨርቅ ክብር፥ ብርሃን፥ እንዲሁም ኃይል የተቀላቀለበት ነበር፡፡ ደም የተረጨበት ወይም እንደዛ ዓይነት ነገር አይደለም-የተዋበ ነበር!

እያንዳንዱ መልአክ የተመረጠውን መጽሐፍ ከፊቱ አስቀመጠ፥ ከዛም፥ ከመጀመሪያው ገጽ ጀመረ፥ በመዝገቡ የተጻፈውንም በደም በተነከረው ጨርቅ አጠፋው፡፡ በያሑዋሕ ምሪት፥ መልአኩ የዚህን ኃጢአተኛ የድሮ ታሪክ ጽሕፈት አጠፋና የዛን ሰው ወይም የዚያችን ሴት ዳግም መወለድ ብቻ አሰፈረ፡፡

> *መተላለፍህን ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህንም አላስብም።* (ኢሳ.43:25)

ልጆች፥ የያሑዋሕ ቃል እውነት ነው፡፡ መላእክቱ ገጾቹን ሲያጥቡ ማየት አስደሳች ነበር፡፡ ሃሌሉያ፥ ያሑዋሕ ለእያንዳንዳችን መዝገቡን ንጹህ አደርጎ ይደመስሳሰል!

ይህን የከበረ ነገር እያየሁ፥ በክብር ያሉ ቅዱሳን ሲዘምሩ ሰማሁ፡

*ኦ፥ ከኢየሱስ ደም ውጪ ኃጢአቴን ሊያጥብ የሚችል የለም፡፡*

*ኦ፥ ከኢየሱስ ደም ውጪ ዛሬ ሙሉ የሚያደርገኝ የለም፡፡*

*ኦ፥ ከኢየሱስ ደም ውጪ ዛሬ የሚያነጻኝ የለም፡፡*

*Oh, nothing but the blood of Jesus Can wash my sins away.*
*Oh, nothing but the blood of Jesus Can make me whole today.*
*Oh, nothing but the blood of Jesus Can cleanse me today.*

ከዚያም መላእክቱ ይህን መዝሙር ሲዘምሩ ሰማሁ፡

*ሌላው ተዋጅቶ ነው*

*በበጉ ደም፡፡*

*ሌላው ከዲያብሎስ እጅ ድኖ ነው*

*በበጉ ደም፡፡*

*ሌላው ከሲኦል ድኖ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም፡፡*

*Another one's been redeemed*
*By the blood of the Lamb.*
*Another one's been saved from the Devil's hand*
*By the blood of the Lamb.*
*Another one's been saved from hell By the blood of Jesus Christ.*

የኢየሱስ ክርስቶስን የደሙን ኃይል ለመጥራት ፈጽሞ አትፈሩ፡፡ ደሙ ከሁለት ሺህ አመታት ገደማ በፊት ኃጠአታችንን ለማጠብ ፈስሷል፥ እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኃይሉን ከቶ አላጣም! ኢየሱስ ሰይጣንን ድል ነስቶ "*ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና።*" (ዕብ. 7፡27) እናም ስለእኛ ወደ መስቀል ሄደ፡፡

ክርስቶስ ከክብር ወርዶ መጣ፡፡ ከድንግል ነበር የተወለደው፡፡ እኛ በከበረ ደሙ እንዋጅ ዘንድ የገዛ ሕይወቱን ሰጠ፡፡ ይህንን ያደረገው እኛ ወደ ሲኦል፥ ወዳሳየኝ አስቀያሚው ስፍራ እንዳንሄድ ነው፡፡

ውድ ወዳጆች፥ ወንጌሉ እውነት ነው፡፡ መላእክቱ ከተከመሩት መጻሕፍ የቀደመውን ታሪክ ሲደመስሱ እንዴት ሀሴት እንዳደረግሁ፡፡ ያለፈውን የድሮውን ሁሉ ደመሰሱት፥ ቆሻሻውን ነገር ሁሉ፡፡ አሮጌው ነገር ሁሉ አልፏል፤ የኢየሱስ ደም ሁሉን አጥፍቷቸዋል፡፡

## የያሑዋሕ መሠዊያዎች

የያሑዋሕ መሠዊያዎችን እወዳቸዋለሁ፡፡ የተዋበ መሠዊያ ወዳለው በመንፈስ ወደተሞላ ቤተክርስቲያን ስሄድ፥ በዚያ ብዙ እንባዎች እንደፈሰሱ አውቃለሁ፡፡

በብሉይ ኪዳን፥ ያሑዋሕ ደጋግሞ ለሕዝቡ ሄደው የቀድሞዎቹን የአሕዛብ መሠዊያዎች እንዲያፈርሱ ነግሯቸዋል፡፡ አንድ ምሳሌ ይኸውላችሁ፡

> *መሠዊያቸውንም አፍርሱ፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብሩ፥ የማምለኪያ ዐፀዶቻቸውንም በእሳት ኣቃጥሉ፥ የአማልክቶቻቸውንም የተቀረጹ ምስሎች አንኳታኩቱ፤ ከዚያም ስፍራ ስማቸውን አጥፉ። ለአምላካችሁ ለያሑዋሕ እንዲህ ያለ ሥራ አትሥሩ።* (ዘዳ.12:3-4)

የያሑዋሕ ሕዝቦች ለእርሱ ውዳሴን የማይሰጡትን መሠዊያዎች ያፈርሱ ነበር፡፡ ለእርሱ ክብር ወይም አድናቆት የማይሰጡትን መሠዊያዎች ያስወግዱ ነበር፥ ያን ጊዜ ብቻ ነው ለእርሱ አምልኮ ብቻ መሠዊያዎችን የሚሠሩትና የሚጠብቋቸው፡፡ የእነዚያ ትእዛዛት ምሳሌ ይኸውላችሁ፡

ኢየሱስ ብቻ ነው ይህን ሊያደርግላችሁ የሚችለው፡፡ እናንተ በራሳችሁ ልታደርጉት አትችሉም፡፡

> *ያሑዋሕም በዚያ ሌሊት። የአባትህን በሬ፥ ሰባት ዓመት የሆነውን ሁለተኛውን በሬ፥ ውሰድ፥ የአባትህ የሆነውንም የበኣል መሠዊያ አፍርስ፥ በእርሱም ዙሪያ ያለውን የማምለኪያ ዐፀድ ቍረጥ፤ በዚያም ኮረብታ አናት ላይ ለአምላክህ ለያሑዋሕ መሠዊያ አሳምረህ ሥራ ሁለተኛውንም በሬ ውሰድ፥ በዚያም በቈረጥኸው በማምለኪያ ዐፀዱ እንጨት ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቅርብ አለው።* (መሳ.6:25-26)

# የአሁን ዘመን መሠዊያዎች

በከተማዋ ሁሉ ሳስተምር፥ የ**ያሕዋሕ**ን መሠዊያ አስባለሁ፡፡ ወደ መሠዊያው ፊት ለፊት መጥተን ልባችንን ለ**ያሕዋሕ** ስናፈስ፥ በእርሱ (በ**ያሑዋሕ**) አናፍርም፡፡ የተመደበ (ቋሚ) መሰዊያ በ**ያሑዋሕ** ህልውና ፊት የምንሆንበት አንዱ ስፍራ ነው፥ እርሱን የምንጠራበትና ኃጢአታችንን የምንናዘዝበት፥ ይቅር እንዲለን እርሱን የምንጠይቅበት፡፡

ብዙዎቻችን በዚያ የእርሱ አስደናቂ ህልውና ይሰማናል! እርሱ ጸሎታችንን እንደሚመልስ ማወቅ እንችላለን፡ አንዳንድ ጊዜም እጁ በዙሪያችን ይሰማናል፡፡ በመሠዊያዎቹ የሆነ ነገር አለ-በድሮ መልኩ ያሉት-የ**ያሑዋሕ** መሠዊያዎች-በቤተክርስቲያን ውስጥ፡፡ በዚያ ሄዳችሁ ተንበርክካችሁ **ጌታ**ን ማምለክ ትችላላችሁ፡፡ **ያሑዋሕ**ን በቤታችሁም ማወደስ ትችላላችሁ፡፡ መኪናችሁም ውስጥ ልታደርጉት ትችላላችሁ፡፡ የትም ቦታ ልታወድሱት ትችላላችሁ፡፡ ሆኖም ግን፥ አንድ ነገር ልንገራችሁ፤ መሰዊያው የተሾሙት በጥልቀት ከእርሱ ጋር ህብረት የሚያደርጉበት ትክክለኛው ስፍራ ነው፡፡

የብሉይ ኪዳን ነቢያት ለ**ያሑዋሕ** መሠዊያዎችን ሲያዘጋጁ፥ ስለሕዝቡ ኃጢአትና ስለራሳቸው ኃጢአት እየተናዘዙ ወደ **ያሑዋሕ** ይጮኹሉ፡፡ በመሰዊያው ላይ ሕዝቡን ወክለው ንስሐ እየገቡ የደም መስዋዕትን ያቀርባሉ፥ እናም **ያሑዋሕ** መሥዋዕታቸውን ተቀበለ፡፡

**ኢየሱስ ክርስቶስ** ባፈሰሰው **ደሙ** ስለእኛ ኃጢአት ፍጹሙን መስዋዕት ስላቀረበ፥ ከዚህ በኋላ መስዋዕትን ማቅረብ አያስፈልገንም፡፡

ሆኖም፥ ስለኃጢአት በተወቀሰን ጊዜ ንስሐ ልንገባ ያስፈልገናል፥ እናም ይህን ለማድረግ አንዱ ዋነኛ ስፍራ መሰዊያው ነው፡፡ የተመደበ የቤተክርስቲያን መሰዊያ ስናይ፥ የሚቻል ከሆነ፥ እርሱ ጋር ተንበርክከን ለ**ያሑዋሕ** ልንጸልይ ያስፈልገናል፡፡

መሰዊያ ሲኖር ብዙ ነገር ማለት ነው፡፡ በቤታችንም አንድ ያስፈልገናል፥ ከ**ያሑዋሕ** ጋር እንድናወራና ከእርሱ ጋር ለብቻ የምንሆንበት ቦታ እንዲኖረን፡፡

ስሰብክ ሁል ጊዜም ለሕዝቡ እነግራቸዋለሁ፥ *"ወደዚህ መሠዊያ ለመምጣት አትፈሩ፡፡ በዚህ **ያሑዋሕ** ይገናኛችኋል፡፡"* አዎን በተቀመጣችሁበት ሊገናኛችሁ ይችላል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን፥ በተቀደሰና ሁል ጊዜም በሚያገለግል መሠዊያ ግን ሁል ጊዜም የሆነ ነገር አለ፥ እራሳችሁን አዋርዳችሁ፥ እጃችሁን ከፍ አድርጋችሁ፥ *"**ያሑዋሕ** ሆይ፥* እነሆኝ፡፡ ውሰደኝ፡፡ ለክብርህ ተጠቀመኝ፡፡" በሉ፡፡

# ከልብ አምልኩት

የምትሉት ነገር በሙሉ ልባችሁ የእውነት ሊሆን ይገባል፡፡ **ያሑዋሕ** የሚወዱትና የሚያወድሱት ሰዎችን ይፈልጋል፡፡ **ያሑዋሕ** ከክፉ ሥራዎቻቸው ተመልሰው ወደ እርሱ የሚመጡ ሰዎችን ይፈልጋል፡፡ በ**እውነትና በመንፈስ ቅዱስ** የሚያመልኩትን ሰዎች እየፈለገ ነው፡፡

> *በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈግሉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።* (2ዜና.7:14)
>
> *ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤ ያሑዋሕ መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።* (ዮሐ.4:23-24)

ከ**ያሑዋሕ** ጋር ግልጽ ሁኑ፡፡ ከ**ያሑዋሕ** ጋር እውነተኞች ሁኑ፡፡ ወደ መሠዊያው ስትሄዱ፥ ተንበርክካችሁ "ቤቲ አጥፍታለች፥" አልያም "ጆ አጥፍቷል" (የሆነ ሰው ስም ጠርታችሁ እገሌ አጥፍቷል ወይም አጥፍታለች) እንዳትሉ፥ እንዲህ በሉ፥ *"ጌታ ሆይ፥ ያጠፋሁት እኔ ነኝ፡፡* ይቅርታ ስለሚያስፈልገኝ በዚህ ቆሜያለሁ፡፡" ከዚያም፥ የሆነ ነገር (ቂም፣ ቅሬታ) የያዛችሁባቸውን ሰዎች ይቀር በሉ፡፡

ቅዱሳን፥ **ያሑዋሕ** የአርነት ሰዎችን እየፈለገ ነው፥ የእውራን ዓይኖች እንዲከፈቱና ጆሮዎች ተከፍው የ**ጌታ መንፈስ** ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን እንዲሰሙ፡፡ (*ራዕ. 2:7*)

ኦ፥ የገነት ክብሮች! በዚያ የሚጠብቃችሁን ማየት ከቻላችሁ! በዕለት ተዕለት ህይወታችን ብዙ ተግዳሮቶችና መከራዎች ውስጥ

እናልፋለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጠላት ሁሉን ነገረ ከእኛ ሊሰርቅ የፈለገ ይመስላል፥ ነገር ግን ያሑዋሕ ለመቋቋም፥ ከፍ ሲልም ድል ለመንሳት፥ ትእግስቱን ይሰጠናል፡፡ ብዙ የህይወት ጫናዎች አሉ፥ ነገር ግን በጌታችን ሰላምና ደኅንነት አለ፡፡

ጥሩ፥ ጠንካራ ቤተክርስቲያን በአቅራቢያችሁ ከሌለ፥ እውነተኛውን የያሑዋሕ ቃል የሚሰብክና የሁሉን ቻዩን አምላክ ህይወትንና ልብን የመቀየር ኃይል የሚያምን ቤተክርስቲያን እንድትፈልጉ አስቸኩላችኋለሁ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያምን ቤተክርስቲያን ፈልጉ፡፡ በዚያ የያሑዋሕን ጥበብ ትማራላችሁ እናም ከችግራችሁ፥ ከሀዘናችሁ፥ እንዲሁም ከጭንቀታችሁ ነጻ ትወጣላችሁ፡፡

ታውቃላችሁ፥ ከያሑዋሕ ሕዝብ ጋር መገናኘት አስፈላጊ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሳችን እንድንሰባሰብ ይነግረናል፡፡ (ዕብራ. 10፡25) ብቻችሁን በውጭ አትሁኑ፡፡ ያሑዋሕ ይወዳችኋል፥ እናም የሚወዷችሁ የያሑዋሕ ቅዱሳንም አሉ፡፡

## ሊገለጡ ያላቸው ክብሮች

ሌላው የገነት ክብሮች ክፍል ገና ሊገለጡ ያላቸውን ምስጢራት አካቷል፡፡ እንዳያቸው አልተፈቀደልኝም፡፡

ሆኖም ግን፥ በአንዱ ጉዞ፥ የሚያምሩ ቤቶችንና ትላልቅ መኖሪያ ቤቶችን አይቻለሁ፡፡ ይህ ክፍል በፍጥነት ያለፈ ይመስላል፡፡ ከዚያም መላእክት ብዙ ዓይነት ሥራ ወደሚሠሩበት ስፍራ ተወሰድሁ፡፡ ስርዓት ባለው መልኩ ከምድር እየመጡ ይመስላል፥ እናም በእጆቻቸው ወረቀቶችን ይዘው በበሮቹ ይገባሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ መላእክቱ ሲጽፉበት የነበረን መጽሐፍ ይዘው ይመጣሉ፡፡ እነዚህ ዘገባዎች (ሪፖርቶች) ይዘው ወደ ገነት የተለያዩ ክፍሎች ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም፥ ለቅዱሳኑ ሽልማት መረጃን ለማስቀመጥ፥ ዘገባዎቹ በመጽሐፍ ውስጥ ይጠረዛሉ፡፡ ወደ ገነት ስትሄዱ፥ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስላደረጋችሁት ማንኛውም ነገር ትሸለማላችሁ፡፡ ለዚህ ነው ይህን መጽሐፍ የምጽፈው፡፡ የገነት ራዕዬን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነትና ክብር እየጻፍሁ ነው፡፡

ያሑዋሕ ያሳየኝን የገነት ምስጢራት ክፍሎች እንድትረዱ እፈልጋለሁ፡፡ ልነግራችሁ የምችለው ያየሁትን ብቻ ነው፥ ምክንያቱም ምስጢራቱ የተገለጡልኝ በከፊል ስለሆነ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አሁን "*ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤*" (1ቆሮ.13፡9) ይላል፡፡

ያሑዋሕ ይመስገን፥ የመጨረሻ መድረሻችን ጋር ስንደርስ፥ የመጨረሻ ቤታችን፥ ጥያቄዎቻችን ሁሉ ይመለሳሉ፥ እናም ሁሉም ጥልቅ መሻቶቻችን ይፈጸማሉ!

---

# መላእክት በሥራ ላይ ሆነው ራእይ

በዚህ ምዕራፍ መላእክት በሥራ ላይ ሆነው ስላየሁት ራእይ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ያሑዋሕ ያሳየኝን አንዳንድ ያማሩ ነገሮች እንድትረዷቸው እፈልጋለሁ፡፡ ምን እንደሚጠብቃችሁ በማወቅ የጌታን ሥራ እየሠራችሁ ሀሴትንና ደስታን ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ያሑዋሕ "*ምስጢሩን ለባሪያው ለነብይቷ*" (አሞጽ 3፡7) በመግለጡ አስገራሚ ነው፡፡ መሻቱ እነዚህን ነገሮች ለእርሱ መገለጦች ንቁ ለሚሆኑና መልእክቱን ለሚያውጁ ለመግለጥ ነው፡፡

> *የእስራኤል ንጉሥ ያሑዋሕ፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ ያሑዋሕ እንዲህ ይላል። እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሣና ይጥራ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፥ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ። አትፍሩ አትደንግጡም፤ ከጥንቱ ጀምሬ አልነገርኋችሁምን? ወይስ አላሳየኋችሁምን? እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም፤ ማንንም አላውቅም።* (ኢሳ.44፡6-8)

ጌታም መለሰልኝ እንዲህም አለ፡

> "*አንባቢው ይፈጥን ዘንድ ራእዩን ጻፍ፥ በጽላትም ላይ ግለጠው።*" (ዕን.2፡2)

ያሑዋሕ በወሰናቸው ተወካዮቹ ነገሮችን ሊገልጥ እንደሚፈልግ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች አሉ፡፡ የያሑዋሕ ቃል እርግጥና

እውነት ነው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ዳንኤል ከጌታ ዘንድ ራእይ አይቷል፡

> *በባቢሎን ንጉሥ በብልጣሶር በመጀመሪያው ዓመት ዳንኤል በአልጋው ላይ ሕልምንና የራሱን ራእይ አየ፤ ከዚያም በኋላ ሕልሙን ጻፈ፥ ዋነኛውንም ነገር ተናገረ።* (ዳን.7:1)
>
> ባለ ራእዩ የሐንስ ራሱ ከጌታ ዘንድ ራእይን አይቷል፥ እንዲጽፋቸውም ተነግሮታል፡ "*የምታየውን በመጽሐፍ ጻፈህ*" (ራእ.1:11)

ኢሳይያስ ለይሁዳ ወሳኝ መልእክቶችን የሚነግር ታላቅ ነቢይ ነበር ምክንያቱም ራእዮቹና እነርሱን ለመናገር የነበረው ድፍረት ነው። መጽሐፉ የሚጀምረው፡ "*በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያንና በኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን ስለ ይሁዳና ስለ ኢየሩሳሌም ያየው የአሞጽ ልጅ የኢሳይያስ ራእይ።*" (ኢሳ. 1:1) ብሎ ነው። ሕዝቅኤል የያሑዋሕን ራእይ ስላየ (ሕዝ. 1:1)፥ ለትንቢታዊ አገልግሎት ለመቀባት ተጠራ።

ያሑዋሕ፥ በዘላለማዊ ምህረቱ፥ ከራሱ የሆነውን ራእይ ሊያሳየኝ ብቁ እንደሆንሁ አይቶ መረጠኝ። ለዚህም ያሑዋሕን አመሰግነዋለሁ። በጸሎትና በማሰላሰል፥ በአንዳንድ ነገሮችም ላይ የያሑዋሕን ፊት እየፈለግሁ ሳለ፥ በመንፈስ ምስጢራትን እንዳይ ተፈቀደልኝ።

በያሑዋሕ የሆነው ጥሪዬ ህልሞችን፥ ራእዮችን፥ ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን መቀበልና ለሌሎች ማካፈል ነው። እንደተቀባ የያሑዋሕ እጅ ሥራ፥ ያሳየኝን ነገሮች በቀላሉ እየገለጽሑላቸው ነው። ይህ የእኔ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርሻ እንደሆነ አምናለሁ።

## የያሑዋሕን እውነት መግለጥ

በእነዚህ ገጠመኞች መጀመሪያ ላይ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲኦልን ሊያሳየኝ ተገለጠለኝ። በሚያንጸባርቅ ነጭ ልብስ ተገለጠልኝ፥ በብርሃንና በኃይል የተሞላ ነበር። ኢየሱስ ወደ ስድስት ጫማ ቁመት ያለው መስሎ ነው የታየኝ። ጺሙ(ጽሕሙ) በጥራት የተከረከመ ይመስላል። ጥቅጥቅ ያለው ጸጉሩ በትከሻው ላይ ተንዘርፍፎ አርፏል። የተዋቡት ዓይኖቹ ውስጥ ድረስ ጠልቀው የሚያዩ ናቸው።

የኢየሱስ አቋም እኔ እንዳየሁት በራዕዮቼ ውስጥ ቅርብ ሆኖ የታየኝ በለቅሶ ግንብ (የኢየሩሳሌም ቅጥር ግምብ) ሆኖ ነው፥ በአይሁድና በኢየሩሳሌም ላይ እየጸለየ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ እጅግ ብዙ ፍቅርና ርኅራኄ አለው፥ ልክ የስነጥበብ ባለሙያው እንደገለጸው፥ ይህም ሲኦልንና ገነትን የሚመጡትንም ነገሮች ለአንድ ሰው ለማሳየት ምን ያህል እርቀት እንደሚጓዝ ነው።

## የእሳት ሰረገላዎች

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ተመልከቱ፡

> *ኤልሳዕም አቤቱ፥ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን፥ እባክህ፥ ግለጥ ብሎ ጸለየ። ያሑዋሕም የብላቴናውን ዓይኖች ገለጠ፥ አየም፤ እነሆም፥ በኤልሳዕ ዙሪያ ያሉት የእሳት ፈረሶችና ሰረገሎች ተራራውን ሞልተውት ነበር።* (2ነገ.6:17)

በገነት ሳለሁ፥ የእሳት ሰረገሎችን አየሁ፥ መላእክትም በእነርሱ ላይ ሆነው እየነዷቸው ነበር። በጣም ረዥምም ተሽከርካሪዎች ነበሩ፥ እናም በአስደናቂነታቸው በጣም ተገርሜ ነበር።

## የያሑዋሕ ራእዮች

ስለመላእክት ያለውን ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተመልከቱ፡

> *እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤* (ሐዋ.1:10)

አንድ ሰው ይህን አንብቦ እንዴት አያምነውም? ኢየሱስ ወደ ሰማይ በተነጠቀ ጊዜ ያሑዋሕ መላእክትን በግልጽ ለሰዎች አሳይቷል፡፡ ቅዱሳን፥ ያሑዋሕ በዚህ የመጨረሻ ዘመን የከበረ ኃይሉንና ድንቅ ሥራዎቹን ሊገልጥ ይፈልጋል፡፡ ያሑዋሕ ለእኛ የሚያሳየን ራዕዮች አሉት፡፡ በምድር ላይ ለእርሱ በምንሠራው ሥራ ጉጉዎችና ደስተኞች እንድንሆን እንዚህን እውነታዎች ከእኛ ጋር ለመካፈል ይፈልጋል፡፡

## ተአምራት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

ከእነዚህ ራዕዮች ጊዜ በኋላ፥ በሆነ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ላይ እያገለገልሁ ነበር፡፡ ጥልቅ በሆነ ጸሎትና ማሰላሰል ውስጥ ነበርሁ፡፡ የዚያን ቀን ምሽት በቤተክርስቲያን ውስጥ፥ መላእክትን በየቦታው አየሁ፡፡ ሁሉም ወርቃማ ሰይፎች በእጆቻቸው ነበሯቸው፡፡

የጌታ መንፈስ ተናገረኝ፡፡ በግልጽም እንዲህ አለኝ፡

> ***ልጄ፥ ለሕዝቤ የጸሎት ሰዓት ሲደርስ፥ አንዳንድ የሰውነት ችግሮችን ልፈውስ እፈልጋለሁ፡፡ ይህም ስለሲኦል ምስክርነትሽ እውነት እንደሆነ በአንቺ አገልግሎት ውስጥ ምልክት እንዲሆን እፈልጋለሁ፡፡ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሲሰበክ ምልክቶችና ድንቆችን እንዲሁም የተዓምራት ሥራዎችንም እንደማደርግ ቃሌን ስጥቻለሁ፡፡***

በጣም ጉጉት አደረብኝ! በመንፈስ አንድ መልአክ ረዥም መጽሐፍ በእጁ ይዞ የምሰብከውን ነገር ሲጽፍ አየሁ፡፡ ኮርኒሱ የተከፈተ ነበር የሚመስለው፥ እናም በዙፋኑ ላይ ሆኖ የያሑዋሕን ራዕይ አይ ነበር፡፡ መላእክት ሀሴት እያደረጉና ያሑዋሕን እያወደሱ ነበር፡፡

## የኃጢአትን እስራት መስበር

ወደ መሰዊያው የመጥሪያው ጊዜ ሲደርስ፥ መላእክት በጉባኤው መካከል ሲሄዱ አየሁ፥ ሰዎች ወደ መሰዊያው እንዲሄዱና ልባቸውን ለጌታ እንዲሰጡ እየገፋፉ ነበር፡፡ መላእክቱ የአንዳንድ ሰዎችን ልብ ሲነኩ ሳይ፥ በያሑዋሕ ፊት ተንበርክከው ሲጸልዩ ኃጢአታቸው በልባቸው ውስጥ የጠቆረው ኃጢአት ሲንተከተክና ከልባቸው ሲወጣ አየሁ፡፡ ኦ፥ ደስ የሚል ነበር!

ልቅሶና ጩኸት ነፃ ከወጡ ሰዎች በየቦታው ይወጣ ነበር፡፡ አስደናቂ ነበር፡፡ በዓለም ዙሪያ ሁሉ በእያንዳንዱ አገልግሎቶቼ፥ ያሑዋሕ እንደዚህ ዓይነት ብዙ ተዓምራቶችን ያቀርባል፥ እናም አስደናቂ አርነቶች መሆን ጀመሩ፡፡

ስለምልክቶችና ድንቆች እንዲሁም ተዓምራቶቹ ያሑዋሕን አመሰግነዋለሁ፡፡ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ እያገዙኝ፥ መላእክት በሥራ ላይ እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡

## እስራትን መስበር

አንድ ሌላ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ጥቅሶች እየተነገሩ ሳለ፥ ቃሉ ከገጾቹ ላይ እየዘለለ የሰይፍ ቅርጽ መሥራት ጀመረ፡፡ ሰይፉ የአንድን ሰው ሰውነት በስቶ ይገባና ቀጥታ ወደ ችግሩ ሄዶ ይፈውሰዋል፡፡

የያሑዋሕ ክብር በየቦታው ነበረ! ተገርሜ ነበር፡፡ ሰማይን በምድር ስለሆነው በረከቱና ስለዚህ ያማረ የቃሉ መገለጥ ያሑዋሕን አወድሰዋለሁ፡፡

-----------------------------------------------------------

# የያሑዋሕ ቃል

በምሄድባቸው ብዙ አገልግሎቶች፥ መላእክቱ እየደረጓቸው ያሉትን ብዙ ያማሩ ነገሮችን አየሁ፡፡ በእርግጥ ይህን ታውቃላችሁ፥ መላእክት መዳንን ሊወርሱ ላሉት ለማገልገል ከጌታ ዘንድ የሚላኩ መናፍስት ናቸው፡፡ (ዕብራ. 1፡13ትን ተመልከቱ) አንድ ጊዜ

አንድ አገልጋይ ትንቢት ሲናገር አየሁ፡፡ እርሱ ትንቢት እየተናገረ፥ **ያሑዋሕ** ከጭንቅላቱ በላይ ያለውን መልአክ እንዳይ ዓይኖቼን ከፈታቸው፡፡ መልአኩ ከእሳት ጋር የተደባለቀ የሚመስል ዘይት በራሱ ላይ ከቀንድ ውስጥ ሲያፈስ አየሁ፡፡ ከዚያም የሰውየውን ልብ በራዕይ አየሁ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተሞላ ነበር፥ በ**ያሑዋሕ ቃል**፡፡ **ቃሉ** ከልቡ ወደ ላይ የሚመጣ ይመስላል፥ ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ ሆኖ የሚመጣ ይመስላል፡፡

ሌላ መልአክ የ**ያሑዋሕ** ሰው (አገልጋዩ) ያለውን እየመዘገበ ነበር፡፡

"ኦ፥ **ያሑዋሕ** ሆይ፥ ይህ በእውነት ቃልህ ለሕዝብህ እየወጣ ነው፡፡" ብዬ አሰብሁ፡፡

ከዚያም ከመላእክቱ አንዱ ቅዱሳን ጽሑፎችን (ጥቅሶችን) ይዞ አየሁ፡፡ ሰውየው ህያው የሆኑትን የ**ያሑዋሕ** ቃላት መስበክ ሲጀምር፥ ቃላቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ውስጥ እየዘለሉ የሚወጡ ይመስላሉ፡፡ ወደ ልቡ ይሄዱና ከዚያ ወደ አንደበቱ ይሄዳሉ፡፡ ይህ ሲሆን፥ የመጽሐፍ ቅዱሱ ቃላት ባለ ሁለት አፍ ሰይፍ ሆኑ፡፡

አገልጋዩ ስለታመሙና በበሽታዎች ስለተጨቆኑ ሰዎች ሲጸልይ፥ **ጌታ** በሳንባ፥ በእግር፥ በልብ፥ አልያም ችግሩ ያለበትን የትኛውም ስፍራ ውስጥ ያለን ጥቁር ቦታ እንዳይ ያደረገኝ ይመስለኛል፡፡ የ**ቃሉ** ሰይፍ በሰውነት ውስጥ ወደ ተጠቃው ክፍል ሄዶ ይገባል፥ ከዚያም ሙቀት በዙሪያው መሞቅ ይጀምራል፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች ለፈውስ ሲጸለይላቸው፥ "አ፥ የመንፈስ ሙቀት ይሰማኛል" ይላሉ፡፡

በሽታ እንዴት ከሰውነት ውስጥ ተቃጥሎ እንደሚወጣ በመንፈስ እንዳይ ተደረጌያለሁ፡፡ የ**ያሑዋሕ** ቃል ሲሠራ መገለጡ እጅግ ያማረ ነበር፡፡ እያየሁም አሮጌው በነበረበት ቦታ አዲስ ቆዳና አዲስ ህዋስ ሲበቅል አየሁ፥ **ጌታ**ንም ማወደስ ጀመርሁ፡፡

በኋላ ላይ፥ አንዳንዶቹን ሳናግራቸው፥ እንዲህ ይሉኝ ነበር፥ "ያን ቀን በተአምር ተፈወስሁ፡፡" እዚህ በምደር ላይ፥ በከፊል ብቻ እናያለን በከፊልም ብቻ እናውቃለን፡፡ **ያሑዋሕ** የፈቀደውን ብቻ እናያለን እናውቃለንም፡፡ ያየሁት **ያሑዋሕ** እንደፈቀደው ብቻ ነበር፥ እናም እውቅናውን፥ ክብሩን፥ ታላቅነቱን ለእርሱ እሰጣለሁ፡፡

## ዙፋኑን መቅረብ

በአሁኑ ዓለምና በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነቢያትን ጥቅምና አስፈላጊነት ማየት ጀመርሁ፡፡ በኤፌሶን ላይ የተጠቀሱት የአምስቱን አገልግሎቶች አስፈላጊነት ማየት ጀመርሁ፡፡

> *እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤* (ኤፌ.4:11)

እያንዳንዳቸው በ**ክርስቶስ** አካል ውስጥ ያላቸውን ጥቅም አየሁ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ "*ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት*" መቅረብ እንደምንችል ይነግረናል፡፡ (ዕብ.4:16) ቃሉ "*በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት*" እንዳለን ያረጋግጥልናል፡፡ (ዕብ.10:19-20) ምክንያቱም "*እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።*" (ዕብ.9:22)

ወዳጆች፥ ይህ እውነት እንደሆነ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ነፍስን የሚያነፃው የ**ኢየሱስ ክርስቶስ ደም** ነው፡፡ **ቃሉና ደሙ** በጸጋው በጋራ ይሠራሉ፡፡

> እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ። (ዕብ.4:16)

## በጣም የቀረበ እርዳታ

ምን ያህል ግዜ ነው ታላላቅ መሻቶች ያሉን? በሰውነታችን በሽታ አለብን፡፡ በእራስ ምታቶች ውስጥ እናልፋለን፡፡ በፍቺ ውስጥ እናልፋለን፡፡ የሞተ የምንወደው ሰው ይኖራል፡፡ በዓለም የቀረ ልጅ ሲኖር፡፡ ምንም ዓይነት የሚመጣ (የሚገኝ) ገንዘብ የሚኖር

ሳይመስል ሲቀር፥ እናም እርዳታ ሲያስፈልገን፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ጊዜያቶች ወደ ያሑዋሕ ዙፋን በድፍረት ቀርበን እንጸልያለን፥ "*ያሑዋሕ ሆይ፥ እርዳታህ ያስፈልገኛል፡፡*"

በምድር ስላሉት ነገሮች ያሑዋሕ በሰጠኝ ራዕይ ውስጥ፥ ቅዱሳን ወደ ጌታ ለእርዳታ በሚጮኹበት ጊዜ ሁሉ የያሑዋሕ ቃል በዚያ ይገኛል፡፡ መልአክ በእጁ ረዥም መጽሐፍ ቅዱስ ይይዛል፡፡ ከዚያም መልአኩ የያሑዋሕን ቃል ይገልጥና በሰይጣን ፊት ላይ ይጠርገዋል፡፡ ሰይጣን በእርኩስ መንፈስ አልያም በእባብ አምሳል በዚያ ይገኛል፡፡ መልአኩ ጥቅሶቹን ሲከፍት፥ ሰይጣን የእውነት ወደ ኋላ ይወድቃል፥ እየጮኸ፥ ምክንያቱም መልአኩ ሁለት አፍ ያለውን ሰይፍ በእርሱ እየተጠቀመበት እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው፡፡

አሁን፥ በመንፈስ ሳያቸው የነበሩት ነገሮች ሁል ጊዜ በማገለግልባቸው ቤተክርስቲያናት ውስጥ የሚታዩ ላይሆኑም እንደሚችሉ ልነግራችሁ እወዳለሁ፡፡ በማይሎች እርቀት ያሉ ነገሮችን ሊሆን ይችላል የማየው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የትና መቼ እየሆኑ ያሉ ነገሮች እንደሆኑ እንኳን አላውቅም፡፡

ያሑዋሕ ይመስገን፥ እኛ የነጻነትን ህይወት እንኖር ዘንድ ኢየሱስ ሰይጣንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመስቀሉ አሸንፎታል፡፡ አሁን ወዳለንበት የጸጋው ዙፋን በድፍረት መቅረብ እንችላለን፡፡

## ቅብዓት እና ፈውስ

የያሑዋሕ ጸጋና ምህረት በቅዱስ ቃሉ ማንኛውንም በሽታና ደዌ ለመፈውስ የቀረበና እውነተኛ ነው፡፡ ዛሬ በያሑዋሕ ቃል እንድትጽናኑ እፈልጋለሁ፡፡

መሻት ካላችሁ፥ በድፍረት ወደ ጸጋው ዙፋን ሂዱና ያሑዋሕን እንዲረዳችሁ ጠይቁት፡፡ የያሑዋሕ መላእክት "*መዳንን ይወርሱ ዘንድ ላላቸው ለማገልገል የሚላኩ መናፍስት*" ናቸው፡፡ (ዕብ. 1፡14)

ይህን ያወቅሁት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው፥ እናም አምነዋለሁ፡፡ ይልቁንም፥ እኔ በእውነታም አውቀዋለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊው ዓለም አይቼዋለሁ፡፡ ወደ ጌታ ስንጣራ፥ በቃሉና በመንፈሱ ታላቅ ኃይል እንዲረዱን መላእክቱን ይልካል፡፡

በአንድ አገልግሎት ውስጥ አጋንንት ከአንድ ሰው እንዲወጣ ሲደረግ፥ እርኩሳን መናፍስቱ እንደ ጥቁር ጥላ ወይም እንደ ሙት-መንፈስ (apparition - ጎስት መሳይ) ሆነው ይወጣሉ፡፡ የኢየሱስ ስም ሲጠራ፥ የያሑዋሕ መልአክ እርኩሱን መንፈስ በሰንሰለት ሲያስረው አይቻለሁ፡፡ ያንን ሳይ፥ "*ያሑዋሕ ሆይ፥ እነዚህን ሰዎች እነዚህን በአጋንንት የተጠቁ ሰዎችን ከእርኩሳን ኃይላት ነፃ የሚያወጣ ቃልህ ምንኛ ኃያል ነው፡፡*" ብዬ አሰብሁ፡፡

የጌታ ቃል ነው የሚሠራው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው፡፡ በእርሱ ስም ብቻ ነው-የኢየሱስ ክርስቶስ ስም-ይህ ሊሠራ የሚችለው፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ጥሩ፡፡ ያድናችሁማል፡፡ ዳግም የተወለዳችሁ፥ ከኃጢአታችሁ ነፃ የወጣችሁ ትሆናላችሁ፥ እናም በገነት ዘላለማዊ ቤት ይኖራቸዋል፡፡

## የቃሉ ኃይል

አንድ ጊዜ በማሌዢያ ሀገር ነበርሁ፡፡ ሕዝቡ ለጌታ እጅግ የተራቡ ነበሩ፥ በያሑዋሕ ህልውና መገኘት ታላቅ የሆነ የያሑዋሕ እንቅስቃሴ እንደሚኖር አወቅሁ፡፡ የያሑዋሕ ክብር በእኛ ላይ መውረድ ሲጀምር፥ ልክ እንደ ዝናብ ነበር፡፡

መንፈስ ቅዱስ በመሀከላችን እየተንቀሳቀሰና ሰዎችን እያዳነ ነበር፡፡ ሰዎች ጌታን ሲቀበሉ ከመቀመጫቸው ወደ መሬት ይወድቁ ነበር፡፡ ብዙ ነፍሶች የጌታ ኃይል ሲነካቸው አርነት ወጥተዋል፡፡ ኦ፥ ደስታውና የመጣው የያሑዋሕ ክብር! የያሑዋሕ ቃል እየተሰበከ ሰዎችን ነፃ እያወጣ ነበር፡፡

ሰዎቹ እንዴት ለያሑዋሕ እንደተራቡ! ዳግም መወለድና ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ልባቸው እንዲመጣ መጠየቅ ይፈልጉ ነበር፡፡

የያሑዋሕ ቃል ኃይል የሚደንቅ ነበር፡፡

## ምግብ ለህሳብ

ልታስቡበት የምፈልገው ሌላ ጥቅስ ይኸውላችሁ፡

> *በእስራኤልም ሠራዊት ፊት ይሄድ የነበረው የያሑዋሕ መልአክ ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ፤ የደመናውም ዓምድ ከፊታቸው ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ቆመ፥ በግብፃውያን ሰፈርና በእስራኤል ሰፈር መካከልም ገባ፤ በዚያም ደመናና ጨለማ ነበረ፥ በዚህ በኩል ግን ሌሊቱን አበራ፤ ሌሊቱንም ሁሉ እርስ በእርሳቸው አልተቃረቡም።* (ዘጸ.14:19)

የያሑዋሕ ልጆች፥ ያሑዋሕ ትላንት እንዳደረገው ዛሬም ተዓምራትን እንደሚያደርግ አታውቁምን? በሆነ ምክንያት ያሑዋሕ ለእኛ ያቀረበልንን ጥቅሞች ስናጠፋቸው ነበር፡፡ ውብ የሆኑትን የያሑዋሕ ነገሮች ሁሉ ቸል እያልናቸው ነበር፡፡

ጠንቋዮች፥ መተተኞችና ደጋሚዎች በምድራችን አሉ፡፡ በሰዎች ልብ ውስጥ ስላለው ረሀብ ይናገራሉ፡፡ ሰዎች ለህይወታቸው ምክርንና አቅጣጫዎችን ከሁሉም ምንጮች ይጠይቃሉ፡፡ ሆኖም ግን፥ ያሑዋሕ ያለና እውነተኛ እንደሆነ እየነገርኳችሁ ነው፡፡ ጠንቋዮችን እንድንከተል አይፈልግም፡፡ በዓለም ያለውን መተትና ጥንቆላ/ ድግምት ማየት አይፈልግም፡፡ ያሑዋሕ መተተኞችንና መናፍስትን ስለመከተል በተቃውሞ ይናገራል፡

> *ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ፤ እንዳትረክሱባቸውም አትፈልጉአቸው፤ እኔ ያሑዋሕ አምላካችሁ ነኝ።* (ዘሌ.19:31)

ለእርዳታና ለምሪት ወደ ጠንቋዮችና መናፍስት ጠሪዎች መሄድ በጣም ኃጢአት ነው፡፡ ይልቁንም፥ የያሑዋሕ መላእክት የእውነትና መዳንን የምንወርስ እኛን ለማገልገል የተላኩ ናቸው፡፡

> *በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤* (መዝ.91:11)
>
> *በጭንቀታቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው፤ በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፥ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው።* (ኢሳ.63:9)
>
> *ናቡከደነፆርም መልሶ፡ መልአኩን የላከ፥ ከአምላካቸውም በቀር ማንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የንጉሡንም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን ያዳነ፥ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎም አምላክ ይባረክ።* (ዳን.3:28)

## ወታደር መላእክቶች

ጌታ ኢየሱስ የሲኦልን ራዕይ ሲሰጠኝ፥ በመንፈሳዊ ዓይኖቼ በቤቴ ዙሪያ ሁሉ በሰማይ ላይ የያሑዋሕ ቃል ተጽፎ ይታየኝ ነበር፡፡

በቤቴ ዙሪያና ውጪ ታላቅ የመላእክት ስብስብ ይታየኝ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ቁጭ ብለው እርስ በእርሳቸው እየተነጋገሩ ነበር፡፡ ሌሎቹ ቡድኖች ደግሞ የስልጣን ዓይነት አስተያየት አላቸው እናም በጥበቃ ላይ ያሉ ይመስላል፡፡ ሌላኛዎቹ ሦስተኞቹ የመላእክት ቡድኖች ደግሞ ክንፎቻቸውን ጫፍና ጫፍ አገጣጥመው ጀርባቸውን ለቤታችን ሰጥተው ቆመዋል፡፡ ይሄኛው የመጨረሻው ቡድን ደግሞ ሁሉም ወታደሮች የሚመስሉ ረዣዥም መላእክቶች አሉበት! እያንዳንዱ ረዥም ሰይፍ ጎኑ ላይ አለ፡፡ ጥቁር ጥላ እንኳን ወደ ቤቴ ሊያልፍ ቢሞክር፥ ሰይፋቸውን ይመዝዙና ቤተሰቤን ይከላከላሉ፡፡

አስታውሱ፥ "*የመንፈስ ቅዱስ ሰይፍ … የያሑዋሕ ሰይፍ ነው፡፡*" (ኤፌሶን 6:17) ቃሉ እየተንበለበለ ይወጣና ወደ ጠላት ይሄዳል፡፡ ጠላት ይቃጠልና ወደ አመድነት ይለወጣል፡፡

ይህ ጥቅስ ወደ እኔ መጣ፡ "*…በደለኞች ከእግራችሁ በታች አመድ ይሆናሉና…*" (ሚልኪያስ 4:3) የያሑዋሕ ቃል ያለማቋረጥ

ሲሠራ ማየቱ አስደነቀኝ፡፡

ያሑዋሕ ቃሉን ሲልክ፥ መልአኩ ጴጥሮስን ከእስር ቤት አስመለጠው፡

> *እነሆም፥ የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ፤ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና። ፈጥነህ ተነሣ አለው። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ። መልአኩም፦ ታጠቅና ጫማህን አግባ አለው፥ እንዲሁም አደረገ። ልብስህንም ልበስና ተከተለኝ አለው። ወጥቶም ተከተለው፤ ራእይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደ ሆነ አላወቀም። የመጀመሪያውንና የሁለተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ፤ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው፤ ወጥተውም አንዲት ስላች አለፉ ወዲያውም መልአኩ ከእርሱ ተለየ። ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ። ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ።* (ሐዋ. 12፡7-11)

## መላእክት እና ቃሉ

መላእክት ለሰዎች የተገለጡበት ብዙ ጥቅሶች አሉን፡፡ አንዳንድ ተጨማሪ ምሳሌዎች፡

> *እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ።* (ማቴ. 1፡20)
>
> *ያሑዋሕም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ፤ የያሑዋሕን መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ፤ ሰገደም፥ በግምባሩም ወደቀ።* (ዘኁ.22:31)
>
> *ያዕቆብም መንገዱን ሄደ፥ የያሑዋሕ መላእክትም ተገናኙት።* (ዘፍ.32:1)
>
> *ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በእግርጌ ተቀምጠው አየች።* (ዮሐ.20:12)
>
> *የጌታም መልአክ ፊልጶስን። ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው።* (ሐዋ.8:26)
>
> *የእርሱ የምሆንና ደግሞ የማመልከው የያሑዋሕ መልአክ በዚህች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ ነበርና፥* (ሐዋ.27:23)

እንደ ክርስቲያን ምን ያህል ጥበቃ እንዳለን ልንረዳ ይገባል፡፡ ያሑዋሕ በቅዱስ ቃሉ ውስጥ ሁሉን ነገር እንዳዘጋጀልን የግድ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ እርዳታ ሲያስፈልገን፥ ባስፈለገን ጊዜ በድፍረት ወደ እርሱ መቅረብ እንችላለን፡፡ በጸጋው ዙፋን ፊት፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፥ እርዳታ እንጠይቀዋለን፡፡ እኔና እናንተ እገዛ ስንጠይቅ፥ እርሱ ሁል ጊዜም ይሰጠናል፡፡ ትእዛዙን መጠበቃችንና እርሱን ማገልገላችንን ስንቀጥል እኛን መርዳትን ይወዳል፡፡

---

# አዲስ ዓለም እየመጣ ነው

ለብዙ ቀናት ከሲኦል ጉብኝቴ በኋላ፥ በጽኑ ታምሜ ነበር፡፡ ስተኛ መብራቱ እንደበራ መተኛት ነበረብኝ፡፡ በሁሉም ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ አጠገቤ ያስፈልገኝ ነበር፥ እንዲሁም ያለማቋረጥ እፈልገዋለሁ፡፡ ነፍሴ በጽኑ መረበሽ ውስጥ ነበረች፡፡ አንዳንድ የጠፉትና ወደ ሲኦል የሚሄዱት የሚቀበሉትን አይቼዋለሁ፡፡

ኢየሱስ፥ "*ሰላም ሁን (ዝም በል)፥ ጸጥ በል*" (ማር. 4፡39) ይላል፥ እናም ሰላም በነፍሴ ይጎርፋል፡፡ ሆኖም፥ ከተወሰነ አፍታዎች በኋላ መጮህ እጀምራለሁ፥ በፍርሀት እሸበራለሁ፡፡

በእነዚህ ጊዜያት፥ ፈጽሞ ብቻዬን እንዳልነበርሁና ኢየሱስ ሁልጊዜም አብሮኝ እንደነበረ አውቃለሁ፡፡ ቢሆንም ግን፥ በዚህ እውቀት እንኳን፥ አንዳንዴ ህልውናው (መገኘቱ) አይሰማኝም፡፡ አንዳንዴ ወደ ሲኦል ተመልሶ ከመሄድ ፍርሃት የተነሣ ኢየሱስ እንኳ

አጠገቤ ሲሆን እፈራለሁ፡፡

ለሌሎች በሲኦል ስለነበረኝ ገጠመኝ ስነግራቸው፥ አይሰሙኝም፡፡ እለምናቸዋለሁ፥ "እባካችሁ፥ ከመርፈዱ በፊት ከኃጢአታችሁ ንስሐ ግቡ፡፡" ስለተቀበልኩት መከራ፥ እንዲሁም ኢየሱስ ስለሲኦል እንድጽፈው የነገረኝን የነገርኳቸውን ለማመን ለብዙዎች የማይቻል ነበር፡፡

ጌታ በድጋሜ አስረግጦ እርሱ ፈዋሽ ጌታ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ባያሳምነኝም ሁሌም ሙሉ በሙሉ እፈወሳለሁ፥ ፍጹሙ ፈውስ፥ በቀስታ ነገር ግን በእርግጠኝነት፡፡

# የሰላም ገነት

ከዚያም እንደገና ሆነ፡፡ በድጋሚ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ነበርሁ፥ ወደ ሰማይ ከፍ ብለን እየበረርን ነበር፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "*የያሑዋሕን ፍቅርና መልካምነት እንዲሁም ገነትን በከፊል ላሳይሽ እፈልጋለሁ፡፡ የጌታን ድንቅ ሥራ እንድታዩ እፈልጋለሁ፥ እነርሱም ለማየት የተዋቡ ናቸው፡፡*"

አንድ መልአክ እንዲህ አለኝ፡- "*የአምላክሽ የያሑዋሕን መልካምነቱና ቅንነቱን እዩ፡፡ ምህረቱ ለዘላለም ነው፡፡*"

ድጋሚ ሲናገር እንባዬን ያመጣው መልአክ የሆነ ፍቅርና ርኅራኄ አለው፥ "*እነሆ የያሑዋሕ ኃይልና ታላቅነት እንዲሁም ግርማ፡፡ ለልጆች ያዘጋጀውን ስፍራ ላሳይሽ፡፡*"

በድንገት፥ የሆነ ፕላኔት ኪፊታችን ይታይ ነበር፥ ከምድር እኩል የሚመስል ፕላኔት፡፡

> *አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከያሑዋሕ ዘንድ ስትወርድ አየሁ።* (ራእ. 21፡1)

ቀጥሎ የሰማሁት ነገር የአብን ድምጽ ነበር፥

> ***አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው፡፡ አብና ወልድ አንድ ናቸው፥ እንዲሁም አብና መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው፡፡ ማንም ሰው እንዳይጠፋ ልጄን በመስቀል እንዲሞት ላከሁት፡፡ ለልጆቼ ያዘጋጀሁትን ስፍራ ላሳይሽ ነው፡፡ ስለሁሉም ልጆች በኃይል ግድ ይለኛል፡፡ እናት ልጇን ስታጣ ግድ ይለኛል፥ የማኅፀን ፍሬ እንኳን ያለጊዜው ሲወጣ፡፡ አየሽ ሁሉንም አውቃለሁ፥ ግድም ይለኛል፡፡***
>
> ***ነፍስ በማኅፀን ካለችበት ጊዜ ጀምሮ፥ አውቃለሁ፡፡ ገና በእናታቸው ማኅፀን ውስጥ እያሉ ስለተገደሉት ሕፃናት አውቃለሁ- ውርጃ የተፈጸመባቸው የተቆረጡትና የማይፈለጉት፡፡ ገና ስለተወለዱትና ከአካል ጉዳት ጋር ስለሚወለዱት አውቃለሁ፡፡ ከመፀነሱ ጊዜ አንሥቶ እያንዳንዱ ነፍስ ነው፡፡***
>
> ***መላእክቴ ልጆቼን ሲሞቱ ወደ እኔ ለማምጣት ይወርዳሉ፡፡ በገነት የተወደዱ ናቸው፥ እናም ፍጹማን ፍጥረታት ይሆናሉ፡፡ ሙሉ ሰውነትን እሰጣቸዋለሁ እንዲሁም ማንኛውም የጎደለውን የሰውነት ክፍል አድስላቸዋለሁ፡፡ ፍጹም ሰውነትን እሰጣቸዋሁ፡፡***

በፕላኔቷ ሞላ የመወደድ ስሜት ነበር፥ ፍጹም ደህና የመሆን ስሜት፡፡ ሁሉም ነገር ፍጹም ነበር፡፡ እዚህም እዚያም በተንጣለለው ሳርና ኩልል ባለው ውኃ መሀል የእምነበረድ መቀመጫዎችና እጅግ ያጌጡ የእንጨት አግዳሚ ወንበሮች ነበሩ፡፡

በተመለከትኩበት ሁሉ፥ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተጠመዱ ልጆች ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ምንም እንከን የሌለበት ልብስና ጥልፍልፍ ጫማ አድርጓል፡፡ ነጩ ልብሳቸው በጣም ደማቅ ከመሆኑ የተነሳ በፕላኔቷ ላይ የሚያንጸባርቅ ብርሃንን ይሰጣል፡፡ በየስፍራው ያሉት እጅግ የበዙት ቀለማት በልጆቹ ልብስ ላይ ያለውን ንጣት የበለጠ እንዲጎላ አድርጎታል፡፡ ደጆቹን የሚጠብቁት መላእክት ነበሩ፥ እናም የእያንዳንዱ ልጅ ስም በመጽሐፍ ተጽፏል፡፡

ልጆቹ የያሑዋሕን ቃልና ሙዚቃን ከውርቃማ መጽሐፍ ላይ ሲማሩ አየሁ፡፡ ልጆቹ በእነዚህ የመላእክት ትምህርት ቤቶች እያሉ የተለያዩ ዓይነት እንስሳት ወደ ልጆቹ ሲመጡ ወይም አጠገባቸው ሲቀመጡ ሳይ ተደንቄ ነበር፡፡

ምንም እንባና ኀዘን አልነበረም፡፡ ሁሉም ነገር ከመጠን በላይ ውብ ነበር፡፡ ሀሴትና ደስታ በየቦታው ነበር፡፡

ከዚያም መልአኩ በፊቴ በታላቅ ብርሃን የሚያበራ ሌላ ፕላኔት አሳየኝ፡፡ ብርሃኑ እንደ ሚሊየኖች ኮከቦች ድምቀት ያበራ ነበር፥ እናም በፕላኔቱ ላይ ያለው እያንዳንዱ ነገር የተዋበና ሕያው ነበር፡፡ በርቀት ከንጹህ ወርቅ የተሠሩ ሁለት ተራሮችን አየሁ፥ በአቅራቢያዩም ሁለት ወርቃማ ደጆች ነበሩ፥ በነዚያም እንቁዎችና የከበሩ ድንጋዮች ተቀብረውባቸው ነበር፡፡

በልቤ ይህች በሚያስደንቅ ሁኔታ በፊቴ የተዘረጋችው ከተማ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም እንደሆነች አውቄ ነበር-ወደ ምድር የምትመጣው የያሑዋሕ ከተማ፡፡

## እንደገና ምድር

በፍጥነት፥ የቀደመችውን ምድር ወደማየት ተመለስሁ፥ ነገር ግን ምድር ከታላቁ መከራ በኋላ ግን ደግሞ የመጨረሻው የአርማጌዶን እሳት ፈጽሞ ሳያጠራት፡፡ በዚህ እይታ ውስጥም፥ ኢየሩሳሌምን አየሁ፥ የሺህ ዓመቱ ዋና ከተማ፡፡

በራእዩ ውስጥ፥ ሰዎች ከሩቅም ከቅርብም፥ መንገዳቸውን ወደ ከተማይቱ አደርገው፥ ሲመጡ አየሁ፡፡ በዚህ ኢየሱስ ንጉሥ ነበር፥ እናም የምድር አሕዛብ ሁሉ ስጦታን ያመጡና ስግደትን ያቀርቡለት ነበር፡፡ በእርግጥ ንጉሥ ብቻ አልነበረም፥ ነገር ግን እንደ የነገሥታት ንጉሥ ይታወቅ ነበር!

ኢየሱስ የራእዩን ትርጓሜ ሰጠኝ በዚያን ጊዜም ስለሚሆነው ነገር ግልጽ አደረገልኝ፡፡

በቅርቡ ወደ ምድር እመለስና የሞቱትን ጻድቃን አስቀድሜ ወደ ገነት ወስዳቸዋለሁ፡፡ ከዚያም ከእነርሱ ቀጥሎ፥ ህያዋን የሆኑትና የቀሩት ከእኔ ጋር በአየር ላይ ይነጠቃሉ፡፡ ያንን ተከትሎ፥ የክርስቶስ ተቃዋሚው ለተቀጠረለት ጊዜ ያህል በምድር ላይ ይገዛል፥ ከዚያ ከዚያ በፊት ሆኖ የማያውቅ፥ ከዚያ በኋላም የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናል፡፡ ከዚያም ከቅዱሳኔ ጋር እመለሳለሁ፥ እናም ሰይጣን ወደ ጥልቁ ይጣላል፥ በዚያም ለአንድ ሺህ ዓመት ይቆያል፡፡ በሺህ ዓመት ጊዜ ውስጥ፥ በምድር ላይ ከኢየሩሳሌም እነግሣለሁ፡፡ ሺሁ ዓመት ሲያልፍ፥ ሰይጣን ለተወሰነ ወቅት ይለቀቃል፥ እናም እኔ በመምጣቴ ብርሃን አሸንፈዋለሁ፡፡ አሮጌው ምድር ያልፋል፡፡ እነሆ፥ አዲስ ምድርና አዲስ ኢየሩሳሌም በእርሱ ላይ ይወርዳል፥ እናም ከዘላለም እስከዘላለም እነግሣለሁ፡፡

---

# የክርስቶስ መመለስ

በሌላ ራእይ፥ የጌታን መምጣት አየሁ! እንደ መለከት ድምጽና የመልአክ ድምጽ ያለውን ጥሪውን ሰማሁ፡፡ (1ኛ ተሰሎንቄ 4:16) መላዋ ምድር ተናወጠች፥ ከመቃብሮችም የሞቱት ቅዱሳን ጌታን በአየር ላይ ለመገናኘት ወጡ፡፡

ለሰዓታት በሚመስል ርዝመት፥ መለከቶቹ ሲነፉ ሰማሁ፡፡ ምድርና ባሕር ሙታኖቻቸውን ሰጡ (ራእይ 20:13) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእሳት መጎናጸፊያን ለብሶ በደመና ላይ ቆሟል፥ እነሆ የሚደንቅ ትእይንት፡፡ የመለከቶቹን ድምጽ በድጋሜ ሰማሁ፡፡ እያየሁም ሳለ፥ ህያዋን የሆኑትና በምድር ላይ የቀሩት እነርሱን ለመቀላቀል ወደ ላይ አረጉ፡

> *ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን ያሑዋሕ ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በያሑዋሕም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።* (1ኛ ተሰሎንቄ 4:14-17)

የተዋጁትን አየሁ፥ በሰማይ ያለን የመሰብሰቢያ ስፍራ ሸፍነው፥ እንደ ሚሊየኖች የብርሃን ነጠብጣቦች ነበሩ፡፡ በዚያ መላእክት እጅግ ንጹህ የሆነውን ነጭ ልብስ ሰጧቸው፡፡ ይህ ታላቅ ፌሽታ ነበር፡፡ ማገልገል የመላእክቱ ድርሻ ነበር፥ (ከሙታን) ለተነሡት ልዩ እንክብካቤን እያደረጉ በየስፍራው ነበሩ፡፡ ለተዋጁት አዲስ የከበረ ሰውነት ተሰጣቸው፥ እናም በአየሩ ውስጥ ሲያልፉ ይለወጡ ነበር፡፡

ታላቅ የሆነ ሀሴት ሰማያትን ሞላ እናም መላእክቱ *"ክብር ለነገሥታት ንጉሥ!"* እያሉ ዘመሩ፡፡

## የክርስቶስ አካል

በዚህ ራእይ ውስጥ፥ ረዥም መንፈሳዊ አካል በሰማያት ላይ ከፍ ብሎ አየሁ፡፡ የክርስቶስ አካል ነበር፥ በጀርባው ተኝቶ ደም ወደ ምድር ይንጠባጠብ ነበር፡፡ ይህ የታረደውን የጌታችንን ሰውነት እንደሚወክል አወቅሁ፡፡ አካሉ ሰማያትን እስኪሸፍን ድረሽ እያደገ እያደገ ሄደ፡፡ ወደ ውስጡም ሚሊየኖች የተዋጁት ቅዱሳን ይሄዱ ነበር፡፡

ሚሊየኖች በመሰላል እየወጡ ሲሞሉት በመደነቅ ተመለከትሁ፥ ከእግሩ ጀምረው፥ በቅልጥሞቹ በክንዶቹ፥ በሆዱ፥ በልቡ፥ እናም በጭንቅላቱ፡፡

ሲሞላ፥ ከሁሉም የምድር ማእዘናት በመጡ ሰዎች እንደተሞላ አየሁ፡፡ በታላቅም ድምጽ ጌታን አወደሱ፡፡

> *መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለያሑዋሕ ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።* (ራእ. 5፡9-10)

በዙፋኑ ፊት ሚሊየኖች ተሰብስበው ነበር፥ ከዚያም መላእክት ፍርድ የሚነበብባቸውን መጻሕፍት ሲያመጡ አየሁ፡፡ በዚያም የምህረት ዙፋኑ ነበረ፥ ብድራቶችም (ሽልማቶችም) ለብዙዎች ተሰጡ፡፡

ከዚያም፥ በመደነቅ እያየሁ ሳለ፥ ጨለማ የምድርን ገጽ ሸፈነ፥ እናም የኢጋንንት ኃይሎች በየስፍራው ወጡ፡፡

የማይቆጠሩ እርኩሳን መናፍስት ከእስራቸው ተፈትተው በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ሌላ ታላቅ ድምጽ እንዲህ ሲል ሰማሁ፡

> *ስለዚህ፥ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤ ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።* (ራእ. 12፡12)

## የያሑዋሕ ቁጣ

የተቆጣ አውሬን ተመለከትሁ፥ መርዙንም ሁሉ በምድር ላይ አፈሰሰ፡፡ ምድር ከቁጣው የተነሣ ተናወጠች፥ ከዚያም የእርኩሳን ፍጥረታት (መናፍስት) ሠራዊት ከብዛታቸው የተነሣ ምድርን ለማጨለም ከጥልቁ ወጡ፡፡

ወንዶችና ሴቶች እየጮኹ ወደ ኮረብታዎች፥ ወደ ዋሻዎችና፥ ወደ ተራሮች ሮጡ፡፡ እናም በምድር ላይ ጦርነቶች፥ ችጋርና ሞት ነበሩ፡፡ በመጨረሻ በሰማይ የእሳት ፈረሶችና ሰረገላዎችን አየሁ፡፡ ምድር ተናወጠች፥ *"ፀሐይም እንደ ማቅ ጸጉር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላ እንደ ደም ሆነ"* (ራእ. 6፡12)

አንድም መልአክ *"ምድር ሆይ አድምጪ፥ ንጉሡ እየመጣ ነው!"* ሲል አወጀ፡፡

ከዚያም የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ በሰማይ ተገለጠ፡፡ ከእርሱም ጋር በሚያስደንቅ ክብር በሁሉም እድሜ ያሉ ቅዱሳን ነበሩ፥ የጸዳ ነጭ ልብስን ለብሰው፡፡ *"ዓይን ሁሉ ያዩታል"* (ራእ. 1፡7) እንዲሁም *"ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከካል"* ጌትነቱንም *"...ምላስም ሁሉ ይመሰክራል"* (ራእይ. 14፡11) የሚለውን አስታወስሁ፡፡

ከዚያም መላእክቱ ማጭዳቸውን ይዘው የደረሰውን ዘር አጨዱ (ራእይ. 14፡14-19)፥ ይህም የዓለም ፍጻሜ ነው፡፡

*እንዲህ አሰብሁ፥ "እርስ በእርሳችን ልንዋደድ ይገባናል፡፡ በእውነቱ ላይ ልንጸናና በቅርቡ በሚሆነው በክርስቶስ (ኢየሱስ) መምጣት ብርሃን ልጆቻችንን ልናስተካክል ይገባል፡፡ በእርግጥም፥ ንጉሡ ይመጣል!"*

----------------------------------------------------------------------

# የጌታ የመጨረሻ ተማጽኖ: ተዘጋጁ

ኢየሱስ እንዲህ አለኝ፥ "***ንስሐ ግቡና ዳኑ፥ የያሑዋሕ መንግሥት በመካከላችሁ ናትና፡፡ ፈቃዴና ቃሌ ይፈጸማል፡፡ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፡፡***" ከዚያም አወጀ:

> *በአሁኑ ዘመን ባለጸጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው ያሑዋሕ እንጂ በሚያልፍ ባለጸግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው።* (1ጢሞቴዎስ 6፡17)
>
> *ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።* (ገላቲያ 5፡16)
>
> *አትሳቱ፤ ያሑዋሕ አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።* (ገላ. 6፡7)
>
> *የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የያሑዋሕን መንግሥት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።* (ገላ. 5፡19-24)
>
> ኢየሱስ ቀጠለና:
>
> ***የያሑዋሕ ቃል ሲፈጸም፥ ያኔ መጨረሻው የምጣል፡፡ የሰው ልጅ ወደ ምድር የሚመለስበትን ሰዓቱንና ጊዜውን ማንም ሰው አያውቅም፡፡ ልጁ ራሱ አያውቅም፥ በአብ ብቻ የታወቀ ነውና፡፡ ቃሉ በፍጥነት እየተፈጸመ ነው፡፡ እንደ ትናንሽ ልጆች ኑና፥ ከሥጋ ሥራ ልቀድሳችሁ፡፡ እንዲህ በሉኝ፥ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ወደ ልቤ ናና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፡፡ እኔ ኃጢአተኛ እንደሆንሁ አውቃለሁ፥ እናም ከኃጢአቴ ንስሐ እገባለሁ፡፡ በደምህ ውስጥ እጠበኝ፥ ንጹህም አድርገኝ፡፡ በሰማይና በአንተ ፊት በድያለሁና ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም፡፡ በእምነት እንደ አዳኜ እጠራሀለሁ፡፡" እንደ ልቤ የሆኑ መጋቢዎችን እሰጣችኋለሁ፥ እኔም እረኛችሁ እሆናለሁ፡፡ እናንተም ሕዝቤ ትሆናላችሁ፥ እኔም አምላካችሁ እሆናለሁ፡፡ ቃሉን አንብቡ፥ እናም እርስ በእርሳችሁ መሰባሰብን አትተዉ፡፡ መላ ህይታችሁን ለእኔ ስጡኝ፥ እኔም እጠብቃችኋለሁ፡፡ ፈጽሞ አልተዋችሁም አልጥላችሁምም፡፡***

## ያሑዋሕን ለመገናኘት ተዘጋጁ

የተወደዳችሁ ሆይ፥ ከልቤ ጥልቀት፥ በሁሉንቻዩ አምላክ ኃይል የተሰጡኝን አብዛኞቹን ራእዮችና መገለጦች ከልቤ ጥልቀት አካፍያችኋለሁ፡፡ ያሑዋሕ(እግዚአብሔር) ምን ያህል እንደሚወደን በመግለጽ ሳቤን ማጠቃለል እፈልጋሁ፡፡ መራራቱንና ታላቅ የሆነውን ፍቅሩን ታላቅ የሆነ ቃሉን በመላክና መገለጡንም ለእኛ በመስጠት በእነዚህ የመጨረሻ ዘመናት አሳየን፡፡

የተወደዳችሁ ልጆች፥ ጌታን ለመገናኘት ዝግጁ መሆን ይኖርብናል፡፡ በሁሉም ጊዜ መምጣቱን ልንጠባበቅ ይገባናል፡፡ እኔና እናንተ አሁን ያለንባቸውን መከራዎች፥ ጊዜያትና ወቅቶች እናውቃለን፡፡ እንደዚህ ያለ ዘመን ፈጽሞ አልነበረም፡፡

በሙሉ ልቤ እንድትዘጋጁ አስቸኩላችኋለሁ፥ "*የሰው ልጅ የሚመጣበትን ቀኒቱንና ሰዓቱን አታውቁምና*" (ማቴ. 25፡13) ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ እየመጣ ነው!

አሁን በገነት ስላሉት ቅዱሳን እንዴት እንደተናገርሁ ታስታውሳላችሁ? የያሑዋሕ መልአከ በክርስቶስ ኢየሱስ በጽድቅ ከኖርን፥ ውዶቻችን (ዘመዶቻችን) ወደዚያ ስንገባ በክብር (በገነት) ደጃፍ እንደሚቀበሉን ነግሮኛል፡፡

ይህን ውብ መልእክት ወደ ልባችሁ ውስጥ እየተቀበላችሁ ነው?

መላእክቶች ስለሚጠብቋቸው (ስለሚመዘግቧቸው) መጻሕፍትና መዝገቦች አውርቻለሁ፡፡ ስለ**ኢየሱስ** ብለን የምናደርገው ነገር ሁሉ ተመዝግቧል፥ እናም ብድራቶቻችን ከምድር ይልቅ በሰማይ እጅግ የበለጡ ናቸው፡፡ መላእክት መሻቶቻችንን ይጽፋሉ፡፡

ብዙ ጊዜ ወንጌላውያን፥ ሰባኪዎች፥ አስተማሪዎች፥ እንዲሁም ሌሎች መሪዎች በጊዜያዊነት ቤታቸውን፥ ልጆቻቸውን፥ እንዲሁም የትዳር አጋራቸውን ትተው የ**ክርስቶስ**ን መስቀል ለመሸከም ይሄዳሉ፡፡ **ጌታ** ይህን ይመለከታል፥ ስለዚህም ነገር ሁሉንም ያውቃል፡፡

እንዲሁም የሆነ ቦታ ሄደን እንደ ጌታ ልጆች የማንታይባቸውን ብዙዎቹንም ጊዜያት ያውቃል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአግባቡ አንታይም፥ እንደዚያም ሆኖ እኛ ግን የንጉሡ ልጆች ነን፡፡

አሁንም፥ ***ያሑዋሕ*** የአገልጋዮች አገልጋዮች እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ እርሱ እንዳገለገለን አንዳችን አንዳችንን እንድናገለግል ይፈልጋል፡፡

ቅዱሳን፥ ***ያሑዋሕ*** የጽጌረዳ አበባ መናፈሻ አይደለም ቃል የገባልን፡፡ ምንም እንኳን በዚህ ምቾትን ቃል ባይገባልንም፥ በረከቶች፥ ሀብቶች፥ ክብር፥ እንዲሁም ቁሳዊ ነገሮች ግን ***ያሑዋሕ*** እንደፈቀደ ሊኖሩን ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን፥ እነዚህ መስቀሉን ተሸክመን **ክርስቶስ**ን እየተከተልን ሊኖሩን ይችላሉ፡፡

ዝግጁ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ፡፡ **ኢየሱስ**ን እንደ ጌታና አዳኝ አድርጋችሁ ካልተቀበላችሁ፥ ልትድኑ ትችላላችሁ፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል፥

> *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ ያሑዋሕ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።* (ዮሐ.3:16)
>
> *ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር ያሑዋሕም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።* (ሮሜ.10:9-10፣13)

እባካችሁ አሁን ይህን ጸሎት ጸልዩ፥

> **አባት** ሆይ፥ በ**ኢየሱስ ክርስቶስ ስም**፥ እንዲሁ እንዳለሁ፥ ወደ አንተ መጣለሁ፡፡ **ጌታ** ሆይ፥ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፡፡ እኔ በአንተና በሰማይ ፊት በድያለሁ፡፡ **ጌታ ኢየሱስ** ሆይ፥ ይቅር እንድትለኝና ወደ ልቤ ገብተህ ነፍሴን እንድታድናት እጠይቅሀለሁ፡፡ እባክህ በ**ህያው አምላክ መንፈስ** ዳግም ልወለድ፡፡
>
> **ጌታ ኢየሱስ** ሆይ፥ ህይወቴን ለአንተ እሰጣለሁ፡፡ አንተ የ**ያሑዋሕ ልጅ** እንደሆንህ አምናለሁ፡፡ ነፍሴን ከሲኦል ለማዳን የተላክህ አንተ **ኢየሱስ ክርስቶስ** እንደሆንህ አምናለው፡፡ በከበረው ደምህ ስላዳንከኝ (ስለዋጀኸኝ) ምስጋናና ውዳሴን ለአንተ አቀረባለሁ፡፡

ይህን ጸሎት ከእኔ ጋር ከጸለያችሁና እንደጸለያችሁ የእውነት ካመናችሁ፥ አሁን ድናችኋል፡፡ **ኢየሱስ ክርስቶስ**ን ወደ ልባችሁ ጠይቃችሁታል፡፡ በአንደበታችሁ እርሱን ማወጅና ማወደስ ጀምሩ፡፡

ውዳሴና ክብር ሁሉ ለ**ያሑዋሕ**(ለ**እግዚአብሔር**) ይሁን!

------------------------------------------------------------

# ስለ ጸሐፊዋ

ሜሪ(ማርያም) ካትሪን ባክስተር የተወለደችው በቻታኑጋ፥ ቴኒሴ ውስጥ ነበር፡፡ ወደ ያሑዋሕ ቤት መጣች፡፡ ገና ልጅ እያለች፥ እናቷ ስለኢየሱስ ክርስቶስና ስለማዳኑ አስተማረቻት፡፡

ካትሪን ዳግም የተወለደችው በአስራ ዘጠኝ ዓመት እድሜዋ ነበር፡፡ ጌታን ለብዙ ዓመታት ካገለገለች በኋላ፥ ለተወሰነ ጊዜ ወደ ኋላ ተመለሰች፡፡ የጌታ መንፈስ የሚለቅቃት አልነበረም፥ ከዚያም ድጋሚ ተመልሳ ህይወቷን ለክርስቶስ ሰጠች፡፡ እስካሁንም ድረስ በታማኝነት ታገለግለዋለች፡፡

በ1960ዎቹ አጋማሽ ካትሪን ከቤተሰቦቿ ጋር፥ ለተወሰነ ጊዜ ወደኖረችበት፥ ወደ ዲትሮይት፥ ሚሺጋን ሄደች፡፡ በኋላ ላይም ከያሑዋሕ ዘንድ ራእይ ወዳገኘችበት ወደ ቤልቪል፥ ሚሺጋን ሄደች፡፡

አገልጋዮች፥ መሪዎች፥ እንዲሁም የጌታ ቅዱሳን ስለእርሷና ስለአገልግሎቷ በጣም ይናገራሉ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በአገልግሎቶቿ ሁሉ ጎልቶ ይታያል፥ ብዙ ድንቆችም ይሆኑባቸዋል፡፡ በጉባኤዎቿ ላይ በመንፈስ ስትመራ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ኃይልን በመገለጥ ይገለጣሉ፡፡ ጌታን በሙሉ ልቧ፥ ሀሳቧ፥ነፍሷ፥ እንዲሁም ኃይሏ ትወድዳለች እንዲሁም ከሁሉ በላይ ለኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሳትን የሚያድን መሆንን ትሻለች፡፡

በእውነት የተሰጠች የያሑዋሕ አገልጋይ ናት፡፡ ጥሪዋ በልዩነት በሕልሞች፥ ራእዮችና መገለጦች ላይ ነው፡፡ በ1983 ዓ.ም በቴለር፥ ሚሺጋን በሚገኝ የሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ውስጥ በአገልጋይነት ተሹማለች፡፡ አሁን በ"ናሽናል ቸርች ኦፍ ጋድ" ዋሺንግተን ዲሲ ውስጥ ታገለግላለች፡፡

በ1976፥ በቤሊቪል ስትኖር፥ ኢየሱስ በሰው አምሳል ተገለጠላት፥ በህልሞች፥ በራእዮች፥ እንዲሁም በመገለጦች፡፡ ከዚያን ጊዜ አንስቶ ከጌታ ዘንድ ብዙ ጉብኝቶች ሆኖላታል፡፡ በእነዚያ ጊዜያቶች በሲኦል ያሉ የጠፉ ነፍሳትን ስቃይ ጥልቀት፥ መጠን፥ ደረጃ አሳይቷታል፡፡ እንዲሁም ብዙ የገነት ጉብኝቶችን፥ ስለታላቁ መከራ፥ እንዲሁም ስለመጨረሻው ዘመን ራእዮችን ተቀብላለች፡፡

በህይወት ዘመኗ፥ ለአርባ ቀናት ያህል ኢየሱስ በየቀኑ ሌሊት ሌሊት ይገለጥላት ነበር፡፡ የሲኦልን ክፉትና የገነትን ክብር ገልጦላታል፡፡ ይህም መልዕክት ለመላው ዓለም እንደሆነ ነግሯታል፡፡

**እኛ እንደ ያሑዋሕ(እግዚአብሔር) ልጆች በመታደስ ተዓምር አዲስ ተደርገን ተለውጠናል፡፡**

# ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

**የእግዚአብሔር አብ** ባሪያዎች፥ **የጌታም የኢየሱስ ክርስቶስ** ደቀ መዛሙርት፥ **የመንፈስ ቅዱስም** አገልጋዮች የሆኑ፥

ሊያደርጉ የሚገባቸውን ያደረጉ የማይጠቅሙ ባሪያዎች ሙሉነህ አዲሱና ቶማስ ጌታቸው፥ በቅዱሱ የእስራኤል ኃያል በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ፥ በጌታችንና በአዳኛችን በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጸጋና ቅዱስ መንፈስ መሪነት ተረጎሙት። ክብር፥ ጥበብ፥ ኃይል፥ በረከት፥ ምስጋና፥ ቅድስና፥ ውዳሴ፥ አምልኮ፥ ማዳን ለቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ይሁን፥ አሜን ሃሌ ሉያ አሜን። ቅዱስና ጻድቅ የሰማዩ አባታችንና አምላካችን ቡሩክና ከሁሉ በላይ ቅዱስ ምስጉን ደግ የሆንህ መካሪያችን አሳዳጊያችን ጠባቂያችን ወዳጃችን የእስራኤል አምላክ ቸሩ ጌታ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ ተባረክ!!!

shalommuluneh@gmail.com, hithomasgetachew@gmail.com። **ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እግዚአብሔር ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ያድናል**

**ክብር ሁሉ ለወደደንና ላፈቀረን በመስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ ለቀደሰን በአባቱ ፈቃድም ዕለት ዕለት በንጽኀና እግዚአብሔርን በመፍራት ለሚመራን፥ ለፈጠረን፥ አንድ አምላክ ለሆነ ለነገሥታት ንጉሥና ለጌታዎች ጌታ ለናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስና ጻድቅ አባቱም ለቅዱስ መንፈሱም ይሁን፥ አሜን ሃሌሉያ። ቅዱስ አባታችን ጌታችን ወዳጃችን አዳኛችን ሕይወታችን መንገዳችን እውነታችን መልካም በጎ እረኛችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቶሎ ና። ተጠምተንሃልና የኛ ጌታ የኛ ፍቅር የኛ አምላክ የኛ አማላጅ የኛ በረከት የኛ ፈራጅ የኛ ንጉሥ ሙሽራችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ና ቶሎ ና ቶሎ ና ቶሎ ና። ከጣዖታት ሁሉ ርቀናል። ጌታ ኢየሱስ ሆይ** አንተን ለመቀበል በቅዱስ መንፈስህ በቃልህም በአባትህም ፈቃድ ከኃጢአት ርቀን ተዘጋጅተናል በጸጋህም በአንተም እምነት በአንተም በመኖር በቸርነትህና በቅዱስ ፍቅር መንፈስህ ርዳታ ፍሬ እያፈራን ጸንተናል፥ **የቅዱስ አባትህ የእግዚአብሔር አብ ፍቅር፥ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ወልድ ጸጋ፥ የቅዱስ መንፈስህም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን ሃሌ ሉያ አሜን**